ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 079 ኅዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# ዘላቂ ሰላም ለሕዝብ ተጠቃሚነት

**ፋንታነሽ ክንዴ**




በሰሜን ዕዝ ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ሰላም ርቆት ቆይቷል፡፡ በአፍሪካ ኅብረት መሪነት በደቡብ አፍሪካ የተፈረመው የሰላም ስምምነት ግን አካባቢው ላይ ሰላም እንዲሰፍን ያደርጋል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ ይህ ተስፋ መሬት ወርዶ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ግን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላም ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶክተር ዮናስ አዳዬ እንደሚሉት፤ ስምምነቱ ተስፋ ሰጪና እንደ አገር ሊካሄድ ለታሰበው አገራዊ ምክክርም ትልቅ አቅም የሚሆን ነው፡፡ ሰላምን በውይይትና በምክክር ማምጣት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል እንዲሆን ጥረት ሲደረግ ለነበረው ጥረትም ጥሩ መነሻ የሚሆን ሥራ ነው፡፡

ከጦርነት የሚያተርፉና የችግሩ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ የማያውቁ አንዳንድ አካላት ስምምነቱን ሲቃወሙ ይሰማሉ የሚሉት ዶክተር ዮናስ፤ እነዚህ አካላት ከራሳቸው የምቾች ዓለም ባለፈ በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋርም ሆነ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ያሉ ዜጎች ላይ ጦርነቱ ያደረሰባቸውን ጉዳት ሊያስተውሉ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ ሲተላለቁ ከዳር ሆነው መሣሪያ በመሸጥ ትርፍ ለማግኘት የሚፈልጉ አካላት እንዳሉ የሚያስታውሱት ምሁሩ፤ ለዓላማቸው ስኬት በማሰብም በሚዲያና በሚያወጧቸው አንዳንድ ሕትመቶች የጥላቻ መርዝ እንደሚረጩ ይጠቁማሉ፡፡

ስምምነቱን የፈረሙት ወገኖችም በሕዝቡ ውስጥ አመኔታ እንዲያገኙ የተናገሩትን ሆነው መገኘት እንዳለባቸው የሚያነሱት ዶክተር ዮናስ፤ እስካሁን ድረስ ጥሩ ተነሳሽነት እየተስተዋለ ነው ብለዋል፡፡ ሆኖም በሕወሓት በኩል አሉታዊ መልእክት እያስተጋቡ ያሉ አንዳንድ ደጋፊዎች የሰላም መንገዱን እንዳያደናቅፉ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል ብለዋል፡፡ የሰላም ስምምነቱ ከዳር ደርሶ ሕዝቡ ዘላቂ ሰላም እንዲያገኝ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በጎ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካና እስያ ጥናት ማዕከል ረዳት ፕሮፌሰር የሆኑት ሳሙኤል ተፈራ (ዶክተር) እንደሚሉት ደግሞ፤ ጦርነት በአንድ አገር ላይ

ዘላቂ ሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## «የፕሪቶሪያው ስምምነት ቅድመ ሁኔታ የለውም፤ ስለሆነም በስምምነቱ መሠረት ይፈፀማል»

- ለገሰ ቱሉ (ዶክተር)

ገጽ 4

# ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ 32 ሺህ ሜትሪክ ቶን የምግብ እህልና ከ360 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ ለትግራይ ክልል ተልኳል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




አዲስ አበባ፡- መንግሥት እና ሕወሓት ያደረጉትን የሰላም ስምምነት ተከትሎ ወደ ትግራይ ክልል 32 ሺህ ሜትሪክ ቶን የምግብ እህልና ከ360 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ ተደራሽ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሺፈራው ተክለማርያም መንግሥት የሰላም ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ሰብዓዊ ድጋፍ ወደ ትግራይ ክልል ያለገደብ ተደራሽ እያደረገ መሆኑንም ለኢዜአ ተናግረዋል፡፡

በዚህም በአራት ኮሪደሮች በየብስ እንዲሁም በመቀሌና በሽረ አውሮፕላን ማረፊያዎች በኩል እርዳታ ተደራሽ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ እስከ ኅዳር 16 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ መንግሥት በራሱ አቅም 13 ሺህ ሜትሪክ ቶን ጥራጥሬና አልሚ ምግብ፣ በእርዳታ ድርጅቶች በኩል ደግሞ 19 ሺህ ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል ወደ ትግራይ ክልል መላኩን ተናግረዋል፡፡

ባለፉት ሳምንታት ወደ ክልሉ የተላከው የሰብዓዊ እርዳታም ከ2 ሚሊዮን በላይ የክልሉ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ነው ያሉት፡፡

ከምግብ አቅርቦት ባለፈ ትግራይ ክልልን ጨምሮ በሰሜን ኢትዮጵያ ለሰብዓዊ እርዳታ ማጓጓዣ የሚውል ከ360 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ ወደ አካባቢው መላኩን ገልጸዋል፡፡

መንግሥት ከፍተኛ መድኃኒትና የሕክምና ቁሳቁስ፣ ለትምህርት ቤቶችና ለአካባቢው ነዋሪ የውሃና ለንጽህና መጠበቂያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ተደራሽ እያደረገ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ሰብዓዊ ድጋፉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመው፣ ለዚህም ከአጋር አካላትና ከዜጎች ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአማራና አፋር ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች በነበረው ግጭት የጉዳት ሰለባ የሆኑ ወገኖችን በማገዝ መንግሥት እያደረገ ካለው ጥረት ባለፈ የማህበረሰቡን

ከሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አገራዊ ለውጡ በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ ጣልቃ ገብነትን በመቀነስ መሻሻሎችን አምጥቷል

- ምሁራን

**ኤፍሬም አንዳርጋቸው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የመጣው አገራዊ ለውጥ የአስፈፃሚ አካላት በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ የሚያደርጉትን ጣልቃ ገብነትን በመቀነስ በኩል ከፍተኛ መሻሻሎችን እንዳመጣ የዘርፉ ምሁራን ገለጹ።

ምሁራኑ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ አገራዊ ለውጡ የአስፈፃሚ አካላት ዳኞች በሚመለከቷቸው የፖለቲካ እና የሕዝብን ትኩረት

አገራዊ ለውጡ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ዜና

# ምርታማነትን የሚጨምሩ 90 አዳዲስ የዘር ዓይነቶች ቀረቡ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ለረጅም ጊዜ በምርት ሂደት ውስጥ የሚቆዩና በሽታን የሚቋቋሙ የዘር ዓይነቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረጉን የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ገለጹ፡፡

አምባሳደር ድሪባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በየዓመቱ በርካታ የዘር ዓይነቶች ከተመራማሪዎች ይፈልቃሉ። ዘንድሮ ከቀረቡት ከ90 በላይ አዳዲስ የዘር ዓይነቶች በሽታን በመቋቋም ረጅም ጊዜ በምርት ሂደት ሊቆዩ የሚችሉ 35 የሚሆኑትን ሥራ ላይ እንዲውሉ ተወስኗል።

ለኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ እድገት የዘር ጥራትና ምርታማነት ወሳኝ መሆናቸውን የጠቆሙት አምባሳደር ድሪባ፤ ዘሮቹ የስንዴ፣ ማሽላ፣ የቅባት እህሎች፣ የበቆሎና ሌሎች የጥራጥሬ ዘሮች መሆናቸውን ነው የገለጹት።

አገራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግ የግብርናው ዘርፍ ወሳኝ በመሆኑና አብዛኛው ሕዝብ በግብርና ዘርፍ የሚተዳደር በመሆኑ የዘር ጥራትና ምርታማነት ለማክሮ ኢኮኖሚው የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ትልቅ ነው።

ባለስልጣኑ ከምርምር የወጡትን ዘሮች በማሳ ላይ በመሞከር፣ ላብራቶሪዎችንና ሌሎች የዘር ጥራት መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የዘሮቹን ውጤታማነት ይለካል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በኢትዮጵያ ለአርሶ አደሩ የሚሰራጩ ዘሮችን የጤና ሁኔታ ለማረጋገጥ 20 የሚሆኑ ላብራቶሪዎች አሉ ብለዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ባለስልጣኑ የዘርና የግብዓት ቁጥጥር ሥራ በማድረግ ዘር ከበሽታ ነፃ ሆኖ ተፈላጊውን መስፈርት እንዲያሟላ በዚህ አመት ወደ 35 የሚጠጉ የዘር ዓይነቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጓል። እነዚህም ጥራታቸውን ጠብቀው የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጡና ሕገወጥ ዘር ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ቁጥጥር እያደረገ ነው።

ተቋሙ በዘር ቁጥጥር የግል ተቋማት እንዲሳተፉ ለማድረግ አዲስ አሠራር ዘርግቶ እየተንቀሳቀሰ ነው። ይህም ኢትዮጵያ ለራሷ ብቻ ሳይሆን በምሥራቅ አፍሪካም



አምባሳደር ድሪባ ኩማ

ጭምር ዘር እያባዛች መሸጥ የምትችል እንድትሆን ያደርጋታል። ለዚህም ከምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥት (ኢጋድ) እና የምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ አገራት የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ጋር ስምምነት ተደርጓል ብለዋል።

በአገራችን የምርጥ ዘር አጠቃቀም ከዓመት ዓመት የምርጥ ዘር ተጠቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ ቢሆንም ከፍላጎት አንጻር የሚመረተው ዘር በቂ አይደለም። ለዚህም የመነሻ ዘር አቅርቦት፣ የመሬት አቅርቦት ችግር፣ የአገር ውስጥ አምራቾች አመለካከት፣ ተጠቃሚው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት የመቀበል ችግር፣ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በተገቢው ሁኔታ የማስተዋወቅ ችግር ተጠቃሽ ናቸው።

በክልል የሚገኙ የዘር ጥራት ቁጥጥር ማዕከላት በአዲስ የተቋቋሙትን ጨምሮ 20 ሲሆኑ፤ የቁጥጥር ሥራውን እንዲያሳልጡ ከየክልሉ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ ብለዋል።

# ኢትዮ ቴሌኮም 181 ከተሞችን የ4ጂ ኤልቲኢ አገልግሎት ተጠቃሚ አደረገ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም 181 ያህል የኢትዮጵያ ከተሞችን የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረጉን አስታወቀ፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በሦስተኛው ዙር የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በያዘው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መሠረት እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህም በ67 ከተሞች አዲስ የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ አገልግሎት እንዲሁም በ27 ከተሞች ተጨማሪ የማስፋፊያ ሥራዎችን በማከናወን አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም በተለይም በቴሌኮም ማዕከላዊ ምሥራቅ ሪጂን በስድስት ከተሞች፣ በማዕከላዊ ሰሜን ሪጂን በ13 ከተሞች፣ በምሥራቅ ምሥራቅ ሪጂን ሰባት ከተሞች፣ በምሥራቅ ሪጂን በስምንት ከተሞች የማስፋፊያ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡

በተመሳሳይ በሰሜን ምሥራቅ ምሥራቅ ሪጂን በ16 ከተሞች፣ በሰሜን ምሥራቅ ሪጂን በ18 ከተሞች፣ በሰሜን ሰሜን ምዕራብ ሪጂን በዘጠኝ ከተሞች እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ሪጂን 16 ከተሞች እና በደቡብ ምዕራብ አዲስ አበባ ከፍተኛ የዳታ አጠቃቀም በሚታይባቸው 67 ከተሞች የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ አገልግሎትን ማሰጀመሩን በመግለጫው አትቷል፡፡

አዲስ የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ አገልግሎት የተጀመረባቸው ከተሞች በማዕከላዊ ምሥራቅ ሪጅን ባቢሌ፣ ባቲ እና ጉርሱም፤ በምሥራቅ ምሥራቅ ሪጅን ጭናክሰን፣ ደገሃቡር፣ ሀርገሌ፤ ምሥራቅ ሪጅን በዴሳ፣ ደደር፣ ገለምሶ ቁልቢና ሚኤሶ እንዲሁም በሰሜን ምሥራቅ ሪጅን አከስታ፣ ባቲ፣ ጨፋ ሮቢት፣ አረርቲና ጫጫ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ከተሞች መሆናቸው ተገልጿል፡፡

በሌላ በኩል በሐረር፣ ጅግጅጋ፣ ቶጎጫሌ፣ ድሬዳዋ፣ ደብረብርሃን፣ ፍቼ፣ ገርበጉራቻ እና ሰንዳፋን ጨምሮ በሌሎች በ27 ከተሞች የማስፋፊያ ሥራዎች ማጠናቀቁን አሳውቋል፡፡

በዚህም መሠረት ኢትዮ ቴሌኮም በአሁኑ ወቅት ጠቅላላ የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ አገልግሎት ተጠቃሚ የአገሪቱን ከተሞችን ብዛት ወደ 181 ማድረስ የቻለ ሲሆን፣ በቀጣይም ከፍተኛ የዳታ አጠቃቀም በሚታይባቸው ሌሎች የአገሪቱ ከተሞች የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት አዲስ እና ተጨማሪ የማስፋፊያ ሥራዎችን በማከናወን አገልግሎቱን የሚያስጀምር መሆኑን አብራርቷል፡፡

የ4ጂ ኤል.ቲ.ኢ. አገልግሎት የላቀ ፍጥነትና ባንድዊድዝ እንዲሁም አስተማማኝ የዳታ አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ የኢትዮ ቴሌኮም ደንበኞች አገልግሎታቸውን ዲጂታይዝ ለማድረግ፣ ምርታማነታቸውን ለመጨመር እና በአጠቃላይ የቴሌኮም አገልግሎት ላይ ያላቸውን ተሞክሮ በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ ያስችላቸዋል ተብሏል።

# ኤጀንሲው የትራፊክ አደጋን ለመከላከል ከመገናኛ ብዙኃን ጋር በትብብር እየሠራ ነው

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በየጊዜው እየተባባሰ የመጣውን የትራፊክ አደጋ ለመከላከል ከመገናኛ ብዙኃን ጋር በመተባበር ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ እንደሚሠራ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በመንገድ ደህንነት ላይ ፕሮግራም ከሚያዘጋጁ እና ከሚድያ ባለሙያዎች ጋር የፓናል ውይይት አድርጓል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አማካሪ አቶ አለምሰገድ ዘውዴ የብዙኃን መገናኛዎች የመንገድ ደህንነት ዙሪያ ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎችን በመሥራት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ የመንገድ ደህንነት መረጃ ባለሙያ ወይዘሮ ሜሮን ጌታቸው በበኩላቸው የመንገድ ደህንነት ጋር የተያያዙ ዳታዎችን አቅርበዋል። በ2014 ዓ.ም በትራፊክ አደጋ 441 ሞት መመዝገቡን ጠቁመዋል። ከ2013 ዓመት አንጻር የተከሰተው የሞት መጠን የጨመረ ሲሆን፣ በየጊዜው በሚከሰተው የትራፊክ አደጋዎች የሚሞተው የሰው ቁጥር እየጨመረ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በ2014 ዓ.ም በትራፊክ አደጋ ለሞት የተዳረጉት በጾታ ደረጃ 78 በመቶ ወንዶች ሲሆኑ 22 በመቶ ሴቶች መሆናቸውንም ገልጸዋል። በዕድሜ ደረጃም ከ20 እስከ 39 ዓመት የዕድሜ ክልል የሚገኘው አምራች የኅብረተሰብ ክፍል ይበልጥ በትራፊክ አደጋ ለሞት የተጋለጠበት እንደሆነ የጠቀሱት ወይዘሮ ሜሮን፤ በሳምንቱ ቀናት ደረጃ በ2014 ዓ.ም ቅዳሜ ቀን ከሌሎች ቀናት ከፍተኛ



አቶ አለምሰገድ ዘውዴ

የሞት አደጋ የተስተናገደበት መሆኑንም ጠቁመዋል።

የመንገድ ደህንነት ባለሙያና የአውቶ ሴፍቲ ፕሮግራም አዘጋጅ ኢንስፔክተር አሰፋ መዝገቡ በበኩላቸው፣ አደጋ መከላከል ብቻ ሳይሆን የትራፊክ ፍሰቱን ማሳለጥ የትራፊክ ማኔጅመንት አንዱ ሥራው መሆኑን ገልጸዋል። እግረኛ የሚያቋርጥባቸው መንገዶች በ30 ብቻ መሄድ እንደሚገባ ቢቀመጥም ተገቢው የእግረኛ ማቋረጫዎች ባለመኖራቸው የተነሳ በሁሉም አካባቢዎች የሚያቋረጥ መሆኑ ችግሩን ያወሳስበዋል ብለዋል።

እግረኛ እንዳያቋርጥባቸው ከታጠሩት የፍጥነት መንገዶች ውጪ ሁሉም የከተማዋ መንገዶች እግረኛ የሚያቋርጥባቸው መሆኑን አመላክተው፣ ነገር ግን ትምህርት ቤቶች፣ የገበያ ስፍራዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት አካባቢዎች ላይ በይበልጥ በ30 መታሰብ እንደሚገባው ጠቁመዋል። በተጨማሪም የመንገዱ አቀማመጥ ቁልቁለታማ ከሆነ ፍጥነት ሊወሰን ይገባል ብለዋል።

እንደ ኢንስፔክተር አሰፋ መዝገቡ ማብራሪያ የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ዋና ተግባር የተሠራውን መንገድ ማስተዳደር እና ፍሰቱን ማሳለጥ ሲሆን፣ እንደአገሪቱ የበጀት ሁኔታ መንገዶች እንዲሠሩ የሚያደርገው ደግሞ የመንገዶች ባለሥልጣን ነው።

በተለያዩ ዝግጅቶች መንገዶች ሲዘጉ፣ እንደ ውሃና ፍሳሽ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን የመሳሰሉ ድርጅቶች መንገድ ሲቆፍሩ ተመልሶ ስለመሥራቱ አዲት መደረግ እንደሚገባቸውም አመላክተዋል። እግረኞችም በተሠራው መንገድ በአግባቡ የመጠቀም ሕግ የወጣ ቢሆንም ተግባራዊ አለመሆኑን አስታውሰዋል።

የእግረኛ ማቋረጫዎች ባሉባቸው መንገዶች በአግባቡ የማይጠቀሙ እግረኞች ተጠያቂ የሚሆኑበት እና የእግረኛ ማቋረጫ ባልተመቻቸባቸው አካባቢዎች ደግሞ ማመቻቸት የሚገባ መሆኑንም ተናግረዋል።

# የሰላም ስምምነቱ ለቀጣይ ሕይወታቸው ተስፋ እንዲሰንቁ እንዳደረጋቸው የራያ ባላ ወረዳ ነዋሪዎች ተናገሩ

**ሞገስ ጸጋዬ**


አቶ መንገሻ አዲሴ


አቶ ምስጋን ትኬ


አቶ ሞገስ ብርሃኑ


ወይዘሮ ዘይባ አብርሃ

ራያ ባላ፡- እንደ አገር ሰላም እንዲመጣና ቀጣይ ሕይወታቸው የተሻለ እንዲሆን መንግሥት ከሕወሓት ጋር ያደረገው የሰላም ስምምነት ከተስፋ መቁረጥ ወጥተው ተስፋ እንዲሰንቁ እንዳደረጋቸው የራያ ባላ ወረዳ ነዋሪዎች ተናገሩ።

የራያ ባላ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሞገስ ብርሃኑ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ መንግሥት ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት የሚደነቅ በመሆኑ ስምምነቱ ፍሬ እንዲያፈራ ሰላም ወዳዱ ኅብረተሰብ ሁሉ ሊደግፈው ይገባል።

ረዘም ላለ ጊዜ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነበርን፣ ይሁንና የሰላሙን ስምምነት ስንሰማ ተስፋ እንድንሰንቅ አድርጎናል ያሉት ያጋገርናቸው የከተማዋ ነዋሪዎች፤ ኅብረተሰቡ ሰላም እንዳይኖር የሚሠሩ ኃይሎችን በመጠቆም ከመንግሥት ጐን ሊቆምና ስምምነቱን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል። በጦርነት ጉዳት ቢደርስብንም፣ የሰው ሕይወት ቢጠፋና ሀብት ንብረት ቢወድምም መካሻው ሰላም በመሆኑ ለዘላቂ ሰላም ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሚዲያዎች ኅብረተሰቡን በማንቃት ረገድ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው ያሉት አስተያየት ሰጪው፣ ስለ እርቁ ጠቀሜታ ለሕዝቡ ማስረዳት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

አንዳንድ ኃይሎች እርቁ እንደፈረሰ አድርገው በማስወራት ኅብረተሰቡ ያገኘውን የሰላም ተስፋ እንዳያጣጥም እያደረጉ ነው ያሉት ነዋሪዎቹ፤ የጠራ መረጃን ለኅብረተሰቡ በማድረስ የተሳሳተውን አመለካከት ማስተካከል እንደሚገባ አስረድተዋል።

ነዋሪዎቹ እንዳሉት፤ ላለፉት ሁለት አመታት አንድም መሠረተ ልማት እየለማ አልነበረም፣ በአንጻሩ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ወድመዋል። ስለሆነም ኅብረተሰብ እርቁን ሊደግፍ ይገባል።

በአሁን ጊዜ ራያ ባላ ወረዳ ሰላም በመሆኑ ኅብረተሰቡ ተደስቷል ያሉት ነዋሪዎቹ፣ በተለይ ድርድሩ ከፍተኛ ደስታን ፈጥሯል ብለዋል። «ሰው ሆኖ ሰው እንዲሞት የሚፈልግ የለም፣ ሁሉም ሰው ሰላም እንዲመጣ ፍላጐት አለው» በድርድሩ ተደስተናል። የራያ ሕዝብ በጦርነት በጣም ተሰላችቷል፣ የሰላም አየርን መተንፈስ፣ አርሶ መብላት ናፍቆታል ሲሉም ተናግረዋል።

በራያ ባላ ወረዳ የማሩ ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ አቶ መንገሻ አዲሴ እንደሚሉት፤ መንግሥት እንደ አገር ሰላም ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው። ኅብረተሰቡም ይህን በመረዳት ከመንግሥት ጐን መቆም አለበት። በጦርነት ወቅት በርካታ ነዋሪዎች ሕይወታቸውን ያጡ ቢሆንም የጦርነትን አስከፊነት ሁላችንም ስለምንረዳው የሰላም ስምምነቱን የራያ ባላ ሕዝቦች እንደግፈዋለን። መንግሥት የያዘው የሰላም ድርድር አማራጭ የለውም። ሕዝቡ አጥብቆ ሊደግፈው ይገባል፡፡

ለዘላቂ ልማታችን ሰላም አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ መንገሻ፣ የራያ ባላ ወረዳ ሕዝብ ሰላምን አጥብቆ ይፈልገዋል። ሁሉም ተጐድቷል፣ ዘመድ ሞቶበታል፣ አዝምሮ መብላት እንዳይችል ሆኗል፣ ይሁንና መሰል ችግር ዳግም እንዳይከሰት ለመከላከል የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን ብለዋል።

ሰላም ለሰው ልጅ ቁልፍ ነው የምትለው የወረዳው ነዋሪ ወይዘሮ ዘይባ አብርሃ በበኩሏ፣ የራያ ባላ ሕዝብ የሰላም ጥማት አለብን፣ መንግሥት የጀመረውን የሰላም ሂደት እንደግፋለን። በአንድ አገር ይህ ሁሉ ሰላም ታጥቶና ንብረት ወድሞ ለሰላም እጁን የማይዘረጋ አካል ሊኖር አይገባም ብላለች፡፡

እንዴት መኖር እንዳለብን ተስፋ ቆርጠን ነበር የምትለው ወይዘሮ ዘይባ፣ የሰላም ድርድሩን ስንሰማ ተስፋ ሰንቀናል። ሕይወትን በአዲስ ለመኖር ዝግጅት እያደረግን ነው ብላለች።

ሰላሙ በፍጥነት እንዲመጣ መደማመጥና መሪዎችን መስማት አስፈላጊ ነው ያለችው ወይዘሮ ዘይባ፤ የአማራና የትግራይ ሕዝብ ተዋልዶና አብሮ የሚኖር በመሆኑ መለየት አይቻልም፣ የሰላም አየር መንፈሱ ሁሉንም አስደስቷል ስትል ገልጻለች።

የራያ ባላ ወረዳ ነዋሪ አቶ ምስጋን ትኬ በበኩላቸው፣ የሰላሙ ድርድር ሊደገፍ ይገባዋል። በጦርነቱ በወረዳው የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ወድመዋል። ሰላም መምጣቱን ሕዝብ ይፈልጋል፣ የሀሰት ወሬ የሚነዙ አካላትን መንግሥት አደብ ማስገዛት አለበት። እንዲሁም የወደመው የጤና፣ የትምህርት ቤት፣ የመብራትና መሰል ማህበራዊ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ መግባት የሚችለው ሰላም ሲመጣ በመሆኑ ከመንግሥት ጐን ነን ብለዋል።

# በአዲስ አበባ እስከ ኅዳር መጨረሻ ድረስ 80 በመቶ መጽሐፍ ይሰራጫል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ ስርጭት እስከ 80 በመቶ የሚሆነው እስከ ኅዳር መጨረሻ ድረስ እንደሚከናወን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የመጽሐፍት ስርጭትና ህትመት እንዲሁም ዝግጅት ለክልሎች የተሰጠ ኃላፊነት በመሆኑ እንደ ከተማ አስተዳደር የመጽሐፍ ዝግጅቱ በራስ አቅም ተሠርቶ እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ከከተማ አስተዳደር አልፎ እንደአገር ለመሥራት ያስቻለ ነው፡፡ ምክንያቱም ከወጪ ቅነሳው ባሻገር ከኦሮሚያና ከአማራ ክልል በስተቀር ብዙዎቹ ክልሎች የበጀት እጥረት ስላለባቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጀውን መጽሐፍ ወስደው እንዲጠቀሙ ተደርጓል ብለዋል፡፡

የመጽሐፍ ዝግጅት ሥራው ለመምህራን ልምድና አቅም የፈጠረ እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር ዘላለም፤ ህትመቱን በተመለከተ ግልጽ ጨረታ በማውጣት ለስድስት አሳታሚ ድርጅቶች ተሰጥቷል ብለዋል፡፡

«አምስቱ አሳታሚዎች የመጽሐፍቱን ህትመት አጠናቀው በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ ያሉት አቶ ዘላለም፤ አስቸጋሪ የሆነው የአንድ አሳታሚ ድርጅት ህትመት ነው ብለዋል፡፡ ይህ የተፈጠረውም አሳታሚ ድርጅቱ በጥሬ ዕቃ ችግር ምክንያት ውጪ ወስዶ በማሳተሙ እንደሆነና ይህም ቢሆን ህትመቱ መጠናቀቁን ጨምረው ገልጸዋል፡፡ እስካሁን ያዘገየውም የማጓጓዙ ሥራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

እስከ ኅዳር 30 ድረስ 80 በመቶ የሚሆነውን የመጽሐፍ ስርጭት እናደርጋለን ያሉት ኃላፊው፤ በከተማ አስተዳደሩ 3 ነጥብ 9 ሚሊዮን መጽሐፍት በኮፒ የተዘጋጀ ሲሆን፤ እስከ አሁን ድረስ ወደ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚደርስ ኮፒ መሰራጨቱን ተናግረዋል፡፡ መጽሐፉ ያልደረሳቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሶፍት ኮፒ እንዲያገኙ በማድረግ ትምህርት እየተከናወነ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

‹‹ሥርዓተ ትምህርት ሁሌ ለትችት ቅርብ ነው፡፡ ሁሌ ይሻሻላል፤ ሁሌ አዳዲስ ነገሮች ይጨመርበታል፡፡ ስለዚህም ዘመኑን፣ ወቅቱንና አካባቢውን ለመዋጀት ሲባል ነገሮችን በአንዴ ወስኖ ወደትግበራው ለመግባት ፈታኝ ነው ሲሉም ዶክተር ዘላለም ተናግረዋል፡፡


ዶክተር ዘላለም ሙላቱ

መጽሐፍት ሁሌ ሀርድ ኮፒ መሆን አለበት ብለን አናስብም ያሉት ኃላፊው፤ ሥርዓተ ትምህርት በሰዓት፣ በቀናትና በወራት እንዲሁም በዓመታት ለውጦች የሚታይባቸው ናቸውና ለውጡን ተከትሎ መተግበር ግድ ነው ብለዋል፡፡ ስለዚህም አማራጮችን እያዩ መጠቀም እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዘላለም ገለጻ፤ የመጽሐፍት ህትመቱ እንደአገር የሚሠራ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁሉንም የሚያስተናግድ የህትመት ተቋም የለም፡፡ ስለሆነም እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀድሞ በመሠራቱና ውል በመያዙ ተከናወነ እንጂ ይህ ሁሉም ጋር ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ ይህንን ተገንዝቦ መታገስ ይኖርበታል፡፡

ዶክተር ዘላለም አክለውም በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት የስድስተኛና ስምንተኛ ክፍል ፈተና ይሰጣል። ነገር ግን መጽሐፉ ባለመድረሱና አማራጮች ባለመስፋታቸው የተነሳ ፈተናውን ክልሎች በእኩል ደረጃ ማከናወን አይችሉም፡፡ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይህ ያጋጥማል የሚል ስጋት የለም፡፡ ትምህርት ሲጀመር ጀምሮ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው ብለዋል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ቅዳሜን ለተጨማሪ ትምህርት የማዋል ሥራ እየተሠራ እንደሆነና መጽሐፍቱ ሙሉ ለሙሉ ሲደርስ ትምህርቱን በሚገባ ተረድተው ለፈተና ዝግጁ እንዲሆኑ ሙሉ ቀን የሚማሩበት መንገድም ይመቻቻል፤ ከተቻለም እሁድንም ለትምህርት ለመጠቀም እቅድ ተይዟል ብለዋል፡፡

# ኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ከምትልከው የኤሌክትሪክ ኃይል በዓመት ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ታገኛለች

**ቴዎድሮስ ካሣ**

ወላይታ ሶዶ፡- ኢትዮጵያ በየዓመቱ እስከ 200 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ኬንያ በመላክ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደምታገኝ ተገለጸ።

የኢትዮ ኬንያ ፕሮጀክት የሳይት ሥራ አስኪያጅ አቶ ቴዎድሮስ አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት (ኢፕድ) እንደገለጹት፣ ይህ ፕሮጀክት አገራችን ያለባትን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንደሚፈታ ከፍተኛ ተስፋ ከሚጣልባቸው ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ይሆናል።

በመሆኑም በሁለቱ አገራት መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት በዓመት እስከ 200 ሜጋዋት ኃይል ወደ ኬንያ በመላክ ለሚቀጥሉት ሦስት አመታት በየአመቱ ከ 100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ከሦስት ዓመታት በኋላ ደግሞ ከ400 ሜጋ ዋት በላይ የኃይል አቅርቦት የሚላክ ሲሆን፣ ገቢው ደግሞ በእጥፍ ይጨምራል ሲሉ አክለዋል።

በአሁኑ ወቅት የሙከራ የኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፣ የሙከራ ስርጭቱ ገቢ እያስገኘ ለአንድ ወር ያህል ከቀጠለ በኋላ ወደ መደበኛ አገልግሎቱ ይገባል ተብሏል።

ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ ከወላይታ ሶዶ ከተማ ወጣ ብሎ የተገነባው የወላይታ ሶዶ ኮንቨርተር ስቴሽን የኤሌክትሪክ ኃይል ከኢትዮጵያ ወደ ኬንያ እየተመጠነ የሚላክበት ማዕከል የሙከራ ኃይል የመላክ ሥራ ከጀመረ ከአንድ ሳምንት በላይ ተቆጥረዋል።

የኢትዮ ኬንያ ፕሮጀክት ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ የተገነባ ሲሆን፣ ፕሮጀክቱ በዓለም ባንክ እና በአፍሪካ ልማት ባንክ በተደረገ የገንዘብ ድጋፍ የተከናወነ ነው ብለዋል።

የወላይታ ሶዶ የኮንቨርተር ስቴሽን የኦፕሬሽን ክፍል ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ግርማ በበኩላቸው፤ ይህ ፕሮጀክት በቀጣይ ከኬንያ ባሻገር የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ እና ሌሎችም የጎረቤት አገራት የሚተላለፍበት መስመር በመሆኑ ለአገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አበርክቶ እንዳለው አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር ነሐሴ 2014 ዓ.ም የኃይል ሽያጭ ስምምነት እንደተፈራረመች ከተቋሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በስምምነቱ መሠረት ኢትዮጵያ አንድ ኪሎ ዋት ሰዓት የኤሌክትሪክ ኃይል በ6 ነጥብ 5 የአሜሪካ ሳንቲም ትሸጣለች።



ከሦስት ዓመታት በኋላ በተቋሙ ጠያቂነት አሁን በተደረሰው የታሪፍ ዋጋ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ ድርድር እንደሚኖር ስምምነቱ ይገልፃል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የትራንስሚሽንና ሰብስቴሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራ አስፈጻሚ አቶ ክብሮም ካህሳይ ኢትዮጵያ ከኤሌክትሪክ ሽያጭ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት እና ከጎረቤት አገራት ጋር ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ፕሮጀክቱን ለጎበኙ ጋዜጠኞች ገልጸዋል።

ይህ ፕሮጀክት ኢትዮጵያ እስከ ሁለት ሺህ ሜጋ ዋት የሚደርስ ኃይል እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ እንድትልክ ያስችላታል።

በዚህ ፕሮጀክት በዓመት ሁለት ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል የመላክ የመጨረሻ ዓላማ ሲሳካ አገሪቱ በዓመት እስከ 1 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ታገኛለች።

የኢትዮ- ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የማስተላለፊያ መስመር የግንባታ ሥራ ሲኢቲ (CET) በተሰኘ የቻይና ኩባንያ የተከናወነ ሲሆን የኮንቨርተር ማከፋፈያ ጣቢያውና የግራውንድ ኤሌክትሮድ መስመሩ ደግሞ ሲመንስ በተሰኘ የጀርመን ኩባንያ ተከናውኗል፡፡

በኢትዮጵያ በኩል የማስተላለፊያ መስመሩ የፕሮቴክሽንና የዳታ ማስተላለፊያ የኮሙዩኒኬሽን መስመሩ 440 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን፣ 994 የከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ የብረት ታወሮች አሉት።

# በአለርት ሆስፒታል ለታማሚዎች መንፈሳዊ ሕክምና ተሰጠ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የተለያዩ የእምነት አባቶች በአለርት ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በመገኘት ለህሙማን መንፈሳዊ ሕክምና ሰጥተዋል፡፡

ዘንድሮ ለአምስተኛ ጊዜ በተካሄደው በዚሁ የጥየቃ መርሃግብር ላይ የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ሽመልስ ገዛኸኝ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ለታማሚዎች የተሰጠው የመንፈሳዊ ሕክምና፤ በሆስፒታሉ የሕክምና አገልግሎት በማግኘት ላይ ላሉ ሰዎች ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል ብለዋል፡፡

ሀኪሞች የስጋ ሕክምናን ሲሰጡ የሃይማኖት አባቶችም በስፍራው በመገኘት በመፀለይና ታማሚዎችን ፈጣሪ ይማራችሁ በማለት እንዲሁም ተስፋ በመስጠት የፈውስ ሕክምናን መስጠታቸው ትልቅ ነገር በመሆኑ ዶክተር ሽመልስ ለሃይማኖት አባቶች ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

አለርት ቤታችሁ ነው ከውጭ ሆናችሁ ሳይሆን ከውስጥ ሆናችው አብራችሁን በመሥራት ደግ ስንሰራ ልታመሰግኑ፣ ስናጠፋ ልትወቅሱን ይገባል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ፕሬዚዳንት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን በሆስፒታሉ በመገኘት ታማሚዎችን የጠቁዩና ያፅናኑ ሲሆን፣ አለርት ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከሌሎች የሕክምና ተቋማት አንጋፋና ትልቅ እንደሆነ በመጠቆም የታመመን መጠየቅ ግዴታ እንደሆነ እና ከፈጣሪ ዘንድም እንደታዘዘ ገልፀዋል፡፡

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ እንደገለጹት፤ አለርት ኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በየወቅቱ እየተሻሻለ የመጣ የሕክምና መስጫ ተቋም ሲሆን ከስጋደዌ ሕክምናነቱ ባሻገር በዓይን፣ በጥርስና በቆዳ ሕክምና ላይም ኅብረተረሰቡን በማገልገል ላይ የሚገኝ እንዲሁም በሚሊዮኖች ለሚቆጠር የኅብረተሰብ ክፍል አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ግዙፍ ተቋም ነው፡፡

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ አለርት ሆስፒታል ተገኝተው ለህሙማን መንፈሳዊ ሕክምና መስጠት ደስተኛ የሚያደርግና እነሱን አለመጠየቅም በፈጣሪም የሚያስጠይቅ መሆኑንም ጭምር ገልጸው፤ ለታካሚዎች ብቻ ሳይሆን ለአካሚ ሀኪሞችም ጭምር ጸሎት የሚያደርግና ሥራቸውንም በስኬት እንዲያጠናቅቁ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

የደብረ ቢታኒያ አቡነ ተክለሃይማኖትና ቅድስት ልደታ ለማርያም ተወካይ የሆኑት ቀሲስ ለይኩን ብርሃን በበኩላቸው በሆስፒታሉ ተገኝተው የመንፈሳዊ ሕክምና መስጠቱ አካል በመሆናቸው ደስተኛ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ሕክምናውም ታማሚዎችን የሚያበረታና ተስፋ የሚሰጥ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

ሆስፒታሉ ለታካሚዎች መንፈሳዊ ሕክምናን ማዘጋጀት ከጀመረ 5ተኛ አመቱን የያዘ ሲሆን፣ በየአመቱ የአካባቢው ማኅበረሰብና የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት አባቶች በጋራ በመሆን የተለያዩ ተኝቶ ሕክምና ክፍሎች በመሄድ ሕሙማንን በመጠየቅና ባለሙያዎችን በማበረታታት መንፈሳዊ ሕክምናቸውን ያበረክታሉ፡፡

# «የፕሪቶሪያው ስምምነት ቅድመ ሁኔታ የለውም፤ ስለሆነም በስምምነቱ መሠረት ይፈፀማል»

**- ለገሰ ቱሉ (ዶክተር)**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ እንደሌለውና በስምምነቱ መሠረት እንደሚፈፀም የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ገለፁ።

ሚኒስትሩ ዶክተር ለገሰ ቱሉ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፣ «ፍላጎቶችን ማጣጣም የዴሞክራሲ መርህ ነው» ብለዋል።

ለሕዝብና ለሕብረ ብሔራዊ አንድነት ሲባል በየዕለቱ መንግሥት መስዋዕትነት እየከፈለ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሩ፤ «እያንዳንዱ ሰው እንደሚመኘው ሰላምንና ብልፅግናን ማስፈን የመንግሥታችን ተቀዳሚ ዓላማ ነው» ብለዋል፡፡ «ሰላምን የምናሰፍነው በመርህ እና በሕግ ነው» ሲሉም አክለዋል።

የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ለሰሜኑ የአገራችን ክፍል መሠረት መጣሉን የገለጹት ዶክተር ለገሰ፤ የናይሮቢው ደግሞ የማስፈጸሚያ መሠረት ማስቀመጡን አመልክተዋል።

ዶክተር ለገሰ እንደገለጹት፤ ያለን ብቸኛው አማራጭ ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ነው። ሁሉንም አሸናፊ ለሚያደርገው መርህ ሁሉም አካል የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡

## ከሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተሳትፎ አድንቀው፣ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል፡፡

ተፈናቅለው የነበሩ ዜጎችን ወደ ቀያቸው በመመለስ በዘላቂነት ለማቋቋም መንግሥት አስተባባሪ ኮሚቴ አደራጅቶ እየሠራ መሆኑን የተናገሩት አምባሳደር ሽፈራው፤ መደበኛ አገልግሎቶችን ከማስጀመር ጎን ለጎን ዜጎች ወደ መደበኛ ሕይወታቸው እስከሚመለሱ ሰብዓዊ ድጋፉን አጠናክሮ ለመቀጠል በቂ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል፡፡

መንግሥት ሀብት ከማሰባሰብ ባለፈ የእርዳታ ድርጅቶችን አቅም ለመጠቀም እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መንግሥት በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች ለመደገፍ እያደረገ ያለውን ጥረት እንዲያግዙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## አገራዊ ለውጡ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሚስቡ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት የዳኝነት ሥርዓቱ እንዲሻሻል አድርጓል።

በማንኛውም ፍርድ ቤት ጠበቃ፣ የሕግ አማካሪና ተመራማሪ አቶ አሰግድ ጥላሁን እንደገለጹት፣ ከአገራዊ ለውጡ በፊት በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ ውስጣዊና ውጫዊ ጣልቃ ገብነት ከአስፈፃሚው አካል ብቻ ሳይሆን ከፍርድ ቤት አስተዳደሮችም በስፋት ይስተዋል ነበር።

በተለይ የፖለቲካ ይዘት ያላቸው የወንጀልና የመንግሥት አስተዳደር አካላት ተከራካሪ ሆነው በሚቀርቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ አስፈፃሚው አካል ተገቢ ያልሆነ ተፅዕኖ ያሳድር እንደነበር ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት በፍርድ ቤት አሠራር ላይ ማሻሻያ መደረጉ ጣልቃ ገብነቱን እንደቀነሰው ተናግረዋል።

የፖለቲካ ይዘት ያላቸው የወንጀል እና የወንጀል ጊዜ ቀጠሮ ጉዳዮችን የሚያዩ ችሎቶች ላይ የተመደቡ ዳኞች ከማንኛውም ፍርሃትና ስጋት ነፃ ሆነው ሥራቸውን በነፃነት እንዲሠሩ የሚያረጋግጥ ዋስትና መሰጠቱ እንዲሁም ከለውጡ በኋላ የተደረጉ የሕግ ማሻሻያዎች እና የዳኞች የውክልና ቁጥር ከቀድሞው ከፍ ያለ መሆኑ መሻሻሎች እንዲመጡ አድርጓል።

በጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ መመደቡ፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር፣ ደመወዝና ማስተዳደር በራሱ እንዲያስተዳድር መደንገጉ እና የዳኝነት ሥርዓቱን ነፃነት የሚጋፋና ተፅእኖ ሊፈጥር የሚሞክር ማንኛውም አካል ላይ ቅጣት እንዲጣል መደረጉ ለዳኞች ሥርዓት መሻሻል ድርሻው የጎላ ነው ብለዋል።

የተሻሻለው የፌዴራል ዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ከመጀመሪያው አዋጅ የበለጠ መስፈርቶችን በዝርዝር ማስቀመጡ እና በየደረጃው የሚሾሙ ዳኞችን ለመለየት የበለጠ ግልፅ አድርጓል ሲሉም ተናግረዋል።



አቶ አሰግድ ጥላሁን



ዶክተር ወንድምአገኝ ታደሰ



ዶክተር ደምመላሽ ካሳዬ

ምንም እንኳን የአስፈፃሚው አካል ጣልቃ ገብነት መሻሻል ቢያሳይም የዳኝነት አካሉ በክርክር ሂደት ውስጥ የሚሰጣቸውን ትዕዛዛትና ውሳኔዎች በአግባቡ ማስከበርና ማስፈጸም ላይ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉም አቶ አሰግድ ጠቁመዋል።

በቀጣይም የፍትህ ሥርዓቱ የበለጠ እንዲጠናከርና ለኅብረተሰቡ ተገቢውን ፍትህ እንዲሰጥ ትዕዛዝና ውሳኔን ማስከበር፣ ሹመቶች አዋጅና መመሪያዎችን ጠብቀው በግልፅ እንዲከናወኑ ማድረግ፣ ለእድገትና ዝውውር ግልጽ አሠራር መዘርጋት እንዲሁም ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግና አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ወንድምአገኝ ታደሰ በበኩላቸው የፍትህ ሥርዓቱ ላይ የመጡትን ለውጦች እና መሻሻሎች ለሰላም፣ ለልማት፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ለእኩልነት፣ ለፈጠራ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት እንዲሆኑ በአተገባበር ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

በተለይም የፍትህ ጉዳይ የፖሊሲ፣ የጠበቃ፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም የዳኞች ብቻ ሳይሆን የሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል መሆኑን የሚያስገነዝቡ እና በፍትህ ሥርዓቱ ላይ የባህል ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች ላይ ማተኮር ይገባል ብለዋል።

የፍትህ መዘግየትን ለማስቀረት፣ ትጋት ለመጨመር እና የአቅም ማነስ ጉዳዮች ለመቅረፍ ከሚሠሩ ሥራዎች በተጓዳኝ የፍርድ ቤት ትዕዛዝና መጥሪያ ለማድረስ እንዲሁም ሙስናን ለመዋጋት የሚደረገው ጥረት በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መታገዝ እንዳለበት አመልክተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ወርክ ትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ደምመላሽ ካሳዬ እንደተናገሩት፣ በአገራዊ ለውጡ የመጡትን የፍትህ ሥርዓት መሻሻሎች የበለጠ ለማጠናከር ተከታታይ የሆኑ እና ሁሉን አቀፍ ስልጠናዎችን መስጠት ያስፈልጋል።

በተለይም የፍትህ ሥርዓቱ ፈጣን፣ ተዓማኒነት ያለው፣ ለሁሉም ተደራሽ የሆነ እንዲሆን የፖሊስ አቅም ላይ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተገቢ ነው።

ይህም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዘው የሚፈጸሙ የረቀቁና ውስብስብ ወንጀሎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመከላከልና ወንጀለኞችን ወደ ሕግ ለማቅረብ ያስችላል ሲሉ አብራርተዋል።

## ዘላቂ ሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለልማት ይውል የነበረን ሀብት በመብላት በዜጎች ላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ይፈጥራል፡፡

ሰላምን የሚቃወሙ ሰዎች ጦርነት ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ሁለንተናዊ ቀውሶች ያላገናዘቡና ጤነኛ አእምሮ የሌላቸው ናቸው የሚሉት ዶክተር ሳሙኤል፤ እነዚህ ሰዎች ወደአእምሮአቸው ተመልሰው ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ሰላም ሊያስቡ ይገባል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው ስምምነት እንደ አገር ሰላም ያሰፍናል የሚል ተስፋ እንደተጣለበት የሚጠቅሱት ዶክተር ሳሙኤል፤ ይህንን ስምምነት የሚቃወሙ አካላት አንድም ከዚህ በፊት ሲደረጉ የነበሩ ሰላማዊ ውይይቶች ፍሬ ባለማፍራታቸው በዚህ ስምምነትም የሕወሓትን ቁርጠኝነት ከመጠራጠር የመነጨ ሊሆን ይችላል፤ አልያም ግጭትን ለጦርነት ለመጠቀም በመፈለግ ሰላም እንዳይመጣ ካላቸው ጽኑ ፍላጎት ሊሆን ይችላል ይላሉ፡፡

ከዚህ ባለፈ ግን በዓለም ላይ ያሉ ኃያላን አገራት ኃይላቸውን አስጠብቀው ለመቀጠል የሚያደርጉት ፉክክር መኖሩን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ የምትገኝበት ቀጣና አለመረጋጋት ቀዳሚነታቸውን የሚያስጠብቅላቸው ከመሰላቸው ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ኢትዮጵያ ውስጥ ትርምስ እንዲኖር የሚፈልጉ ኃይሎች ሊኖሩ እንደሚችሉም ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ ለእነሱ የሚታዘዝና ለእሳቤያቸው ተቀራራቢ አመለካከት ያለው ኃይል ስልጣን ላይ እንዲቀመጥ የመፈለግ አዝማሚያዎች እንደሚስተዋሉም ይጠቁማሉ፡፡

ለሁሉም ግን መፍትሔ የሚሆነው ስምምነቱ ወደ ተግባር ተለውጦ ዘላቂ ሰላም ሲሰፍን ነው የሚሉት ዶክተር ሳሙኤል፤ መላው ኢትዮጵያውያን እውቀት ያላቸው በእውቀታቸው በማገዝ ስምምነቱ ወደ መሬት ወርዶ እንዲተገበርና የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን እንደሚገባ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ፡፡

እንደ ምሁራኑ ገለጻ፤ አሁን የተደረሰው የሰላም ስምምነት ለሁሉም የሰላም ወዳድ ዜጋ እና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው ፋይዳ ትልቅ ነው፡፡ በአንጻሩ ይህ የሰላም ስምምነት ወደመሬት መውረድ ካልቻለ የሚከሰተው ችግር ከመቼውም ጊዜ የከፋ መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ለሰላሙ ስምምነት ተግባራዊነት በቁርጠኝነት መሥራት አማራጭ የሌለው የሁለም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሙስናን መንቀል ፍትሃዊነትን ማንገስና የሕዝብን ርካታ ማረጋገጥ ነው!

ከመንግሥት መዋቅር ከሚጠበቁ ጉዳዮች መካከል አንዱና ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፈው ጉዳይ ለዜጎች ተገቢውን መንግሥታዊ አገልግሎት መስጠት ነው:: ይሄ መንግሥታዊ አገልግሎት ከላይኛው መሪ እስከ ታችኛው የቀበሌ አስተዳዳሪ ያለውን ሹመኛ፤ ከከፍተኛው እስከ ታችኛው ባለሙያ፤ ብቻ በሁሉም የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሕዝብን ለማገልገል ሲባል ከተሰየሙ ኃላፊዎች እስከ ባለሙያው ያለውን የሚመለከት ነው:: በዚህ መልኩ ሕዝባዊ አገልግሎትን ለመስጠት የተደራጁ ተቋማት፤ ተቋማቱን የሚመሩ ኃላፊዎች እንዲሁም ሥራዎችን በሙያቸው እንዲያቀላጥፉ የተመደቡ ባለሙያዎች ይሄን ኃላፊነት ከመወጣት አንጻር ትልቁና ሊላበሱት የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የሕዝብ አገልጋይነትን ከፍ ያለ ሰብዕና ነው::

ይሁን እንጂ ይሄ የአገልጋይነት ከፍ ያለ ልዕልና ከዕለት ዕለት እየተሸረሸረ ስለመምጣቱ በርካቶች በቃል ከሚናገሩት በላይ በመሬት ላይ ያለው እውነት በግልጽ ይመሰክራል:: ዛሬ ላይ ሕዝብን ለማገልገል መቀመጣቸውን አውቀው የሚሠሩ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በጠራራ ፀሐይ በኩራዝ መብራት የሚፈለጉ ሆነዋል:: ምክንያቱም አገልጋይነት የሚለው ተግባሩ ቀርቶ ቃሉ በራሱ የደበዘዘ መስሏል፤ አገልጋዮችም ተግባራቸውን በሕዝብ ወደ መገልገል አሸጋግረው ተገልጋይን ማማረርና አገልግሎት ለማግኘት በእግር ሳይሆን በእጅ መሄድ ግድ ያለበትን ሃቅ እንዲለማመድ አስገድደውታል::

ዛሬ ላይ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞንም ሆነ በክልል፤ በከተማ ደረጃም ሆነ በክፍለ ከተማ፣ አለፍ ሲልም በሚኒስቴር መስሪያቤቶች፣ በፋይናንስ ተቋማት እና በሌሎችም የክልልም ሆነ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ሁሉ ሕዝቦች ብርቱ ቅሬታን ሲያነሱ፤ ለአገልግሎት ወንበር የተሰጣቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ሙያቸውን በእጅ መንሻ ካልሆነ ለሕዝብ እያደረሱ እንዳልሆነ ብዙዎች የሚናገሩት እውነት ሆኗል:: ሕዝቡ:- የመታወቂያ አገልግሎት፤ የውልና ማስረጃ አገልግሎት፤ የፓስፖርት አገልግሎት፤ የመንጃ ፈቃድ፤ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት፤ የመሬትና መሬት ነክ አገልግሎቶች፤ የቅጥርና ዝውውር ሥራዎች ሳይቀር በእጅ መንሻና ጉቦ ካልሆነ በስተቀር የሚቀመሱ አልሆኑም ማለት ከጀመረ ውሎ አድሯል::

ይሄ ደግሞ ሕዝቡ በመንግሥት የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ምሬት እንዲያሰማ፤ ከመንግሥት ጋር ያለው መልካም ግንኙነት እያደር እንዲላላ፤ በመንግሥት ኃላፊዎችና ባለሙያዎቻቸው አሠራር ላይ መተማመን እንዳይኖረው፤ የመንግሥት አገልግሎት ለማግኘት የተሟላ መረጃና ሰነድ ሳይሆን እጅን በእጅ መንሻ አዳጉሶ መሄድ የግድ ብሎ እንዲያስብ፤ በጥቅሉ መንግሥታዊ አገልግሎቶች በመብት ሳይሆን በገንዘብ ብቻ ማግኘት አለብህ ተብሎ የተወሰነበት ያህል እንዲሰማው እያደረገ ይገኛል::

ይሄ ደግሞ ሕዝብ ከፍ ወዳለ ቅሬታ እንዲሸጋገር ብቻ ሳይሆን፤ በመንግሥት መዋቅር ውስጥም ስር የሰደደ የሰብዕና መበስበስ እንዲስተዋል አድርጓል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰሞኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያሰሙት እውነትም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: ሙስና ቀይ መስመር ነው ቢባልም ቀይ ምንጣፍ አድርገው በሌብነት ክብር ውስጥ የሚረማመዱበት፤ በአንጻሩ አገልግሎት በእግር ሄደው የሚያገኙት ሳይሆን በእጅ ጨብጠው የሚቀበሉት ሸቀጥ ሆኖ ስለመስተዋሉ አስረግጠው የተናገሩትም ለዚሁ ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዛሬ ላይ ገንግኖ የወጣውን ሙስና በግልጽ ችግር ሆኖ ስለመታየቱ ከመናገር ባሻገር፤ ሙስናን መዋጋትና ሙሰኞችን አደብ ማስያዝ የመንግሥት ቀጣይ አቅጣጫ ስለመሆኑም ነው ያረጋገጡት:: ይሄን ከቃል ያለፈ ተግባር ለመጀመር ቁርጠኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥም የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ አዋቅረው ወደሥራ እንዲገባ፤ ሕዝቡም ከዚህ ኮሚቴ ጎን ሆኖ ሙሰኞችን በማጋለጥና ርምጃ እንዲወሰድባቸው ማስረጃዎችን በማቀበል በኩል እንዲተባበር ጥሪን አቅርበዋል::

ይሄ በመንግሥት በኩል የተወሰደ መልካም ተነሳሽነትና ችግሩን ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት ነው:: ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም ሙስናና ሙሰኞች በአደባባይ ያሉ ቢሆንም፤ ተግባራቸው ግን በረቀቀና በተጠና መልኩ የሚፈጸም ከምስጢርም በላይ ምስጢር ነው:: ይሄ ምስጢር ግን ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ የተሸሸገ ያለመሆኑ ደግሞ እሙን ነው:: ምክንያቱም ሙሰኛውም፣ ሙሰኛውን ቀላቢውም በዚሁ የሕዝብ ውቂያኖስ ውስጥ ተሸሽገው ያሉ ናቸውና:: በመሆኑም እነዚህን ሙሰኞች ከተሸሸጉበት ለማውጣትና ምንጫቸውን ለማድረቅ ይቻል ዘንድ የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎችን በወጉ መፈተሽ ተገቢ ነው:: ምክንያቱም የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎች/ተቋማት ለሙሰኞች የመነሻና የሙስናውን መንገድ መለማመጃ ቦታዎች እንደመሆናቸው፤ እነዚህን ስፍራዎች መፈተሽ ማለት በየደረጃው ሙስና የዘጋውን የአገልግሎት አውድ ሁሉ መክፈት ማለት ነው::


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ</u>**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**<u>ዋና አዘጋጅ</u>**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**<u>አድራሻ</u>**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**<u>ማከፋፈያ</u>**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ‹‹ደሃ ሆኖ በሰቆቃ ለመቀጠል...

አምና ለማጥናት ሞክረን ነበር፤ በተለይ የዱቄት ፋብሪካ ላይ የነበረና በብዛት ከውጭ የሚገባ ስንዴ ይጠቀሙ የነበሩ ፋብሪካዎች አምና ችግር ገጥሞናል የሚል ሮሮ ሲያቀርቡ አልሰማሁም። ይህ ነገር በየዓመቱ እየተቀየረ ይሄዳል።

ለምሳሌ አርባ ምንጭ ላይ ያለ የአግሮ ኢንዱስትሪ ሁሉ ነገር ተሟልቶለታል ማለት አይደለም። በዚሁ ረገድ በቁራ ደረጃ ያሉ ኢንተርናሽናል ላኪዎች የእንስሳት ሀብቱ በዛው ልክ ቀርቦላቸዋል ማለት አይደለም። የእንሳሳት ሀብቱ መቅረብ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የሚሄደው ስለሚበዛ ነው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተደማምረው በበቂ ሁኔታ እየቀረቡ አይደለም።

ስለዚህ የመጀመሪያው ነገር እቅድ መያዝ አለበት። አንደኛ መቼ? የሚባለውን ይፈልጋል። ይህን በተመለከተ ባለድርሻዎችን ባሳተፈ መንገድ ከእቅዱ ጀምረን ስራ እየሰራን ነው። ሁለተኛው በተለይ ከምርት አቅርቦቱ አንጻር በተለይ ፋብሪካ ያላቸው ሰዎች ካፒታሉ ኖሯቸው እንደቢዚነስ ፋብሪካውን ብቻ ሊሰሩት ይችላሉ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ የምንመክረው የንግድ እርሻን ይዞ እንቅስቃሴ ያላደረገ አካል በጣም ትልቅ ማኑፋክቸሪንግ የዘይትም ይሁን የሌላ ፕሮሰስ የሚያደርገው ማሽን ቢኖረውም እምብዛም ውጤታማ መሆን አይችልም። የሚያመርተው አርሶ አደሩ ነው፤ አነስተኛ አርሶ አደሩ አስቦ የሚያመርተው ደግሞ በብዛት ፍጆታውን አስቦ ነው። ገበያውን አስበው የሚያመርቱት የተወሰኑት ብቻ ናቸው። የኩታ ገጠምን ጽንሰ ሐሳብ ያመጣነው ለዚህ ነው። አሁን ኩታ ገጠም ያለበት ደረጃ ጥሩ የሚባል ነው። ከ47 እስከ 50 በመቶ ደርሰናል። እውነት ለመናገር ባለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት ለውጦች አሉ። ግን ከኢንዱስትሪ ፍላጎት አንጻር የተሟላ ነው ማለት አይቻልም። አንዷ ላይ ቢሟላ ሌላው ላይ የሚጎድል ነገር ነው ያለው። በጥቅሉ ግን ውጤታማ መሆን የሚቻለው ምርታማነትን ማሳደግ ሲቻል ነው። ከግብርና ሴክተር ሁሉም ይጠብቃል። ነገር ግን ለግብርናው ምን ሰጥተነው ነው ከእሱ የምንጠበብቀው የሚለው መታሰብ አለበት። መንግስት አንዳንድ ነገር ለይቶ ድጎማ የማድረግ እንዲሁም የማዳበሪያ ፋብሪካዎችን ወደፊት እንዲኖሩ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በመሰረታዊነት መፈታት ያለባቸው ናቸው። በሚገባ ተፈቷል የማልለውም የፋይናንስ አቅርቦት ስራ ባንኮቹ ከከተማ ወጥተው ምርቱ ላይ የመስራት ባህል ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፤ እነዚህ ነገሮች በደንብ ከተሰሩ ለውጥ መምጣት ይችላል።

አዲስ ያስተዋወቅነው የኮንትራት ፋርሚኒግ (አመራረት ) ነው። የኮንትራት አመራረት ጽንሰ ሐሳቡ ወጣ ብለው ከአርሶ አደሮች ጋር ካመረትኩ በኋላ ምርቴን ለመሸጥ ሳልጨናነቅ የማምርትበት አይነት ኢንቫይሮሜንት የሚፈጠርበት ነው። ለምሳሌ ፋብሪካዎቹ ግብስ ከሚያመርቱ አርሶ አደሮች ጋር ቀድመው ውል ይገባሉ። አርሶ አደሩም ይህ ሲሆን ይበረታታል። ምርቱንም ለመጨመር ይሄዳል። እኛ በአሁኑ ወቅት ለዘይት ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን ነን። ምክንያቱም አንዱ የሚያምሰን ከዋጋ ንረት አኳያ ዘይት ስለሆነ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በምርት ደረጃ ማምረት የምንችላቸው ሰፊ አቅም እንደ አገር አለ፤ ቀደም ሲል እንዳነሳነው የሌማት ትሩፋት አይነት ማለት ነው፤ ይህ በአንዳንድ አካባቢ ጎላ ብሎ ይታያል፤ በሌላ አካባቢ ደግሞ ምርቱ መመረት እየቻለ ነገር ግን የምርት አቅርቦትና ምርቱን ከማስተዋወቅ ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ለአብነት የሩዝ ምርትን መጥቀስ ይቻላል፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ፓርላማ ላይ ባደረጉት ማብራሪያ ላይ ጉዳዩን አንስተዋልና በዚህ ላይ ሚኒስቴሩ ምን እየሰራ ነው?**

**አቶ ዑመር፡-** በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አግሮኢኮሎጂ ሁሉም አይነት ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ቦታ የመሰረት ልማት ያለመኖር፣ ወደምርቱም ለመሄድና ምርቱንም ለመሰብሰብ ያስቸግራል። አሁን ለምሳሌ ሰፋፊ ቦታዎች ያሉትን የኢትዮጵያውያንን ባህል ስናይ 60 በመቶ የሚሆን መሬት ላይ ከ40 በመቶ በታች የሚሆን ሰው ነው ያለው። ደጋማው ደግሞ 40 በመቶ የሚሆን መሬት ላይ ከ60 በመቶ በላይ ሰው ነው ያለው። በደጋና በወይና ደጋ ላይ ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፤ ቆላው ላይ ግን መሬት አለ፤ ስራው ግን በዚያ ልክ እየተሰራ አይደለም። ስለዚህ ልምድ በዚህም ላይ ቢሆን ጥሩ ነው። ሌላው ደግሞ የክልሎች ነባራዊ ሁኔታ የኅብረተሰቡ አረዳድ ብቻ ሳይሆን ፈተናቸውም ይለያያል። መሰረተ ልማቱም ይለያያል። ስለዚህ ያደረግነው ነገር አገራዊ ፕሮግራሙ እንዳለ ሆኖ ክልሎች በራሳቸው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ነው። ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሱማሌ፣ ደቡብም እንቅስቃሴ አድርጓል፤ አፋር በግማሽ አድርጎ ሰነዱን አልጨረሰውም። ስራዎች ግን ተለይተው መሰራት አለባቸው። ለምሳሌ ሱማሌ ክልል ትልቅ አቅም ያለበት ነው፤ ግን ደግሞ ድርቁ አለ። ለዚህ አንዱ ምክንያት እዛ አካባቢ የውሃ እጥረት መኖሩ ነው። ይሄ ደግሞ መኖውንም ለማምረት እንስሳውንም ለማቆየት የሚቸግር ነው።

ሩዝ ላይ ሲመጣ መጀመሪያ ያደረግነው አስሩ አገራዊ ፕሮግራሞች ውስጥ የሩዝ አቅም ያለው የት ነው የሚለውን መለየት ነው፤ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየተለመደ ያለው አንዱና ዋናው ምግብ ሩዝ ነው፤ ከዚህ አንጻር ኢምፖርት የሚሆነውን ለየን፤ ክፍተቱን ካየን በኋላ ወደትግበራ ለመግባት መጀመሪያ ላይ ስንዴ ላይ በደንብ ተይዘናል። ይህ የሚካድ አይደለም። ከዛ የስንዴው ጉዳይ ፈር ሲይዝልን ሩዝ ላይ መጥተናል። አሁን ሩዝ ላይ ሌላው ቀርቶ አኩሪ አተር (ሶያቢን) ላይ ሌሎችም የቅባት እህል የሆኑና ለዘይት እንደግብዓት የሚያገለግሉት ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን ነው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የማመጣጠን ነገር ይመጣል። የሌማት ትሩፋት ፕሮግራሙ ለሁሉም በእኩል ተዘርግቷል። ነገር ግን እኩል ይንቀሳቀሱበታል ማለት አይደለም።

**አዲስዘመን፡- ግብርናውና ኢንዱስትሪው ተጣጥሞ እየሰራ ያለው እንዴት ነው? ምን ያህልስ ተመጋጋቢ እየሆነ ነው?**

**አቶዑመር፡-** የተቋማት መዘመን አንዱ ማሳያው በውስጥ የሚሰራው ስራ ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹ ጋር ከእቅድ ጀምሮ ሲሆን ፤ ስራው በራሱ ዲስፒሊን የሚጠይቅ ነው። ከራስ የተረፈና ሕዝብን ታሳቢ ያደረገ ስራ ነው መሰራት ያለበት። ለምሳሌ የእኛን መስሪያ ቤት ከወሰድኩ ብዙ ባለድርሻዎች አሉ። አንዱን ከፍ ለማድረግ ሲሞከር ሌላውን ዝቅ ማድረግ ይመጣል። ስለዚህ ሁሌ ንቁ መሆንን ይጠይቃል። እንኳንስ አንዱ ለአንዱ ግብዓት የሚሆን ተቋም ቀርቶ ሌሎቹም አነስተኛ አገልግሎት ከመስሪያ ቤቱ የሚፈልጉም ሁሌ ንቁ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ለምሳሌ እኔ የሚፈለገውን የምርት መጠን ለማምጣት በጥራትና በብዛት የሚቸግረኝ ምንድን ነው? እድሉስ ምንድን ነው? የሚለውን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማወቅ አለበት። ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፋብሪካዎች ከተቋቋሙ በኋላ በግማሽና ከዛ በታች አቅም እያመረቱ ነው ብሎ ሪፖርት ሲያድርግ ለምን? የሚለውን እኔ እዛ ሆኜ ማወቅ አለብኝ። ቢያንስ ይህንን መፍጠር ችለናል። ከባለሙያ ጋርም በአመራር ደረጃም ከዛ በማለፍም ኢንዱስትሪ ያላቸውን ተቋማት በጋራ አምጥተን መለየት ችለናል። ዋጋ መክፈልን ግን ይጠይቃል።

ሁለተኛው ማን ምን እንደሚፈልግ መለየት ነው፤ ይህን ለማድረግ ደግሞ ሁለቱም ተቋማት አቅም አላቸው። ከሌሎች ተቋማትም ጋር ሰርተናል። እቅዶቻችንን እንደገና ማየት ያስፈልገናል፤ ምክንያቱም ፍላጎቶች ዓመት እየጠበቁ ብቻ ሳይሆን በወራት ውስጥም ይቀያየራሉና ነው። ስለዚህ ቲዮሪዎቹን እንደገና መከለስ ያስፈልገናል። ኮቪዱም ግጭቱም ስለነበር እቅዱን መፈተሽ ተገቢ ነው።

ደሃ ሆኖ በሰቆቃ ለመቀጠል አሊያም ሰርቶ ለመለወጥ የሚያስችል ዕድል በእጃችን አለ። የተሻለውን በመምረጥ አገራችንን ወደፊት መውሰድ ከዚህ አንጻር ደግሞ የትኛውም አይነት ትችት ሲመጣ ተቀብሎ ማየት ምንም የሚያስከፍል ነገር አይኖረውም። ነገር ግን ትችት በሁለት ገጽታ የሚታይ ነው። በበጎም በጎ ባልሆነ በኩል ማለት፤ በጎውን ተቀብሎ መማር ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበርዎ ቆይታ ከልብ እናመሰግናለን።**

**አቶ ዑመር፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ፋሽን

## ወጣቷ ባስራዕይ ዲዛይነር

**ደበል ካሳ**

ሄርሜላ ተሾመ ትባላለች:: የሃያ አራት ዓመት ወጣት ናት:: ነፍስ ካወቀችበት ማለትም ከሰባት ዓመቷ ጀምራ ከእናትና አባቷ በወረሰችው የፋሽን ዲዛይነርነት ሙያ ተሰማርታ ላለፉት አስራ ሰባት ዓመታት እየሠራች እንደምትገኝ ትናገራለች:: ከቤተሰቧ በተረከበችው ሙያ ላይ ዕውቀትና ክህሎት ጨምራ፣ በዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ታግዛ ሥራውን የበለጠ አጠናክራ በውጤታማነት ለማስቀጠል ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጨርቃ ጨርቅና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በ2013 ዓ.ም (በኮቪድ ወረርሽኝ የተነሳ ወደ2014 ዓ.ም የተዛወረ) በፋሽን ዲዛይንና ቴክኖሎጂ ተመርቃ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች::

በአባቷ አቶ ተሾመ ስሜ እና እናቷ ብስራት ጣሰው የተመሠረተው "ኤም.ኬ ዲዛይንና ዲኮር" ከተመሠረተ አሁን ላይ ሃያ ስምንተኛ ዓመቱን ይዟል:: ከሰባት ዓመቷ ጀምራ ላለፉት አስራ ሰባት ዓመታት በእናትና አባቷ ድርጅት ውስጥ በፋሽን ዲዛይነርነት እየሠራች የምትገኘው የ24 ዓመቷ ወጣት ሄርሜላ፤ "ድርጅታችን ከእኔ ዕድሜ በላይ ከሃያ ሰባት ዓመታት በላይ በዘርፉ ተሠማርቶ እየሠራ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው" ትላለች:: በዋነኝነት በባህል አልባሳት ስፌትና ዲዛይን ሥራ ላይ ተሰማርቶ እየሠራ መቆየቱን የምትናገረው ዲዛይነር ሄርሜላ አሁን አሁን ግን በባህላዊ ብቻ ሳይሆን በዘመናዊ አልባሳት ስፌትና ዲዛይን ላይ ጭምርም እየሠሩ መሆናቸውን ትገልጻለች::

ከስፌትና ዲዛይን እንዲሁም ሽያጭ በተጨማሪም በአሁኑ ሰዓት በተለይም ለልዩ ልዩ ሁነቶች የሚሆኑ ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳትን በማከራየት፣ የተለያዩ ሁነቶችንና አውደ ርዕዮችን በማዘጋጀትና ለዚሁ የሚሆኑ ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳትን በሽያጭና በኪራይ በማቅረብ ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ትናገራለች:: የምርቶቻቸውን የገበያ ተደራሽነት በተመለከተም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን ደንበኞች ሁሉንም ባማከለ መንገድ ሁለገብ ምርቶችን በማምረትና በማቅረብ ላይ እንደሚገኝ ትናገራለች::

ወጣቷ ዲዛነር ሄርሜላ፤ "በቀጣይ መሥራት የምፈልገው በልዩ ሁነትና በዓላት ወይንም መርሃ ግብሮች ጊዜ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሰዓትና በየትኛውም ቦታ መለበስ የሚችሉ በዘመናዊ መንገድ ተሰፍተው የተዘጋጁ የባህል አልባሳትን ለኢትዮጵያውንና ለአፍሪካውያን ብሎም ለዓለም ማቅረብ ነው" በማለት የወደፊት ራዕይዋን ትናገራለች:: ይሁን እንጂ የኅብረተሰቡ የባህል አልባሳትን ለዘወትር የመጠቀም ፍላጎትና ባህል በጣም ዝቅተኛ መሆንና ገበያው በተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ መያዙ እርሷም ሆነ ድርጅቷ ለሰነቁት የወደፊት ራዕይ ትልቅ ተግዳሮት መሆኑን በስጋትነት ታነሳለች::

ለአብነትም የአገር መከላከያ ሠራዊት አልባሳትና ጫማዎች፣ ቦርሳዎች፣ የተማሪዎች ዩኒፎርም አልባሳትና ቦርሳዎች፣ የተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች አልባሳትና ጫማዎች፣ ለተለያዩ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች የሚያስፈልጉ እንደመጋረጃ ዓይነት አልባሳትና ጨርቆችን... የማምረትና የማቅረብ ዕድል የተሰጠው ለጥቂት የአገር ውስጥና የውጭ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራች ድርጅቶች መሆኑን ታነሳለች::

"እናም የቱንም ያህል ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳትን በምርጥ ዲዛይንና በጥራት ብናመርትም የገበያ ዕድሉ የሚሰጠው ሁሌም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ትልልቅ የአገር ውስጥና የውጭ አምራቾች ብቻ ከሆነ በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የምንገኝ አምራቾች እንዴት ተወዳዳሪ መሆን እንችላለን? እንዴትስ ወደከፍተኛ አምራችነት መሸጋገር እንችላለን?" ትላለች:: ስለሆነም መንግሥት ድጋፍ ባያደርግልን እንኳን ቢያንስ የገበያ ዕድሉን ለእኛም ሊሰጠን ይገባል ትላለች::

ለአንድ አምራች ለሕልውናው መቀጠልም ሆነ ወደቀጣዩ የእድገት ደረጃ ለመሸጋገር ዋነኛው ነገር ገበያ መሆኑን የምታመላክተው ዲዛይነር ሄርሜላ መንግሥት የገበያውን ሁኔታ ካመቻቸላቸውና ዕድሉን ከሰጣቸው የእርሷና ቤተሰቦቿን ጨምሮ በዘርፉ የተሰማሩ የመሥራት አቅም ያላቸውና ወደከፍተኛ ደረጃ ማደግ የሚችሉ ሌሎችም በርካታ ድርጅቶች መኖራቸውን ትጠቁማለች:: በገበያ በኩል ያለው ከተፈታ ከኅብረተሰቡ አመለካከትና ባህል ጋር በተያያዘ ያለው ቀሪው ተግዳሮት በአንድ ጊዜ ባይሆን ቀስበቀስ በሂደት መፍታት የሚቻል መሆኑንም ታመላክታለች:: ይህንን ለማድረግም የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችና መገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ ሚና ያላቸው መሆኑንም ታስረዳለች::

ለዚህም ከራሳችን መጀመር አለብን ትላለች:: መጀመሪያ መንግሥትና የአገራችንን ዜጎች አምነውብን ዕድሉን እንዲሰጡንና ምርቶቻችንን እንዲገዙን ማድረግ ይገባናል:: ከዚያም በእኛው የተሠሩና



የተመረቱ "በኢትዮጵያ የተመረቱ" የሚሉ ባህላዊም ሆኑ ዘመናዊ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርቶቻችንን ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ብሎም ለአውሮፓና ለመላው ዓለም መላክ እንችላለን ትላለች ወጣቷ ባለራዕይ ዲዛይነር ሄርሜላ ተሾመ::

የባህል ልብሶቻችን የሚሠሩበት ጨርቅ ጥራና የሚሰፉበት ክር ጥንካሬም ለዘወትር ልብስነት ተመራጭ እንዳይሆኑ አንደኛው ተግዳሮት መሆኑንም ነው ዲዛይነር ሄርሜላ የምታመለክተው:: ይህንን ችግር ለመቅረፍም የእርሷና የቤተሰቧ ድርጅት የሆነው ኤም.ኬ ዲዛይንና ዲኮር በመፍትሔ አማራጭነት የያዘው ጨርቆቹን ከውጭ በማስመጣትና በአገር ውስጥ ሰፍቶ ለገበያ ማቅረብ ነው:: ለዚህም ብራንዲንግ ላይ ትኩረት አድርጎ ለመሥራት መወሰኑንም ታመላክታለች::

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ዓለም ዋንጫው እና አንዳንድ ትዝብቶች

**አቤል ገብረኪዳን**

የኳታሩ የአለም ዋንጫ ከተጀመረ እነሆ ሳምንት አለፈው:: እንደተለመደው አይኖች ሁሉ ወደ መካከለኛዋ ምስራቅ ሀገር ዞረው ሁሉም ሰው ሙሉ ትኩረቱን እዚያው ላይ አድርጓል:: ኳሱም እንደተጠበቀው ዘና የሚያደርግ እየሆነ ነው:: የሳውዲን እና የአርጀንቲናን ጨዋታ ያየ ሰው ለዚህ ምስክር መሆን ይችላል:: ጨዋታው አዝናኝ እና አስደሳች ከመሆኑም በላይ እግር ኳስ ለምን ተወዳጅ ስፖርት እንደሆነም አመላካች ነው:: በኳስ የማትታወቀው ሳኡዲ አረቢያ ለዋንጫ የታጨችውን አርጀንቲናን የረታችበት መንገድም አሰደናቂ ነው::

በእግር ኳስ የተነሳ የሚናደዱ እና የሚሰዳደቡ ሰዎች መብዛት ያስገርማል:: በጣም አስገራሚ እኮ ነው፤ ዛሬም በዚህ ዘመን ቡድኔን ተናገራችሁብኝ ብለው የሚዘላለፉ ሰዎች አሉ:: እኔ ራሴ በአንድ የሆነ አገር ደጋፊ ነኝ በሚል ሰው በግል የማህበራዊ ድረገጽ እንዳልሸጥ እንዳልለወጥ ተደርጌ ተሰድቤያለሁ:: ይሁን ግድየለም ሀገር ወደ ሰላም በምትሄድበት በዚህ ወቅት ጦርነት አልከፍትም ብዬ አሰናበትኩት እንጂ ነገሩስ ራሱን የቻለ ጦርነት ቀስቃሽ ነገር ነበር:: እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ኳስ ስሜታዊ ያደርጋል፤ የሚወዱት ቡድን ሲያሸንፍ የሚፈጥረው ደስታ ከፍተኛ ነው:: ሲሸነፍም ንዴቱ እንደዚያው ነው:: ብሽሽቅም የኳስ ባህል ነው፤ ነገር ግን መስመር አልፎ መሰዳደብ እና መዛዛት አላስፈላጊ ነገር ነው:: አሁን አንድ ኢትዮጵያዊ በሆነ አገር ሽንፈት ተናድዶ ሌላ ኢትዮጵያዊን መታ ቢባል ነውር አይሆንም፣ እነሱስ ይሄን ቢሰሙ አይስቁብንም፣ በእውነቱ የኛ ነገር እኮ ቅቤ አንጣሪዋ እያለች ጎመን ቀንጣሽዋን ምች መታት እንደማለት ነው::

ሌላኛው ትዝብቴ ደግሞ ምን መሰላችሁ፤ ምእራባውያኑ በኳታር ላይ እያደረጉ ያሉት ጫና እና እኛ የተረዳንበት መንገድ አስገርሞኛል:: ሁላችንም እንደምናየው ምእራባውያኑ የኳታርን የአለም ዋንጫ ለማጠልሸት የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ነው:: ነገሩ በእርግጥ አስገራሚ አይደለም:: የትኛውም ነገር እነሱ በሚፈልጉት መልኩ የራሳቸውን እሴቶች ለማንጸባረቅ ካልተጠቀሙበት ነገሩን እንደማይጠቅም አድርገው ማጣጣል የተለመደ አካሄዳቸው ነው:: አሁን እያረጉት ያሉትም ነገር ይሄንኑ ነው:: ከአሁን በኋላ የአለም ዋንጫም ሆነ ሌላ ትልቅ ውድድር ማዘጋጀት ከምእራባውያኑ ጋር በእሴት ወደማይቀራረቡት አፍሪካ፣ መካከለኛው ምስራቅ እና አንዳንድ የእስያ ሀገራት እንዳይሄድ ለማሳመን ነው የማጣጣል ዘመቻው አላማ:: ብዙ የኛ ሀገር ሰውም ይሄን ተረድቶታል:: ታዲያ ይህ የምእራባውያን አካሄድ እንዲህ ከገባን ይህን መሰል ነገር በገዛ ሀገራችን ላይ ሲያካሂዱ ለምንድን ነው የማይገባን፤ በአንድነት ለምን አንቆምም:: እነሱ የማያዙት መንግስት እና እነሱ የሚፈልጉት ነገር የማይፈጸምባት ሀገር ኢ ዴሞክራሲያዊ ፤ ኋላቀር ፤ ሰላም አልባ እንደሆነች አድርገው ሲስሉ እያየን አይደል:: ስለዚህ በኳታር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ያሳየነውን ሀዘኔታ ለገዛ ሀገራችንም ማድረግ አለብን:: እንዲያውም ልናውቀው የሚገባው ዋነኛ ጉዳይ ኳታር የፈለገ ጫና ቢደረግባት መቋቋም የምትችል ሀገር ናት:: የነዳጅ ሀብቷ የፈጠረላት የኢኮኖሚ ጉልበት አለ:: አልጀዚራን የሚያህል ግዙፍ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያም የግሏ ነው:: ብዙ ውስጣዊ ትርምስም የለባትም:: ለዚያም ነው ባህር ተሻግራ አፍሪካ ቀንድ ድረስ የሚደርስ ፖለቲካዊ ክንድ መዘርጋት የቻለችው:: ከዚህ አንጻር ከታየ ኢትዮጵያ ኳታርን የምትበልጠው በህዝብ ብዛት ብቻ ነው:: ኢትዮጵያ በተጽእኖ ውስጥ ለመውደቅ ቅርብ ናት:: ታዲያ እኛ ግን ለተጽእኖ ቅርብ ከሆነችው ከገዛ ሀገራችን ይልቅ ተጽእኖ ተቋቁማ የአለም ዋንጫን ለማዘጋጀት ለቻለችው ኳታር አዝነናል:: ይህ አግባብ አይደለም:: እንዲያውም ለዚህ የሚስማማው አባባል አሽቃባጭ ዝናብ ወንዝ ዳር ያካፋል የሚለው ነው::

አንድ ትዝብት ልጨምር፤ የአለም ዋንጫውን የሚያስተላልፉ መገናኛ ብዙሀን ውስጥ ባሉ ጋዜጠኞች ዘንድ ያለው የእውቀት ክፍተት:: በጋዜጠኝነት ስራ አቅራቢው እና ተደራሲው በእውቀት በጣም የተቀራረቡበት ዘርፍ የስፖርት ጋዜጠኝነት ዘርፍ ነው:: ጋዜጠኛው ያለውን መረጃ ያህል አድማጩም በስልኩ ይዞ ነው የሚዞረው:: ስለዚህም ጋዜጠኛው ሰሚው የማያውቀውን ነገር ፈልጎ ማምጣት አለበት:: ነገሩ ግን እንደዛ አይደለም፤ ብዙውን ጊዜ እንዲያውም ሰሚው ከተናጋሪው ቀድሞ መረጃ ይደርሰዋል:: ይህ አሳፋሪ ነገር ይሆናል:: ስለዚህም ይህን የአለም ዋንጫ የሚያስተላልፉ ጣቢያዎች እና የስፖርት ጋዜጠኞች የአለም ዋንጫውን በርከት ላለ ጊዜ የተከታተሉ ሰዎችን ቢጋብዙ መልካም ይሆናል:: ለምሳሌ ያህል ከ1994ቱ የአለም ዋንጫ አንስቶ እስካሁን ያሉትን 7 የአለም ዋንጫዎች የተመለከቱ እና እያንዳንዱን ጨዋታ የሚያስታውሱ ሰዎች አሉ:: ጋዜጠኛ ባይሆኑም ስቱዲዮ ተገኝተው ያን ትውስታቸውን እያስታወሱ አሁን ያለውን ጨዋታ ቢያዋዙ ለተመልካቹ አዝናኝም ጠቃሚም ይሆናሉ:: ይህንን ነገር እስኪ ሚዲያዎችም አስቡበት::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# እኔ... ከዚያ... ትውልድ ነኝ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

**ስሚመለከተው ሁሉ...**
**እንሆ ግለሰባዊ አቋም...**

እኔ ከዚህ ትውልድ አይደለሁም፤ ከዚያኛው ከአባቶቼ ትውልድ ነኝ። ከዛኛው አብሮ እየበላ፣ አብሮ እየጠጣ ኢትዮጵያዊነትን በፍቅር ቀለም ከቀለመው አብራክ ነኝ። ከዚያኛው... በጨዋነት አገር ካቆመው፣ በፍቅር ጥልን ከገደለው፣ በአንድነቱ ታሪክ ከሠራው ከዚያ ትውልድ ዘንድ ነኝ። እኔ በባዶ እግሩ እየሄደ ጫማ ካለበሰኝ፣ ሳይማር በፈሪሃ እግዚአብሔር ሁሉን ካወቀው፣ ፊደል ሳይቆጥር ዘመናዊነትን ካስተማረኝ ከዚያ ብሩክ አብራክ የበቀልኩ ነኝ። እኔ ብሔር ሳይል ሃይማኖት፣ ዘር ሳይል ጎሳ ፊደል ቀርጾ፣ የቀን መቁጠሪያ ሠርቶ ታሪክና ቀዳማይነትን ያለበሰኝ የዚያ የባለታሪክ ጵንስ ነኝ። እናም ራሴን በገዛ ፍቃዴ አሁን ካለው ከስሜታዊው ትውልድ አገለልኩ። በብሔር ስም ፍቅር ካጣው፣ በእኔነት ጽንፍ አንድነት ካጣው፣ በራስ ወዳድነት ኢትዮጵያዊነትን ከሻረው ከዚህ ትውልድ ተለየሁ። እናም እኔ አባቶቼን ነኝ ስል ሁሉም እንዲሰማኝ ጮህ ብዬ ተናገርኩ።

እኔ ሰው ነኝ፤ አባቶቼ ያስተማሩኝም ሰውነትን ነው። እናንተም ሰው ናችሁ፤ ያኛው ትውልድ የነገራችሁ ሰውነትን ነው። ታዲያ ሰውነት በዚህ ዘመን የት ገባ? ዛሬ ላይ የምንባላባቸው ብሔርና ቋንቋ፣ ዘርና እኔነት በምን ሚዛን ከሰውነት በለጡ? ለዚም ስል ራሴን ከእናንተ አገለልኩ፤ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ እኔ የእውነተኛዎቹ የአባቶቼ ፍሬ ነኝ ስል ተነሳሁ። ይሄ ሰው ምን ነካው? እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ዛሬ ላይ ሆኜ የዛሬነቴን ተቃውሜ ትናንትን በማማተሬ አበድክ ካላችሁኝም፣ መልሴ እናንተ እንጂ እኔ አላበድኩም ነው። ምክንያቱም ሰው የሚያብደውና ከተፈጥሮ ሚዛን የሚጎድለው ሰውነትን በሌላ ሲቀይር ነው። ሰው ኋላ ቀር የሚባለው የአባቶቹን የአንድነት ምድር በመለያየት የእኔ.... ብቻ፣ የእኛ... ብቻ፣... ሲል ነው። እናም እንደዚህ ልላችሁ ወደድሁ፡- አገር ድሀ የምትባለው ፍቅርን ያጡ ሕዝቦች ሲኖሩባት ነው። ብዙ የጋራ ታሪኮች እያሉ ሕዝብ ያን የጋራ ታሪክ መጠቀም ሳይችል ሲቀር ነው። የእኛ ድህነት ባለመሥራት የመጣ የሚመስለው ሞልቷል። የእኛ ድህነት የኢኮኖሚ ችግር ብቻ የሚመስለው ብዙ ነው። የእኛ ድህነት የኢኮኖሚ ድህነት አይደለም። የእኛ ድህነት የፍቅር ማጣት፣ የአንድነት ማጣት የወለደው ነው። የእኛ ኋላ መቅረት የከሸፈ የፖለቲካ ሽር የፈጠረው ነው። ዛሬ ላይ ጎልተው የምናያቸው ኢኮኖሚያዊም ሆኑ ማህበራዊ ችግሮቻችን አንድነት በማጣት የተፈጠሩ ናቸው።

ሰው አንድ ከሆነ፣ ሕዝብ በፍቅርና በአንድነት ከቆመ አይደለም ድህነትን፣ አይደለም ኋላ ቀርነትን ሌላም አይበግረውም። ትልቁ ችግራችን የአንድነት ማጣት ችግር ነው። ትልቁ ችግራችን ስልጣን እጃችን ሲገባ የእኛ የምንለው ክፍል መፍጠራችን ነው። ሆኖም የትኛውም የዓለም ስልጣኔ በሕዝቦች የአንድነት መንፈስ ተጠንስሶ ፍሬ ያፈራ ነው። ሩቅ ሳንሄድ በቀላሉ እንኳን የአድዋን ድል ብናይ አንድነት የፈጠረው ሆኖ እናገኘዋለን። አስቡት እስኪ..ዓለም ላይ በስልጣኔ ፊት አውራሪ የሆነች፣ በሎጀስቲክና በጦር ኃይል አካዳሚ አንቱታን ያገኘች፣ ከዚህ ሁሉ በላይ በአየርና በየብስ የሚምዘገዘጉ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቀች አገር በአንድ ድህና ባህላዊ መሣሪያ ባነገቡ ሕዝቦች ስትሸነፍ። ይሄን እውነት ምን ትሉታላችሁ? ይሄ እውነት የአንድነት እውነት ነው። ይሄ እውነት ታሪክ የቀየረ፣ ኢትዮጵያዊነትን ከአጽናፍ አጽናፍ ከፍ ያደረገ የአባቶቻችን የአንድነት ክንድ ነው። እኛም ከፍ ለማለት፣ አፈር ድሜ እያስጋጠን ካለው ኋላቀርነትና ድህነት እንድንወጣ አንድነት ነው የሚያስፈልገን። ዛሬን ሽሽቼ ትናንትን መፈለጌም ለዚሁ ነው።

ምክንያቱም እኔ ከዛሬው ትውልድ የስሜትና መነጣጠል መንገድ ርቄ በምክንያት የተፈጠርኩ፣ በምክንያት የምኖር ወጣት ነኝ። እኔ የአገሬ ድሀ መሆን፣ የወገኔ በቀን ሦስት ጊዜ አለመብላት የሚያሳስበኝ፣ ብሔሬ የማያስጨንቀኝ፣ በፖለቲካ ቅራኔ ጥላቻ የማላውቅ ምክንያታዊ ወጣት ነኝ። ለአገሬ ምርጡን የማስብ፣ ለድህው ወገኔ የምጨነቅ ባለ ራዕይ ወጣት ነኝ። እኔ የኢትዮጵያን ስም በመልካም ከሚያስተጋቡት ምርጦች ውስጥ ነኝ። በዘርና በብሔር፣ በቋንቋና በሃይማኖት ከሚባሉት ውስጥ አይደለሁም። የሚያግባቡንና አንድ የሚያደርጉን ብዙ ነገሮች እያሉ በለያዩን ጥቂት ነገሮች የምሸነፍና ድንጋይ ከሚያነሱት ውስጥ አይደለሁም። እንደ እኔ ትውልዱን የጠላ፣ እንደ እኔ በምክንያትና በማሰብ የሚኖር ካለ ይከተለኝ። እንደ እኔ ሰውነትን ያገነነ፣ እንደ እኔ ፍቅርና ይቅርታን አንድነትንም ለመልበስ የተሰናዳ ካለ ጎኔ ይቁም። እንደ እኔ ወገኖቹን ሁሉ የሚያፈቅር፣ ኢትዮጵያን ያለ ታማኝ ዜጋ ካለ አብሮኝ ይቁም። የዛኔ እኔም ትናንትን ከመናፈቅ ዛሬን ማጽናት ላይ እንድሠራ የብርታት ክንድ አገኛለሁ።

በእኔና በእናንተ መካከል የቆመ የማንነት ድንበር፣ ብሔርተኝነትን የሚሽር የህልውና አጥር፣ የአንድነት ምሰሶ ኢትዮጵያዊነት ነው። በዚህ ስም ካልተግባባን በሌላ በምንም አንግባባም። ፈጣሪ ስንት ጊዜ ታዘበን? አጋንንት ስንት ጊዜ ቀናብን?። ሁሉ ነገራችን በእጃችን ያለ ሕዝቦች ነበርን። ፍቅር ቢኖረን የጎደለን አንዳች እንደሌለ እንደርስበት ነበር። አንድነት ቢኖረን በዚህ ልክ በርሀብ፣ በዚህ ልክ በመገፋፋት ባልኖርን ነበር። እየሱስ ክርስቶስ ምድር ላይ ሰላሳ ሦስት አመት ሲኖር ፍቅርን ነበር ያስተማረን። እየሱስ ከፍቅር በላይ ገናና ነገር ቢኖር ስለዛ ነገር ያስተምረን ነበር። ግን ከፍቅር የሚልቅ ስላልነበረ ተወልዶ መስቀል ላይ እስከዋለበት ጊዜ ድረስ ፍቅር..ፍቅር እንዳለ ነበር። በጣም የሚገርመው በእሳት በታጠረ በመለኮት ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ዛሬም ፍቅርን ለሚያውቅ ልብ መንግሥቱን ክፍት ማድረጉ ነው። ዛሬም ለሚዋደዱ፣ ለሚፋቀሩ ልብና ነፍሶች ርስቱን ማዘጋጀቱ ነው። ሕዝቤ ሆይ ስማኝ ካለ ፍቅር የምንራመደው መንገድ ወደ ሞት ካልሆነ ወደየትም አያደርሰንም። ስለዚህ ፍቅርን እንወቅ።

ኢትዮጵያ መግባቢያ ቋንቋችን ናት። በእያንዳንዳችን ነፍስ ላይ፣ በእያንዳንዳችን ከንፈር ላይ ያለ ቅዱስ ቃላችን ናት። ይሄን እውነት ስላልተረዳነውና ስላልተቀበልነው ነው ዛሬ ላይ በብሔር ስም ብዙ ነገር እየሆነን ያለነው። ሰውነት ከዘር ቢበልጥብን ኖሮ፣ ኢትዮጵያዊነት ከብሔር ቢልቅብን ኖሮ ዛሬ ላይ እነዚህን ሁሉ የሞትና የጦርነት መርዶዎች ባልተጋፈጥን ነበር። እንደ እኔ ትውልዱን ሽሹና ወደ አባቶቻችን መንፈስ እንመንን። በአባቶቻችን የአንድነት ገዳም ውስጥ ፍቅርን ተምረን በቅተን ስንመለስ ምናልባት ያኔ አገርና ሕዝብ ምን ማለት እንደሆኑ ይገባን ይሆናል። እኔ ይሄን በማለም ትውልዱን ሸሽቼዋለሁ... እናተም ሽሹትና ይሄን በብሔር ከለላ መነጣጠልን የሚያስተምር ትውልድ ባዶውን እናስቀረው.. ከዚያም ኢትዮጵያን የሚል ትውልድ እንፍጠር።

በደምና በአጥንት የተቀለመ ኢትዮጵያ የሚል የአንድነት ሐውልት እኮ አለን። በሞትና በጀግንነት የተፈጠረ ሀበሻ የሚል ድንቅ የወል ስም እኮ አለን። ታዲያ ኦሮሞነት፣ አማራነት፣ ትግሬነት፣... ከዚህ መላቁ ለምን ይሆን? በየትኛው መስፈርት ነው ብሔርተኝነት ከኢትዮጵያዊነት ሊልቅ የሚችለው? አትሳቱ፣ ኢትዮጵያዊነት መሪያችን ነው። የተጠለልነው በኢትዮጵያዊነት ትልቅ ዋርካ ስር ነው። ኢትዮጵያዊነትን ሽሽቶ ብሔርተኝነትን መትከል ይሄን ትልቅ የጋራ ዋርካ መገንደስ፤ ትልቋን መርከብ አፍርሶ ትንንሽ ጀልባዎችን መሥራት ነው የሚሆነው። እኛነትን ሽሮ እኔነትን መትከል ለዘመናት በአባቶቻችን እንባና ደም የጸደቀችውን፣ ጸድቃም የለመለመችውን፣ ለምልማም ሰላሳና ስልሳ መቶም ያፈራችውን ኢትዮጵያን ማሳነስ፣ ማጠውለግ፣ ማምከን ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያዊነት ምንድነው ስንባል የምንመልሰው የጋራ እውነት ሊኖረን ይገባል። እኔ ግን እላለሁ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ ሌላ ብሔር፣ ሌላ ማንነት የለኝም። የእኔ ብሔር፣ የማንነቴ ጥላ፣ ዋርካዬ ኢትዮጵያ ናት። እናተም አይኑራችሁ፤ መማያችሁ ኢትዮጵያ ትሁን። አገራችን ኢትዮጵያ ለሁላችን የምትበቃ ማህጸነ ለምለም አገር ናት። እኛ ለእሷ እንመቻት እንጂ እሷ ለእኛ የሚሆን ብዙ ነገር አላት። እኛ በፍቅር፣ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን እንቁም እንጂ ማጀቷ ሙሉ ነው። ሌማቷ ጎድሎ አያውቅም። አይደለም ለእኛ ለሌሎች የሚሆን ብዙ ነገር ያለን ሕዝቦች ነን። ግን ይሄ ሁሉ ሙላት፣ ይሄ ሁሉ መትረፍረፍ ያለፍቅር፣ ያለአንድነት ምንም ነው።

> **እኔ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ደግፎ ያቆመኝ የብሔረሰብ ልጅ... የብሔረሰብ ቅይጥ ነኝ። እኔ እዚህ ቦታ ሰው ሆኜ እንድቆም አማራው፣ ኦሮሞው፣ ትግሬው፣ ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ወላይታው፣ ጋሞው፣ ጉራጌው፣ አርጎባው ሁሉም ብሔር አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዴት ራሴን በክብር ካቆመኝ ከዚህ ሕዝብ መገንጠል እችላለሁ?**

በብሔር ሳይሆን በሰውነት አገር እንስራ። በነውር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ትውልድ እንቅረጽ። የሚበጀን ይሄ ነው። የሰለጠነው ዓለም ብሔርተኝነትን ገድሎ ቀብሮታል። አሁን ላይ ስለብሔር ቢጠየቁ መልስ የሌላቸው ብዙ ስልጡን አገራት አሉ። በዚያው ልክ የብሔር አስተሳሰብ ዋጋ ያስከፈላቸውና ጥቁር ጠባሳ የጣለባቸው እንደ ሩዋንዳ ዓይነት አገራትም አሉ። የሚሆነንን መምረጥ የእኛ ፈንታ ነው። በበዛው ማንነታችን ውስጥ አንድ መሆናችንን ማጽናት እንጂ ዓለም ጥንት የተወውን ነገር እንደ አዲስ ጉዳይ አድርጎ ማውራትም ሆነ በዛ ነገር ሰላም ማጣት ከዚህ ዘመንም ሆነ ከዚህ ትውልድ የሚጠበቅ ተግባር ነው ብዬ አላስብም። ለዚያም ስል እኮ ነው ራሴን ከዚህኛው ትውልድ አግልዬ ሳይማሩ ወደተማሩት የአባቶቼ ዘመን መመነኔ። ያወቅን እየመሰለን ስህተት እየሠራን ነው። በጎ ያደረግን እየመሰለን ታሪካዊ ስህተት እየሠራን ነው። ያለፉትን በርካታ አመታት ማየት ብንችል ለስህተት የተጋለጠ ፖለቲካና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እያራመድን እንደነበር እንደርስበታለን። አሁንም እንደ ዜጋ፣ እንደ መንግሥት፣ እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ ራሳችንን መፈተሽ ይኖርብናል።

አገራችንን እያሳነስናት ያለነው ራሳችን ነን። ወጣቱ ራሱን ለአፍታ ቢመለከት እየሄደበት ያለው መንገድ ልክ እንዳይደለ ይደርስበታል። እኔ አማራ ብቻ፣ ኦሮሞ ብቻ ወይም ትግሬ ብቻ አይደለሁም፣ እኔ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ደግፎ ያቆመኝ የብሔረሰብ ልጅ... የብሔረሰብ ቅይጥ ነኝ። እኔ እዚህ ቦታ ሰው ሆኜ እንድቆም አማራው፣ ኦሮሞው፣ ትግሬው፣ ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ወላይታው፣ ጋሞው፣ ጉራጌው፣ አርጎባው ሁሉም ብሔር አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዴት ራሴን በክብር ካቆመኝ ከዚህ ሕዝብ መገንጠል እችላለሁ? እንዴትስ ውለታውን ረስቼ ኦሮሞ ነኝ፣ አማራ ነኝ፣ ትግሬ ነኝ እላለሁ? እንዴት በኩራት ካቆመኝ ብሔርብሔረሰብ ተለይቼ ሲዳማ ነኝ፣ ጉራጌ ነኝ እላለሁ? እኔ ሁሉንም ብሔርብሔረሰብ ነኝ። የእኔ የምለው ብሔር የለኝም። የእኔ ካልኩም ኢትዮጵያዬን ነው የእኔ የምላት። የእኔ ብሔር እሷ ናት። ከእንግዲህ ባለው ታሪካችን፣ ከእንግዲህ ባለው ሕይወታችን ኢትዮጵያን አገርም ብሔርም አድርገን እንድንኖር እፈልጋለሁ። ከእንግዲህ ባለው ማህበራዊ ሕይወታችን፣ ከእንግዲህ ባለው ፖለቲካችን ኢትዮጵያን ርስትም መመኪያም አድርገን እንድንኖር እሻለሁ። አገሩን ብሔሩ ያደረገ ትውልድ በዚህ ዘመን እንዲፈጠር እሻለሁ። አገሩን ሁሉ ነገሩ ያደረገ መንግሥትና ሕዝብ በዚህ ዘመን እንዲበዛ እሻለሁ። ያለዛ አትመልሱኝም። ያለዛ ከምናኔዬ አልመለስም። አገራችሁን ብሔራችሁ አድርጋችሁ ካልጠበቃችሁኝ እየሄድኩበት ካለው የምናኔ ጉዞ አልመለስም። ለዚህ ምስክሬ እመብርሃን ናት።

ብቻችንን ተዐምር የለንም። ብቻችንን አገርና ሕዝብ መሆን አንችልም። ብቻችንን አስፈሪ የመሆን አቅም የለንም። ኃይላችን አንድነታችን ነው። እድገታችን ብዙሀነታችን ነው። አንድ መሆን ከኃይልና ከውበት ባለፈ አስፈሪነትም ነው። ግርማ ሞገስ ነው። አንበሳነት ነው..ኩራት ነው። ታዲያ ወንድማማችነት አይሻልም ትላላችሁ? ታዲያ ፍቅርን ያገነነ፣ አንድነትን የወደደ አገርና ሕዝብ ቢወጣን ምኑ ነው ችግሩ? ልዩነታችንን ለውበት እንጂ ለመለያየት አንጠቀመው። ብዙሀነታችንን ለልማት እንጂ ለሁከት አናድርገው። ከጉዞዬ ትመልሱኝ ዘንድ..አብሬአችሁም በወንድምነት እቆም ዘንድ በኢትዮጵያዊነት ታረቁኝ። በኢትዮጵያዊነት ማሉልኝ። ያለዛ በዚህ ዘመን ተፈጥሬ የዚያ ዘመን ትውልድ እሆናለሁ። ያለዛ እናተን ትቼ ኢትዮጵያን አፍቅረው ወደሞቱት የዋህ ነፍሶች አዘግማለሁ። ያለዛ ርቄአችሁ በኢትዮጵያዊነት ገዳም ውስጥ ለብቻዬ እመንናለሁ። አበቃሁ፤ ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## ፍላጎቱና አቅርቦቱ እየጨመረ የመጣው የግብርና ሜካናይዜሽን

ስምስም መንግሥቱ

ወቅቱ በገጠር አዝመራ የሚሰበሰብበት ነው፤ እናም ሥራ ይበዛል። በዚህ ወቅት ከተሜው ወደ ገጠር ቢሄድ ሊመለከት የሚችለው ሰብስቡኝ ሰብስቡኝ የሚል በማሳ ላይ የደረሰ ሰብልና አርሶ አደሩ አዝመራውን ለመሰብሰብ የሚያደርገውን ርብርብ ነው።

በኢትዮጵያ በቆየው የግብርና ሥራ ባህል መሰረት አርሶ አደሩ በዚህ ወቅት አዝመራ ያጭዳል፤ይከምራል፤ ይወቃል። ውቂያ ለማካሄድ ራሱን የቻለ ዝግጅት ማድረግ ይገባል። ይህ አይነቱ ዝግጅት ምርት እንዳይባክን፣ ጥራቱ እንዳይጓደል፣ወዘተ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

እህሉ የሚወቃበት አውድማ በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርበታል፤ ለእዚህም አውድማው በእበት ተለቅልቆ በሚገባ እንዲዘጋጅ ይደረጋል። ይህን ማድረግ ደግሞ የሴቶች ድርሻ ነው። የአካባቢው ሴቶች ተሰባስበው ወይንም በደቦ አውድማውን በእበት ለቅልቀው ለውቂያው ዝግጁ ያደርጋሉ።

የተከመረው አዝመራ በአውድማው ላይ ይደረግና በሬዎች አፋቸው ታስሮ እንዲመላለሱበት ይደረጋል። ውቂያው በሚገባ እየተከነወነ እያለ አዝመራው በመንሽ እየተገለበጠ ፍሬው ከገለባው እስከሚለይ ድረስ በሚገባ እንዲወቃ ይደረጋል።

መንሽና ላይዳ የአርሶ አደሩ የውቂያ ወቅት ዋነኛ የግብርና መሣሪያዎች ናቸው። የተወቃው አዝመራ ገለባና ፍሬ በመንሽ በቅድሚያ ይለያል፤ ገለባው ከተለየ በኋላ አሁንም በመንሽና በላይዳ/ ትልቅ ማንኪያ ይመስላል/ ለንፋስ ይሰጣል። በዚህም እህሉ ከገለባው ይለያል።

ጤፍ ሲሆን ደግሞ እንደ ሰፌድና ማራገቢያ የሚመስሉ ቁሳቁስ እብቁ ይለያል፤ ጤፉን ከእብቁ ለመለየት እንደ ጥራጥሬው መንሽም ላይዳም ጥቅም ላይ አይወሉም። በሰፌድና በመሳሰሉት ነው ጤፉ ከእብቁ እንዲለይ የሚደረገው።

እንዲህ ባለው ባህላዊ መንገድ የደረሰው አዝመራ እየተሰበሰበ፣ እየተወቃ ነው ወደ ጎተራ እንዲገባ ሲደረግ የኖረው። አሰራሩ እጅግ ኋላ ቀር ነው፤ የሐገራችን ግብርና ስራ የግብርናውን ሥራ የሚያቀላጥፍ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ጊዜን በመቆጠብ፣ ድካምን በመቀነስ ተጠቃሚ ከሆኑ ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር በእርግጥም እጅግ ኋላቀር ሆኖ ቆይቷል።

ግብርናውን ከዚህ አይነቱ ኋላቀር አሰራር ለማውጣት በተለያዩ መንግስታት ሙከራዎች ተደርገዋል፤ በንጉሱ ዘመን በባለርስቶች ከዚያም በደርግ ዘመን የመንግስት እርሻ በባሌና አርሲ በትራክተር እና በኮምባይነር የታገዘ የሰፋፊ ግብርና ስራዎች ይካሄዱ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ።

የግብርና ሥራው በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ፣ ወንዝ በመጥለፍና ግድብ በመሥራት የመስኖ ልማትን ለማካሄድ ጥረቶች ተደርገዋል። በመስኖ ልማቱም ጎዴ መስኖ እርሻ፣ አልዌሮ መስኖ ግድብ፣ ጣና በለስ ፕሮጀክት፣ ከሰም መስኖ ግድብ፣ ተንዳሆ መስኖ ግድብ፣ ፈንታሌ ቦሰት መስኖ እርሻ፣ ወለጪቲ ቦፋ፣መገጭ፣ርብና ጊዳቦ መስኖ ግድብ፣ አርጆ ደዴሳ ግድብ፣ኩራዝ ፕሮጀክት፣ወልቃይት ወይንም ዛሬማ ግድብ ለመስኖ ልማት ለማዋል ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል።

ከእነዚህ ለመስኖ ልማት ከተዘጋጁ ግድቦች አብዛኞቹ ለስኳር ልማት የታቀዱ ነበሩ። አንዳንዶቹም ከአትክልት ልማት የዘለለ ብዙም ስራ ያልተሰራባቸው ናቸው። በእዚህ የተነሳም እቅዱ ወደ ሥራ ተተግብሮ እንደ ሀገር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በምግብ እህል ራስን ለመቻል የሚደረግ ጥረትን በማገዝ ይህ ነው የሚባል ለውጥ አልተመዘገበም።

የግብርና ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ለአርሶ አደሩ ለማስተዋወቅና ተጠቃሚ እንዲሆን ለማደረግም ተሞክሯል። የሕብረት ስራ ማህበራት፣ በግብራናው ስራቸው አንቱ ተብለው ተሸላሚ እስከመሆን የደረሱ አርሶ አደሮች የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ጥሩ ተነሳሽነት ቢያሳዩም፣ ግብርና አንደ ሀገር ከሚያስፈልገው ቴክኖሎጂ አኳያ ግን ብዙ ተሰርቷል የሚያሰኝ ሁነታ አልነበረም። በተለይ የግብርናው ዘርፍ ለሜካናይዜሽን ተግባር የሚያስፈልገውን የፋይናንስ አቅርቦት የሚቀርብበት ሁኔታ አልነበረም። ሀገሪቱም ለግብርናው ዘርፍ ፋይናንስ የማይቀርብባት ተብላም በባለሙያዎች ስትተች ኖራለች።

ከጥቂት አመታት ወዲህ ግን መንግስት ግብርናው ላይ በስፋት እየሰራ ይገኛል። ግብርናው በየአመቱ ምርትና ምርታማነቱ እያደገ ቢመጣም የሐገሪቱን ፍላጎት በማመቋላት በኩል ግን ብዙ እንደሚቀረው ታምኖበት እየተሰራ ነው። ውጤታማነቱ በሚገባ የተረጋገጠው የኩታ ገጠም እርሻ እየተስፋፋ ነው፤ የመስኖ እርሻ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ይገኛል።

ሜካናይዜሽን ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶታል። ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ ምርት እስከመሰብሰብ ያለው ሂደት በሜካናይዜሽን ወይም በትክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በመንግሥት በልዩ ትኩረት እየተሰራበት ነው።

በሀገሪቱ በመኸር አርሻም ሆነ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተሰፋፋ በመጣው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የግብርና ሜካናይዜሽን





እየተሰፋፋ ይገኛል። በትራክተር በማረስ፣ በኮምባይነር አዝመራ በመሰብሰብና በመውቃት የመስኖ ልማትን በስፋት በማከናወን በኩል ሀገሪቱ ታምር እያሳየች ትገኛለች። በአሁኑ ወቅት ግለሰቦችና ማህበራት የእነዚህ ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎች ባለቤት እየሆኑ ናቸው። መሳሪያዎቹ በኪራይ ጭምር ሊገኙ የሚችሉበትን ሁኔታም አነዚህ አካላት እያመቻቹ ይገኛሉ። በእዚህ የምርት ዘመን እየተመለከትን ያለውም ይህንኑ ነው።

በሀገሪቱ ግብርና ሜካናይዜሽን በአጠቃላይ፣ በእዚህ የምርት ዘመን በሜካናይዜሽን መሳሪያዎች እየተካሄደ ስላላው የግብርና ስራ በተለይ ያነጋገርናቸው በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ በረከት ፎርሲዶ እንዳሉት፤ የምርት ዘመኑ የመኸር ግብርና ሥራ ከፍተኛ የሆነ የመሬት ስፋት ለግብርና ሥራ የዋለበት ሲሆን፣በመደበኛ በዝናብ ወቅት ከሚከናወን የግብርና ሥራ በተጨማሪ በመስኖ ጭምር የልማቱ ሥራ የተጠናከረበት ነው። በቅድመ ዝግጅት ግብርና እና በድህረ ምርት አሰባሰብ ከፍተኛ የሆነ የቴክኖሎጂ ወይንም በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች የመጠቀም ፍላጎትም ታይቷል።

በተለይም ካለፉት ሶስት አመታት ወዲህ የግብርና ሜካናይዜሽን ፍላጎት እየጨመረና አቅርቦቱም እያደገ መጥቷል። በየግላቸው እንደ ትራክተር፣ ኮባይነር ሀርቨስት (ሰብል አጭዶ የሚወቃ መሣሪያ)፣ሌሎችም የግብርና ቴክኖሎጂ ገዝተው የኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ተፈጥረዋል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተናጠል አንድና ከዚያ በላይ የሜካናይዜሽን መሣሪያ ያላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች በማህበር ተደራጅተው በጋራ አቅም ፈጥረው አገልግሎቱን እንዲሰጡ በማስተባበር በተወጣው ሚና ከ270 በላይ የሆኑ አባላትን የያዘ ኢትዮጵያ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጭዎች ማህበር ተመስርቶ የተናበበ ሥራ እየተሰራ ነው፤ ይህም በዘርፉ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

አገልግሎት አቅራቢዎችም በየግላቸው አገልግሎት ሲሰጡ ያጋጥማቸው የነበረውን ችግርና ከመንግሥትም የሚፈልጉትን ድጋፍ ለማግኘት እንዳስቻላቸው በማህበር ተደራጅተው በጋራ መሥራት ከጀመሩ ወዲህ መገንዘብ ተችሏል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ለግብርናው ቅድመ ዝግጅት ሲያደርግ ከማህበሩ አባላት ጋር ቀድሞ ምክክር ያደርጋል።

ቅድመ ምክከሩም የአገልግሎት ጥራት እንዲጠበቅ የአሰራር ሥርአቱን ተከትለው እንዲያከናውኑ ለማስቻል ነው። ነዳጅ ለመቆጠብ ሲባልና በችኮላ በእርሻ ወቅት በሚያስፈልገው የጥልቀት መጠን መሬቱን ያለማረስ ሁኔታ እንዳይፈጠር፣ በሰብል መሰብሰብና መውቃት ወቅትም በተመሳሳይ በሚሰጠው የቴክኖሎጂ አገልግሎት በአግባቡ እንዲከናወን፣አገልግሎት ሰጭዎቹ ገቢ የሚያገኙት አርሶ አደሩ ምርታማነቱ ሲጨምር እንደሆነ፣አገልግሎታቸውም ወቅታዊ የዋጋ ሁኔታን ያገናዘበ እንዲሆን ሚኒስቴሩ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሰራል። ወጭ ቆጣቢ የሆነ አሰራር እንዲጠቀሙና የግብርና መሳሪያ አጠቃቀም ላይም ሥልጠናም ይሰጣል።

ምክክሩ አገልግሎት ተጠቃሚው አርሶ አደርም አገልግሎቱን ከማግኘቱ በፊት ማወቅ ስላለበት ቅድመሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖረው ይደረጋል ሲሉ አቶ በረከት ይጠቁማሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ በተለይም ስለቴክኖሎጂ አጠቃቀሙና የቴክኖሎጂውን ጥቅም በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው በመንግሥት በጀት በተለያዩ ፕሮግራሞች በሚደረግ ዝግጅት በአርሶ አደር ማሳ ላይ ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ ያለውን ሂደት የተግባር ትምህርት እንዲያገኝ ይደረጋል። ይህም የሚከናወነው ከክልሎች ጋር በመሆን ነው።እንዲህ ያለ ቅድመዝግጅት ችግሮችን ቀድሞ ለመፍታትና ሥራውንም የተቀላጠፈ ለማድረግ ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ ያልተቋረጠ ምክክር ይደረጋል።

በዚህ የምርት ዘመንም ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱን አቶ በረከት ይናገራሉ። በአሁኑ ጊዜ ከነዳጅና ከመለዋወጫ ዋጋ ጋር በተያያዘ የአገልግሎት ዋጋ ጭማሪ ስለሚኖር የተጋነነ ዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር በምክክር መድረክ መግባባት ላይ ተደርሶ ነው ወደ ሥራ የተገባው ሲሉ ይገልጻሉ። በተጨማሪም እንደ ሀገር ከፍተኛ ጭማሪ ያለው የምርት ዝግጅት በመደረጉ አገልግሎት ሰጭዎቹ በአንዱ አካባቢ ሥራቸውን እንዳጠናቀቁ ወደሌላው በመሄድ አገልግሎታቸውን እንዲያቀላጥፉ የማነቃቂያ ፕሮግራምም መካሄዱንም ይገልጻሉ።

አስቀድሞ ምርት በሚደርስበት ኦሮሚያ ክልል አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን ጠቅሰው፣ በመቀጠልም ወደ ደቡብ ክልል እንዲሄዱ መደረጉን ተናግረዋል። ከዝዋይ፣መቂ፣ቆሴ፣ስልጤ፣ሐዲያ፣ጉራጌ ይዘው ነው በክልሉ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ የሚገኙት። ወደ ሶማሌ ክልልም የሚንቀሳቀሱ አሉ ይላሉ።

ባለፈው ሳምንትም ሚኒስቴሩ የአገልግሎት ሰጪዎችን ተወካይ ወደ አማራ ክልል ይዞ በመሄድ በአካባቢው እንዲሰሩ የማነቃቂያ ሥራ መሰራቱን አስታውቀዋል። በዚህ መልኩ እየተሰራ ባለው የመኸር ሰብል አሰባሰብ በምርት ዘመኑ ወደ1800 ኮባይን ሀርቨስተር(ማጨጂያና መውቂያ ማሽን)፣በከፊል በአርሶአድር ጉልበት የተከናወነውን ሥራ የሚያግዝ 13ሺ የመውቂያ ማሽንም በሥራ ላይ መዋሉን አስታውቀዋል። በኪራይ አገልግሎት ከቀረቡት ከነዚህ ቴክኖሎጂዎች በተጨማሪ አርሶ አደሩ በራሱ አቅም አነስተኛ በሆኑ ማሽኖች በመጠቀም ጉልበቱንና ጊዜውን በመቆጠብ እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ።

በማህበራት ከሚቀርቡ አገልግሎቶች በተጨማሪ አቅም ያለው አርሶ አደርም የማረሻ፣ማጨጃና መውቂያ ቴክኖሎጂዎችን ለአካባቢው አርሶ አደር በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲያደርግ እየተሰራ መሆኑንም ነው አቶ በረከት የጠቀሱት። ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት የግብርና ቴክኖሎጂዎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና በማህበር ተደራጅተው አገልግሎት ከሚሰጡ በተገኘ መረጃ ላይ የተሰመሰረተ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

የግብርና ሜካናይዝሽን ቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት ይፈልጋል ያሉት አቶ በረከት፤የሥራ መሳሪያዎቹን በግብርና ሥራው ላይ ለማዋል በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ ሚኒስቴሩ ማሰልጠኛ ተቋም አቋቁሞ በአጭር ጊዜ ስልጠና ባለሙያዎች እያበቃ መሆኑንና በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛም በቴክኖክና ሙያ (ቲቤቲ) በደረጃ(ሌብል) እንዲሰለጥኑ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ግብርናው በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆነ አስረድተዋል።

ለግብርናው አገልግሎት የሚውለት መሳሪያዎች ከቀረጥ ነጻ ከውጭ እንዲገቡ፣በሀገር ውስጥ የተፈጠሩ አነስተኛ የቴክኖሎጂ አምራች ኢንዱስትሪዎችም የጥሬ ዕቃ ግብአት ከቀረጥ ነጻ ከውጭ እንዲያስገቡ በመንግሥት እንዲበረታቱ መደረጉ አጠቃቀሙ እንዲጨምር ካደረጉ ተግባራት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ የሰጠውን ትኩረት እንደሚያመለክት ተናግረዋል።

በግብርና ሜካናይዜሽን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚደረው ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ እንደሚኖረውና ተከታታይ ሥራም እንደሚያስፈልግ ይታመናል። አቶ በረከት ይህን አስመልክቶም ሲናገሩ በቴክኖሎጂ ታግዞ የተገኘውን ውጤት በቁጥር ለማስቀመጥ ጥናት ይፈልጋል ብለዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ካለው ነባራዊ ሁኔታ በሜካናይዜሽን በኩል መልካም ውጤቶች እየተመዘገቡ ናቸው። እንደ ሀገር ወደ 13 ሚሊየን ሄክታር መሬት ለግብርና ሥራ እየዋለ እንደሆነ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ወደ 75 በመቶ የሚሆነው ለሜካናይዜሽን የግብርና ሥራ ምቹ ነው። በቴክኖሎጂው በመጠቀም ቀደም ሲል በማምረት ሂደት ያጋጥም የነበረውን ወደ 30 በመቶ ብክነት ወደ አምስት በመቶ ለማውረድ በአስርአመት መሪ እቅድ ውስጥ ተካትቷል። ጥቅም ላይ እየዋለ ባለው ቴክኖሎጂ ብክነቱን በምን ያህል ማስቀረት እየተቻለ እንደሆነ የጥናት ሥራ ይፈልጋል።

በእስካሁኑ ሂደት ስለነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችም አቶ በረከት እንደገለጹት፤ በጠንካራ ጎን ከሚጠቀሰው አንዱ በግብርና አመራረት ላይ የአርሶ አደሩ ግንዛቤና የእውቀት ደረጃ ከፍ ብሏል። በግብርና ኤክስቴንሽን የሚሰጠውን ምክርና አገልግሎት በመጠቀም ገበያ ተኮር ምርት ለማቅረብ የሚያደርገውም ጥረት የሚሰጠውን ምክር ተግባር ላይ በማዋል እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ያሳያል። ለአብነትም በአማራ ክልል በክላስተር የአዘራር ዘዴ በመጠቀም እየተገኘ ያለው ውጤት ወይንም የምርት ቁመና አበረታች ነው። ደቡብ ጎንደር መተማና ቋራ አካባቢዎች ወደ 250ሺ ሄክታር በሚጠጋ መሬት ላይ አኩሪአተር ተመርቷል።

ይህም አግሮ ኢንደስትሪውን ወይንም አቀነባብሮ ለተጠቃሚው የሚያቀርበውን ኢንዱስትሪ ለመመገብ ታስቦ በአካባቢው የተጀመረ ልማት ነው። ልማቱ በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ለማስቻል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሰሞኑ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ሥፍራው ሄዶ ነበር። አገልግሎት ሰጪዎች ወደ ስፍራው በመሄድ አገልግሎት ለመስጠት ፍላጎት በማሳየታቸው በቅርቡ የደረሰውን የአኩሪ አተር እንደሚሰበስቡ ይጠበቃል።

ካላቸው የመሬት ስፋት ወይንም ከተነሳሽነትና ፍላጎት ጋር በተያያዘ የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀም አካባቢ ከአካባቢ ልዩነት ሊኖር ይችላል። በዚህ ላይም አቶ በረከት በሰጡት ማብራሪያ የሜካናይዜሽን አቅርቦቱ ተጠናክሮ ከመቀጠሉ በፊት ቀደም ሲልም ተሞክሮው ባለባቸው አካባቢዎች በተሻለ መንቀሳቀስ፣ፍላጎትም መጨመር ጋር ተያይዞ የስርጭት ከፍ ማለት በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍል ኦሮሚያ፣ደቡብ፣አማራ ክልሎች ይስተዋላል። አሁን ላይ በአርሶ አደሩ በኩል እየታየ ያለው ቴክኖሎጂውን የመጠቀም ፍላጎት ቴክኖሎጂውን ጥቅም ላይ የመዋል ተከታታይነት ያሳያል።

አርሶ አደሩ ቀደም ሲል መሬቱን አርሶ ለመከስከስ ብቻ ነበር ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ፍላጎት የነበረው ያሉት አቶ በረከት፣ በአሁኑ ጊዜ ግን በመስመር መዝራትን፣በሰው ጉልበት የሚካሄደውን የፀረተባይ መርጨት ስራን የመሳሰሉ ሰፋፊ ተግባሮችን የሚያከናወኑ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ነው። የበጋ መስኖ ልማት የአርሶ አደሩን በግብርና ሜካናይዜሽን የመጠቀም ፍላጎት እንዲጨምር አድርጎታል። በአርሶ አደሩ የተፈጠረው መነቃቃትና ከዝናብ ጥገኝነት ተላቅቆ አመቱን ሙሉ ለማምረት እንዲችል የቴክኖሎጂ አቅርቦቱ መጠናከር ይኖርበታል።

በግብርና ሜካናይዜሽን ታግዞ ስለተከናወነው የምርት አሰባሰብ ሁኔታ አቶ በረከት ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በየጊዜው ባለው የመረጃ መለዋወጥ ትክክለኛውን መረጃ ለማስቀመጥ እንደሚያዳግት ተናግረዋል። የመኸሩ ምርት መሰብሰብ ቢጀምርም በአብዛኛው ግን ከተያዘው ህዳር ወር ጀምሮ ነው የመሰብሰቡ ሥራ የሚጠናከረው ብለዋል።

የግብርና ሜካናይዜሽን ሥራውን ለማጠናከር በሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ዳይሬክቶረት ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከተገባ ከሰባት አመት በላይ እንደሆነው የጠቆሙት አቶ በረከት፣ የፖሊሲ ድጋፍ የሚፈልጉ ሥራዎችን ከተበጣጠሰ አሰራር በመውጣት በተጠናከረ መልኩ መሥራት ከጀመረ ግን ሶስት አመት እንደሆነው ይገልጻሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥም ከተቋማዊ አደረጃጀት ጀምሮ ለውጥ የታየባቸው ሥራዎችን ማየት ተችሏል ብለዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ቅሬታ ያልተለየው የመጽሃፍ ስርጭት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ወይዘሮ ሮዛ ሀብታሙ ይባላሉ። የመማርያ መጽሃፍት እጥረት የራስ ምታት ከሆነባቸው ወላጆች አንዷ ናቸው። በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው መፅሐፍ ለልጆቻቸው መድረስ ባለመቻሉ ብዙ ነገራቸው ተዛብቶባቸዋል። አንዱ ልጆቻቸውን ማገዝ አለመቻላቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ላልተገባ ወጪ መዳረጋቸው ነው። ልጃቸውን ማስጠናትም ሆነ የከበዳቸውን ትምህርት ማገዝ ያልቻሉት እንደሌላው ትምህርትቤት በሶፍት ኮፒ እንኳን መጻሐፍቱን ሳያገኙ መቆየታቸው ነው። አብዛኞቹ ትምህርትቤቶች መጻሐፍቱን በቴሌግራምና መሰል የማሰራጫ አማራጮች ለተማሪዎችና ለመምህራን ሰጥተው የመማር ማስተማሩ ሥራ እንዲሳለጥ ቢያደርጉም እርሳቸው ጋር ግን ይህ አልሆነም። በዚህም ልጆቻቸው የቤት ሥራ ለመስራት ቤት መጥተው የቸገራቸውን ሲጠይቋቸው ምንም ማለት አልቻሉም።

ከሳምንት በፊት በፍላሽ ውሰዱ የሚል መልእክት እንደደረሳቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ሮዛ፤ ትምህርትቤቱ ይህን ያደረገው ተማሪዎች ፈተና ሊወስዱ በመቃረባቸው የተነሳ ብቻ ነው። የይድረስ ይድረስ ስራ እንደተሰራም ይናገራሉ። እርሱም ቢሆን በፍላሽ መፅሐፉን ወስዳችሁ ፕሪንት አድርጉ እንጂ ምን ያህል ምዕራፍ እንደሆነ አይገልጽም። ይህ ደግሞ ወላጅን ኪሳራ ውስጥ መክተት ብቻ ሳይሆን ለማይጠቅም ነገር ወጪ ማውጣትንም ያስከትላል ። ምክንያቱም በአንድ የትምህርት አይነት ብቻ ከ140 በላይ ገጽ የሚባዛ ሲሆን፤ መጽሀፉ የሚቆይበት ጊዜ አጭር በመሆኑ ይጣላል። እናም ለወላጅም ሆነ ለተማሪ ማሰብ እንኳን ያልተቻለበት አሰራር እያዩ መሆኑን ይገልጻሉ።

ተማሪዎች መጽሀፉ በእጃቸው ስላልገባ ከዚህ ቀደም ከነበረው የበለጠ ከሞባይላቸው ጋር እንዲገናኙ እየሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ነገሮችን ከሞባይል ውጪ እንዳያደርጉ ያስገድዳቸዋል። ልምድ ይሆንባቸውና ወደአላስፈላጊ ተግባርም ሊገቡ ይችላሉ። ስለሆነም እንደ አገር ልጆችን መታደግ የሚቻለው በአፋጣኝ መጻሐፉቱ ታትመው እጃቸው ላይ ሲገባ ነውና ሁሉም ፈቃደኝነቱን ማሳየት እንዳለበት ያነሳሉ። እስከዚያ ደግሞ ትምህርትቤቶች አማራጭ መንገዶችን መጠቀም እንዳለባቸውም ይናገራሉ።

መጽሐፍትን አሳትሞ በፍጥነት የማድረስ ሥራ የመንግስት ብቻ ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት የሚናገሩት ወይዘሮ ሮዛ፤ የልጆቻችን ጉዳይ የእኛም ጉዳይ ነው። እናም የተቻለንን ሁሉ አድርገን ቋሚ የመማርያ መጽሐፍትን አሳትሞ ማሰራጨት ይገባናል። በተለይም አሳታሚዎች ፤ ማተሚያ ያላቸው ትምህርትቤቶች እንዲሁም ባለሀብቶች በዚህ ላይ ትብብር ቢያደርጉ ነገሮች ይቀላሉ። ወላጆችም ለማባዢያ የሚያወጡትን ወጪ ለዚህ ድጋፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ ቢመቻች ለልጆቻችን መድረስ እንችል ነበር ይላሉ።

የዳግማዊ ምኒልክ አንደኛ ደረጃና አጸደሕጻናት ትምህርትቤት ርዕሰመምህር አቶ ግሩም መዝገበ በበኩላቸው፤ የመጻሐፍ ህትመትና ስርጭት ጉዳይ የአንድ አካል ችግር ብቻ እንዳልሆነ ያነሳሉ። መጻሐፍት የመማር ማስተማሩን ስርዓት በብዙ መልኩ ያሳልጣሉ። ስለሆነም ቶሎ ታትመው ተማሪዎች ጋር መድረስ ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን የመማር ማስተማሩን ሥራ በብዙ መልኩ ያደናቅፈዋል። ጫና የሚፈጥርባቸው አካላትም ይፈጠራሉ። ለአብነት መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ወላጆች። ስለዚህ መጻህፍት የትምህርት የጀርባ አጥንት ናቸውና ችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሄን እንደሚሹ ያስረዳሉ።

እንደ ትምህርትቤት የመጻሐፍት ስርጭቱ ሌሎቹ በሚያሳስባቸው ልክ አይደለም። ምክንያቱም በትምህርት ቤቱ ሙሉ ለሙሉ የትምህርት አይነቶችን ማድረስ ባይቻልም የተወሰኑትን መጻሐፍት አንድ ለአንድ በሚባል ደረጃ ማድረስ ተችሏል። ያልደረሱትን የትምህርት አይነቶች ደግሞ በተማሪው ላይ እና በመምህራኑ እንዲሁም ወላጅ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ በሶፍት ኮፒ ለሁሉም ተደራሽ እየተደረገ

> **ከመጽሐፍት ስርጭትና ህትመት ጋር በተያያዘ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ እንደሚሉት፤ ምንም አይነት አዲስ ነገር በሚተገበርበት ጊዜ ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ አይሆንም። የመጽሐፍ ህትመትና ስርጭቱ ጉዳይም አንዳንድ ችግሮች የታየበት ከዚህ የተነሳ ነው። በዚያ ላይ እንደሚታወቀው በአገራችን በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ተማሪዎች የሚሆኑ መጸሐፍትን ለማተም ብቃት ያላቸው ተቋማት ብዙ አይደሉም**

ነው። አስፈላጊ ሲሆንም የማባዛትና ለተማሪዎች የማሰራጨት ሥራ ይሰራል። ማለትም ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሰሩ መጻሐፉን ፕሪንት በማድረግ ይሰጣል። በተለይ የምዕራፉ ማጠቃለያ ላይ ያሉ መልመጃዎችን ተማሪዎች በአግባቡ እንዲሰሯቸው ለማድረግ ብዙ ጥረቶች እንደሚደረጉ ይናገራሉ። መምህራን የቤት ሥራ ሲሰጡም ጥያቄዎችን በቦርድ ላይ ጽፈው ነው። ይህ ደግሞ በቴሌግራም መጻሐፍቱን ለማያገኙ ልጆች የሚያግዝ ነው።

ከመጽሐፍት ስርጭትና ህትመት ጋር በተያያዘ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ እንደሚሉት፤ ምንም አይነት አዲስ ነገር በሚተገበርበት ጊዜ ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ አይሆንም። የመጽሐፍ ህትመትና ስርጭቱ ጉዳይም አንዳንድ ችግሮች የታየበት ከዚህ የተነሳ ነው። በዚያ ላይ እንደሚታወቀው በአገራችን በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ተማሪዎች የሚሆኑ መጻሐፍትን ለማተም ብቃት ያላቸው ተቋማት ብዙ አይደሉም። ሁሉም ክልል ያሳትማል። ስለዚህም ችግሩ መፍትሄ እስኪያገን ድረስ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀ መጽሐፍ ዲጅታል በሆነ መንገድ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከዳታ ነጻ በሆነ መንገድ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያም እየተሠራ ነው።

የመጽሐፉ ስርጭት የክልሎች ኃላፊነት በመሆኑም የፋይናንስ፣ አሳታሚ ድርጅቶችን ያለማግኘትና በቶሎ የማድረስ ችግሮች እንደነበሩባቸው ያነሱት ሚኒስትሩ፤ ይህንን ችግር ለመፍታት በሚኒስቴሩ በኩል ድጋፍ እየተደረገ ነው። በዚህም ሁሉም በሚባል ደረጃ ወደ ህትመት መግባት ችለዋል። በቀጣይም ይህ ተጠናክሮ የሚሄድ ይሆናል ብለዋል።

ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ልክ እየተጓዙ እንደሆነ ራሳቸውን አብነት በማድረግ ያነሱልን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት፤ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ያስፈለገበት ምክንያት ተማሪዎች በሶስት መልኩ እንዲቀረጹ ነው። እነዚህም በአዕምሮ፣ በስነልቦናና በክህሎት እንዲዳብሩ ማድረግ የሚሉት ሲሆኑ፤ መጽሐፍቱ ይህንን ታሳቢ አድርገው ተዘጋጅተዋል። ዝግጅቱ ደግሞ ፈታኝና ብዙ ልፋትን የጠየቀ ነበር። ሆኖም በብዙ መልኩ ተስተካክሎ ለብዙዎች መድረስ ችሏል። ከአንዳንድ የትምህርት አይነቶች በስተቀር ተሰራጭቷልም።

አዲሱ ስርዓተ ትምህርት አዕምሮ፣ ልብና እጅን ያገናኘ እንዲሆን ለማስቻል የመጻሐፍ ዝግጅቱ ላይ ብዙ እንደተጨነቁበት የሚያነሱት ኃላፊው፤ መጀመሪያ አካባቢ የዩኒቨርስቲ መምህራን እንዲያዘጋጁት ጥረት ተደርጓል። ሆኖም በቢሊዬን የሚጠጋ ገንዘብ በመጠየቃቸው ትተውት በራስ ወደመሥራቱ ሂደት ገብተዋል። በዚህም በራስ አቅም መጠቀም ያለውን ዋጋ ያዩበት እንደነበር ያነሳሉ።

የመጻሐፍ ዝግጅቱ በራስ አቅም በመሰራቱ በብዙ ነገር እንደ ከተማ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን እንደአገርም ተጠቅመናል የሚሉት ዶክተር ዘላለም፤ የመጀመሪያው ወጪ ቅነሳ ነው። ወጪያችንን ማለትም አሁን የተቀየረው ስርዓተ ትምህርት ያኔ ሲዘጋጅ ከወጣው ወጪ በ57 ሚሊዬን ብር የቀነሰበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከዚያም በተጨማሪ ከኦሮምያና ከአማራ ክልል በስተቀር ብዙዎቹ ክልሎች የበጀት እጥረት ስላለባቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጀውን መጽሐፍ ወስደው እንዲጠቀሙ ሆነዋልና ለሌሎች አቅም በመሆን ሃብትን ማዳን ተችሏል። ሁለተኛው መምህራኑ ከሁሉም ክፍለከተሞች የተውጣጡና ምስጉን የተባሉ በመሆናቸው ችግሮች ሲኖሩ ወዲያው መፍትሄ እንዲሰጡበት ተደርጓል። ለማስተማርም ቀላልና ያልተረዱትን በቀላሉ ግልጽ ለማድረግ የሚያስችልበት ሁኔታን ፈጥሯል። በዚያ ላይ መምህራን ላይ አቅም መፍጠር ተችሏል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዘላለም ማብራሪያ፤ የመጻሐፍ ህትመትን በተመለከተ ግልጽ ጨረታ ወጥቶ ለስድስት አሳታሚ ድርጅቶች የተሰጠ ሲሆን፤ ጨረታው የአገር ውስጥ አሳታሚዎችን የያዘ ነው። ሆኖም አንዱ ድርጅት በጥሬ እቃው መወደድ የተነሳ በራሱ ውጪ በመውሰድ እንዲታተም አድርጓል። ይህ ደግሞ ኑ ህትመቱ ቢጠናቀቅም መጓጓዙ ጊዜ ስለሚወስድ እስካሁን መግባትና ማሰራጨት አልተቻለም። እስከ ህዳር 30 ድረስ ግን ይህ የሚጠናቀቅ ይሆናል። 80 በመቶ የሚሆነውን የመጻሐፍ ስርጭትም ይደረጋል።

የመጽሐፍ ዝግጅት ሥራው የተጀመረው በ2013 ዓ.ም እንደነበር የሚያስታውሱት ኃላፊው፤ በ2014ዓ.ም የመጽሐፍ ዝግጅቱ ለሙከራ በሚሆንበት ደረጃ በመጠናቀቁ በ44 ትምህርት ቤቶች ላይ ትግበራው እንዲጀመር ተደርጓል። ነሐሴ መጨረሻ ላይ ደግሞ ሁኔታዎች ተጠናቀቁና የመጻሐፍ ህትመት ጨረታ ተጀመረ። መስከረም መጨረሻም የጨረታ ሂደቱ አለቀ። እስከዚህ ወር መጨረሻ ድረስ ደግሞ መጻሐፍቱ ታትመው ይገባሉ። በከተማ አስተዳደሩ 3 ነጥብ 9 ሚሊዮን መጽሐፍት በኮፒ የተዘጋጀ ሲሆን፤ እስካለፈው ሰኞ ድረስ የነበረው መረጃ በየትምህርትቤቱ ወደ 1 ነጥብ 5 የሚደርሱ ኮፒ መሰራጨቱን ያስረዳሉ።

መጽሐፉ ያልደረሳቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሶፍት ኮፒ እንዲያገኙ በማድረግ ትምህርት እንዲጀምሩ ተደርጓል። ይህ ደግሞ ጫናው መምህራን ላይ የሚያርፍ ቢሆንም ለተማሪዎች ግን ብዙ ጥቅም እንደነበረው ማየት ተችሏል። አንዱ አዳምጠው የመጻፍ ክህሎታቸውን ያዳብሩበት ሲሆን፤ ሌላው አንዱ የትምህርት መስክ የሆነውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በስፋት እንዲተገብሩት እድል የሰጠበት ነው።

‹‹ስርዓተ ትምህርት ሁሌ ለትችት ቅርብ ነው። ሁሌ ይሻሻላል፤ ሁሌ አዳዲስ ነገሮች ይጨመርበታል። ስለዚህም ዘመኑን፣ ወቅቱንና አካባቢውን ለመዋጀት ሲባል ነገሮችን በአንዴ ወስኖ ወደትግበራው ለመግባት ፈታኝ ነው። ነገር ግን አሁንም መጻሐፍት ሁሌ ሀርድ ኮፒ መሆን አለበት ብለን አናስብም።›› የሚሉት ዶክተር ዘላለም፤ ስርዓተ ትምህርት በሰዓት፣ በቀናትና በወራት እንዲሁም በዓመታት ለውጦች የሚታይባቸው ናቸውና ለውጡን ተከትሎ መተግበር ግድ ነው። ስለዚህም አማራጮችን እያዩ መጠቀም ያስፈልጋልና ይህንን እንደሚከተሉ አስገንዝበዋል።

‹‹ትምህርትቤቶች የሚመስሉት መሪያቸውን ነው። ጥረት የታከለበት ትምህርትቤት በጥረቱ ልክ ወጥቶ ይታያል። ምንም ያልተሰራበት ደግሞ ድክመቶች ይበዙበታል›› የሚሉት ኃላፊው፤ ስለዚህም አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ውጤት እንዲያመጣ የሁሉም ወገን ድጋፍ ያስፍልገዋል ሲሉ መልዕክት ያስተላልፋሉ ።በመጻሐፍቱ ላይ ያሉ ችግሮችም ሆኑ የመጻሐፍቱ አለመዳረስ የአንድ አካል ችግር ሳይሆን የሁሉም ነውና ተረባርቦ መፍታት ላይ መተኮር አለበት። በተለይም አሁን የመጽሐፍት ህትመቱ እንደአገር የሚሰራ በመሆኑ ሁሉም ክልል በፍጥነት እንዲከናወንለት ይወተውታል እንጂ በፍጥነት ስራውን የሚያጠናቅቀው ጥቂት ነው። ምክንያቱም ሁሉንም የሚያስተናግድ የህትመት ተቋም እንደአገር የለም። ስለሆነም ማህበረሰቡ ይህንን ተገንዝቦ መታገስ እንዳለበትም ያነሳሉ።

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀድሞ ውል መያዙ ህትመቶች እየተጠናቀቁ እንዲመጡ አስችሏል። ከሌሎች ክልሎችም ተማሪዎችን ቀድመው ተጠቃሚ አድርጓል።

‹‹ ስርዓት በቁርጠኝነት የሚጠነክር ነው። አለዚያ ግን በግለሰብ ድክመት የሚገፋና የማይተገበር ከሆነ ብዙ ነገሮችን እንደአገር ያፋልሳል።›› የሚሉት ኃላፊው፤ በአዲሱ የትምህርት ስርዓት የስድስተኛና ስምንተኛ ክፍል ፈተና ይሰጣል ተብሏል። ነገር ግን መጽሐፉ ባለመድረሱና አማራጮች ባለመስፋታቸው የተነሳ ፈተናውን የማይሰጡ ክልሎች ይፈጠራሉ። እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግን ይህ ያጋጥማል የሚል ስጋት የለም። ምክንያቱም ትምህርት ሲጀመር ጀምሮ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው። ለአብነት ቅዳሜን ለተጨማሪ ትምህርት ማዋል ተጀምሯልም። መጻሐፍቱን በሚገባ እንዲረዱትና እንዲተገብሩት ደግሞ መጻሐፍቱ ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎች ጋር ሲደርስ ሙሉ ቀን የሚማሩበትን መንገድ ይመቻቻል። ከተቻለ እሁድንም ለመጠቀም እቅድ ተይዟል።

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁሉ ሌሎች ክልሎችም መጓዝ ከቻሉ የመጻሐፍ ጉዳይ የመማር ማስተማር ሥራውን ይፈትነዋል ተብሎ አይታሰብም።በቅርብ ቀናት ውስጥም ቀሪዎቹን መጽሃፍት ወደ ተማሪዎች ለማድረስ ስራዎችን እየተከናወኑ መሆኑን በመጠቆም የትምህርት ቢሮ ኃላፊው ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።

# ‹‹ደሃ ሆኖ በሰቆቃ ለመቀጠል አሊያም ሰርቶ ለመለወጥ የሚያስችል ዕድል በእጃችን አለ››

- አቶ ዑመር ሁሴን
የግብርና ሚኒስትር

አስቴር ኤልያስ

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የሰጡትን ማብራሪያ መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የግብርና ሚኒስትሩን አቶ ዑመር ሁሴንን ጋብዞ ያካሄደውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሴ

**አዲስ ዘመን፡- በ2014 ዓ.ም እንደ አገር 6 ነጥብ 4 በመቶ እድገት ተመዝግቧል፤ ቀጣይ እድገቱ 7 በመቶ እንደሚሆን ተገልጿል፤ ይህ እድገት ከምስራቅ አፍሪካ እና ከሰሃራ በታች ካሉ አገራት ትልቁ መሆኑ ተገልጿል። የዚህ እድገት አንድምታው ምንድን ነው? በእድገቱ ውስጥ የግብርና ዘርፍ ድርሻው እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ዑመር፡-** ዋናው ነገር ምን ትምህርት ተገኘበት የሚለው ነው፤ ከዛ ትምህርት አንጻር ለቀጣይ ምን መስራት እንደሚቻልም የታየበት ይመስለኛል ። የ2014 ዓ.ም አፈጻጸም ለእኔ የሚሰጠኝ ትርጉም አመራሩ ጠንካራ ሆኖ ጉዳዩን ይዞ መምራት እንደሚችል ነው ። የነበረው ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም በውስጥም ሆነ በውጭ የነበረው የኢኮኖሚ ጫና ባለበት ሁኔታ ውስጥ የአመራር አሰጣጥ ምን መሆን እንዳለበት ትምህርት የተገኘበት እና አንደምታውም ከዚህ በላይ የነበረው ሰላም ሲመለስ መስራት እንደሚቻል የሚያሳይ ነው ። ከዚህ በላይ ሰላም ሲመለስ መስራት እንደሚቻልም የሚያሳይ ነው።

ሁለተኛው የአገራችን ኢኮኖሚ የነበረውን ተጽዕኖ የመቋቋም አቅሙ ምን ያህል እንደሆነ የተፈተነበት ነው ። ሶስተኛ ደግሞ ኅብረተሰቡም ቢሆን በእንደዚህ አይነት ችግር ወቅት በቁጭት ተነሳስቶ ውጤታማ መሆን እንደሚችል ያሳየበት ነው ። ምክንያቱም ችግር ባለበት ወቅት ብዙ ነገር አለ ። የሚያስጨንቅ ነው ። ኅብረተሰቡ ድንጋጤ ባለበት እንዲሁም በቂ የፋይናንስ አቅርቦት እና ሌሎች የግብዓት አቅርቦቶች በሌሉበት ሁኔታ እንኳን አማራጭ በመፈለግ የማምረት ሒደቱ እንዳይቋረጥ ማድረግ መቻል ትልቅ ትምህርት የተወሰደበት ይመስለኛል ። እነዚህ እንድምታዎች እንዲህ አይነት ግፊት ባለበት ጊዜ ውስጥ በደንብ መስራት ከተቻለ በሌላ ወቅት ከዛ በላይ መስራት እንደሚቻል ያሳያል ። ይህ እንደ አጠቃላይ ሲታይ ነው ። ይህ ደግሞ የሚነሳው ከአስር ዓመቱ እቅድ ነው ። እንደገና የአስር ዓመቱ እቅድ ብቻ በቂ የማይሆንበት ጊዜ አለ፤ የዓለም ሁኔታ ተለዋዋጭ የሚሆንበት ሁኔታ ውስጥ ስላለን አንዳንድ ተጨማሪ የተፈጠረውን ነገር ሊቋቋም የሚችል አይነት እቅድ አገራዊ ፕሮግራሞችን ማስተዋወቅ መቻላችን ደግሞ በነበረው እቅድ ብቻ ሊሄዱ የማይችሉ ነገሮችን በተለየ ተነሳሽነቶች መውሰድ መቻላችን ችግሩን እንድንቋቋም በሁሉም ግንባር ኅብረተሰቡን ማሰለፍ መቻላችን ለዚህ አብቅቶናል ።

ወደግብርና ሚኒስቴር ስመለስ በግብርናው ሴክተር ያለፉትን ሁለት ሶስት ዓመታት ለዚህ እድገት የተደረገው አስተዋጽኦ በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን ። አንደኛው መንግስት ራሱ ለግብርናው ሴክተር ምን ማድረግ አለብኝ ብሎ በግልጽ የሰራቸውን ስራዎች ማየት ይቻላል ። ሁለተኛው ደግሞ ኅብረተሰቡ ያንን ወስዶ ወደ ምርት የቀየረበትን ሒደት ማየት እንችላለን።

ከመንግስት አንጻር ብዙ ድጋፎች ተደርገዋል። ከሁለት ሶስት ዓመት በፊት የግብርና ማምረቻ ማሽኖች እኩል እንደ ቅንጦት መኪናዎች ከውጭ የሚገቡበት እንዲሁም ታክስ የሚጠየቁበት ሁኔታ ነበር ። ለእነዚህ የታክስ እረፍት መስጠት፤ ባልተለመደ መንገድ ደግሞ የግብርና ግብዓቶችን በተለይ አምና ከማዳበሪያ ዋጋ ከፍ ማለት ጋር ድጎማ የመስጠት ሁኔታ ነበር ። ለመስኖ ስራዎች የተሰጡ ትኩረቶች፣ አገራዊ ፕሮግራሞችን ደግሞ ከፍ አድርጎ መምራት መቻል፣ አረንጓዴ አሻራና ሌሎች አገራዊ ፕሮግራሞችን በአግባቡ መምራት መቻላችን አሁን ለመጣው እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ነው የምለው ።

ዋናው ነገር በእንደዚህ አይነት ጫና ውስጥ ሆነን ይህን ማድረግ ከቻልን አገራችን ሰላም ሲሆን እንዲሁም አመራሩ ተረጋግቶ ከዚህ ትምህርት ወስዶ መምራት ከቻለ ምን መስራት ይቻላል በሚል ትልቁ ትምህርት መሆን የሚገባው ነው ። ለእኔ ይህ የሚሰጠኝ፤ ጫናዎች ቢኖሩም እድገቱ ከዚህ በላይም መሄድ እንደሚችልም እና ኢኮኖሚው ምን ያህል አስደንጋጭ ሁኔታዎችን መሸከም እንደሚችል ነው ። ይሁን እንጂ በዚህ መጽናናት የለብንም።

ካለው የአገር አቅም አንጻር ሲታይ ከዚህ በላይ ማምረት፣ የሰው እጅ አለማየትና ብዙ ነገር መስራት የሚችልበት አገር እንደሆነ ታይቷል ። ይህ ከመንግስት የተደረገው ነው፤ ከኅብረተሰቡ ደግሞ እውነት ለመናገር በዚህ መከራ ወቅት ኅብረተሰቡ ብዙ የሚያነሳቸው ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ ። ነገር ግን ያንን ተቋቁሞ ወደፊት መሄድ መቻል ትልቅ የሞራል መሰረት እንዳለ የሚያሳይ ነው ። በአንድ በኩል የነበረውን ግጭት ማኔጅ ማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ ያለውን ተጽዕኖ ከዚያም አልፎ ደግሞ በኤክስፖርት ጥሩ ነገር የታየበት ዓመት ነው። በኢንዱስትሪ ሚኒስትር የተጠቀሰው ከቡና ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የተሻገርንበት ዓመት ነው ። ይህ ሪኮርድ ነው ። ያገኘነው አንድ ነጥብ 42 ቢሊዮን ዶላር ነው ። ከዚህ በፊት 900 ሚሊዮን ዶላር ያለፍንበት ጊዜ አልነበረም ። ስለዚህ ከአንድ ሴክተር ያውም በአንድ በተወሰነ ምርት ይህን ውጤት ማምጣት ከቻልን ሌሎች ያሉንን እድሎች በአግባቡ መጠቀም ብንችል የት መድረስ እንደሚቻል የሚያሳይ ነው ። ስለዚህ እዚህ ላይ መረባረቡ ችግር ሲኖር ጥሩ ሰርተን፤ ችግር ሳይኖር ወደቦታችን የምንመለስ ሳይሆን ትምህርት ልንወስድበት የሚገባ ትልቅ እንድምታ ነው፤ ለኢትዮጵያ በተለይ ለምሁሩ ቴክኒካል ድጋፍ ለሚያደርጉ ሁሉ ትምህርት የሚወስዱበት ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የግብርና ምርታማነትን በተመለከተ እድገት መኖሩ ይነገራል፤ ከኑሮ ውድነት አንጻር ደግሞ የሚነሱ የሕዝብ ጥያቄዎች አሉ፤ ግብርናው ይህን ለማመጣጠን እንዴት አልቻለም፤ አሊያም ሌሎች ምክንያቶች ካሉ ቢጠቀስ?**

**አቶ ዑመር፡-** አሁን ንድፈሃሳብ ሳይሆን በተግባር መሬት ላይ ያለውን እና የተደረገውን ጥረት እንዲሁም ያለውን ክፍተት አይተን እሱ ላይ መስራት ነው ። የዋጋ ንረቱ እንደሆነ መኖሩ የሚታወቅ ነው ። ነገር ግን ለዋጋ ንረት አስተዋጽኦ ያደረገው ነገር አንድ ነገር ብቻ አይደለም። በጣም ብዙ ናቸው፤ ከዚያ ውስጥ በምርት አቅርቦት ላይ ያለውንና ከግብርና ሴክተር ጋር ያለውን ነገር ሳነሳ አንደኛው ለዋጋ ንረቱ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው በቂ ምርት ማቅረብ ነው ። በቂ ምርት የምንለው አሁን ስለምርት ስለምናወራ እንጂ አገልግሎት ላይም እንደዚያ ነው ። ሌሎቹም ሆኑ ከፋይናንሱ ዘርፍም እኩል መታየት አለባቸው ። እነዚህ ሁሉ ሲደማመሩ የዋጋ ንረቱ ላይ ስለሚታይ ሕዝቡ ላይ ጫና ሊፈጥር ይችላል ። ከምርት አቅርቦት አንጻር መነሻ ሊሆን የሚችለው በአስር ዓመት የተያዘው እቅድ ነው፤ ይህን ደግሞ ወደ አምስት ዓመት እንዲሁም ወደ አንድ ዓመት ከሚለው ላይ ነው ማየት የሚቻለው።

ከዚህ አንጻር ይመስለኛል በአስር ዓመት ከታቀደውና ወደዓመት ተከፍሎ ከተሰራው ጫና የበዛበት አገራዊ ሁኔታ ላይ ሆነንም ቢሆን እየተመረተ ነው ያለው። በምርቱ ስናይ አምና በ2014 የተከናወነውን ስለሆነ የምናገረው ካቀድነው ወደ 336 ሚሊዮን ኩንታል በዋና ዋና ሰብሎች የእቅዱን 90 በመቶ አካባቢ ፈጽመናል ። ይህ የሆነው አንዳንድ የአገራችን ክፍሎች ላይ ማምረት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን ሊመረትባቸው የሚችልባቸው አካባቢዎች በደንብ አሟጠን በመጠቀም ነው ይህ የመጣው ። በእንደዚህ አይነት አገር ብዙ ነገር በታነቀበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን እንኳን በአገር ውስጥ ያለው ችግር ከውጭ ለምርት ግብዓት የሚሆኑ በተለይ እንደ ማዳበሪያ አቅርቦት ያሉት በጣም ፈተና በሆኑበት ወቅት ውስጥ ሆነን ያንን ማሳካት መቻል በራሱ ጥሩ ነው። ነገር ግን በቂ ነው ማለት አይቻልም ። በቂ ስላልሆነም ነው ሌሎች አገራዊ ፕሮግራሞችን ጎን ለጎን ማስኬድ አስፈላጊ የሆነው።

አሁን በነበረው ሒደት በመኸር ከተመረተ በኋላ የተወሰኑ በመስኖ የሚለሙ ነገሮች ይኖራሉ። ሌላው የምንጠብቀው ዝናብ በመጠበቅ በልግ ላይ ነው። ከ90 በመቶ በላይ ይይዝ የነበረው ይህንን ነው። ይህን አካሄዳችንን እንቀይር ብለን መስኖ ላይ በጣም ትኩረት አድርገናል ። የተወሰኑ ለዋጋ ግሽበት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርገን እንስራ በሚል ዲዛይን ተደርጎ ወደ አስር የሚሆኑ አገራዊ ፕሮግራሞች ተመርጠው ከዚያ ውስጥ የስንዴው በአሁኑ ወቅት ጎልቶ ወጥቷል ። ነገር ግን እዛ ላይ የተያዘው ስንዴ ብቻ አይደለም ። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም ለፓርላማው ሲያነሱ እንደነበረው የሰሊጥ ምርት ላይ ትልቅ አቅም አለን። እዚያ አቅም ላይ ተነሳስተናል ። ይህ የተጀመረው አምና ነው ። አሁን ግን ስኬሉን የማስፋትና ከፍ ያለ ምርት በዛ በኩል ሊመጣ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጎ እየተሰራ ነው ያለው ። ሌሎች ደግሞ እስካሁን በአገራዊ እቅዱ ተይዘው ያልገባንባቸው፣ ለኒውትሬሽን የሚሆኑ፣ እንዲሁም ለውጭ ገበያ የሚሆኑ አሁን አብዛኛው ከውጭ የሚመጣውንም ገቢ ምርቶችን እና ለግሽበት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን የመተካት ይሁን በሒደት ደግሞ የስራ እድል ለመፍጠር የሚያስችሉት የእንስሳት ሀብት ውጤት የሆኑት ዘንድሮ በዶሮ ልማት፣ በወተት ልማት እና በሌሎችም በፓኬጅ አድርገን የጀመርናቸው አሉ፤ እነዚህ ደግሞ ማፍራት ላይ ሲደርሱ አሁን ያለው ሁኔታ እየተቀየረ ይሄዳል።

እንደ ግብርና ሚኒስቴር የዋጋ ግሽበት ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ምርቶች ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን ነው ። ይሁንና አላዳረስነንም ። ስንዴው ላይ ትኩረት መደረጉ አንድ እፎይታ ነው ። በተለይ ግብዓትን ከመተካት አንጻር በየዓመቱ አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጪ ወጥቶበት የሚገዛን ስንዴ መተካት እና ወደውጭ መላኩን መሞከር በራሱ ስኬት ነው ። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እዚህ ያለውን ችግር ይፈታዋል ማለት አይደለም ። እዚህ ያለውን ችግር ለመፍታት ከምርትም አንጻር ሌሎችንም በእኩል ማየት ይጠይቃል ። ነገር ግን እኩል ሆነው በአንዴ አይመጡም። ያ ሲሆን አሁን ያለው ሁኔታ ሊቀንስ ይችላል የሚል ነው ያለኝ ።

እንደ ሴክተር እነዚህ የመረጥናቸው ምርቶች በግብርናው ወይም የግብርና ምርቶችን ለዋጋ ግሽበት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ይቀርፋል የምንላቸው ናቸው። እንደ አገር ሲታቀድም ግብርናው ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦ ሊሸፍኑ የሚችሉ ናቸው ተብሎ ነው እየተሰራ ያለው ። በእርግጠኝነት ለተወሰነ ጊዜ አገራችን ሰላም ሆኖ በጀመርነው ቁርጠኝነት ከሄድን አሁን የምንለውን ነገር መቀየር እንችላለን ።

**አዲስዘመን፡- ከግብርና ምርቶች ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል እንደተነሳው በአገር ውስጥ የተለዩ ምርቶች አሉ፤ ወደ ኤክስፖርትነት ማደግ የሚችሉት እንዲሁም ከውጭ የሚገቡትን ማስቀረት ዓላማ ቢኖርም፤ ነገር ግን ከእርሻ መሳሪያ ጋር በተገናኘ ከኤክስፖርት ይልቅ በአገር ውስጥ ምርት የሚል**

# ወቅታዊ

**እቅድ ስምን አይያያዝም የሚሉ ጥያቄዎች** ይነሳሉ፤ ኤክስፖርት ለማድረግ የተያዘው እቅድ እንዴት ውጤታማ መሆን ይችላል?

አቶ ዑመር፡- በሁሉም ላይ የምናደርገው ርብርብ አራት ዓላማዎችን ማዕከል አድርገን ነው ። የመጀመሪያው ከውጭ የሚገባውን የመተካት ስራ ነው፤ ምክንያቱም እኛ እንደ አገር የምናመነጨው ዶላር ካለን አጠቃላይ የአገራዊ ምርት ምጥጥን አንጻር ሲታይ በጣም አናሳ ነው ። ይህ ሁሌ የሚነሳ ጉዳይ ነው ። ስለዚህ የዶላር እጥረት ያለበት አገር እንደገና ከውጭ በዶላር እቃ አስገብተን የተጣራ ከፍተኛ የንግድ ሚዛኑን ጠብቆ ሊሄድ የሚችልበት ነገር ሊያመጣ አይችልም ።

ስለዚህ በንጽጽር አቅም ያለውን ነገር ማምረት መቻል፤ ሲመረት ደግሞ ምርታማነትን በማሳደግና በዘመነ መንገድ ማድረግ መቻል ትልቅ ድርሻ አለው ። ስለዚህ የመጀመሪያው በሁሉም የምናየው መለኪያውም ሲመረጥ አንዱ አሁን የምንመርጠው አገራዊ ፕሮግራም አድርገን የምንይዛቸው ምርቶች ሌሎቹም ቢሆኑ በእቅዳቸው መሰረት ይሰራሉ፤ እውነት ከውጭ እየገባ ያለው ምርት የመተካት ድርሻቸው ከፍተኛ ነው ወይስ አይደለም? ስንዴንም ስናይ በመጀመሪያ ተነሳሽነቱ የመጣው ከሶስት ዓመት በፊት ነው ። አሁን የደረስንበት ቦታ የመኸሩንና የበጋውን መስኖ የምናለማውን አንድ ላይ ስናመጣ በአማካይ ከ25 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ወይም 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን በላይ ትርፍ ይኖረናል ። በጣም ወግ አጥባቂ ሆነን ብንይዝ ትርፍ የሆነው ምርት አገር ውስጥም ሊሸጥ ይችላል ። የአገርን ፍጆታ መጀመሪያ ሲወጣ የሚሸጠውንም የሚበላውን በማውጣት ነው ። አሁን ያለንበት ሁኔታ ያንን ይደርሳል ። ያ ከደረሰ በኋላ ደግሞ እጥረት ያለብንን ነገር ኤክስፖርት አድርገን ዶላር ማመንጨት፤ ከዚያ በላይ ደግሞ የኢትዮጵያን ገጽታ መቀየር፤ ይህ አገር ለ50 እና 60 ዓመት ስንዴ ከውጭ ሲያስገባ ያልተናገረ ሰው ዛሬ ኢትዮጵያ አስር ሚሊዮን፣ ሃያ ሚሊዮን ኩንታል ኤክስፖርት ስታደርግ ትችቱ መቅደም የለበትም ። በሌሎች ምርቶች ላይም ቢሆን ማበረታታ በእጥረት ውስጥም ሆኖ የሚደረግ ነው ። ያ ማለት ግን ኢትዮጵያውያን እየተራቡ ሊቀርብላቸው የሚገባ ነገር ሳይቀርብላቸው መሆን የለበትም ። የኢትዮጵያ ኤክስፖርት በአብዛኛው አሁን ማኑፋክቸሪንግ ያለው በተወሰነ ደረጃ ሆኖ ለዓመታት የተቀመጠው ከግብርና የተወሰኑ የገቢ ምንጭ ላይ ብቻ ነው ። ይህን ካላባዛን በስተቀር የኤክስፖርት አጠቃላይ አገራዊ ምርት (ጂዲፒ) ምጥጥን መጠበቅ አንችልም ። ስለዚህ ይህን ስናይ በአቮካዶ ማየት አለብን፤ ወደግሪን ሌጋሲው ስንገባ አቮካዶ ጥሩ ሆኖ እየመጣ ነው ። የሚቀረን የመሰረተ ልማት ስራው ነውና እሱን ማጠናከር አለብን ።

ስንዴ ላይ ተነሳሽነቱን ወስደን አቅማችንን መፈተሽ አለብን ። ትንሽ ዋጋ የሚያስከፍልም ቢሆን እሱ ያለ ነገር መሆኑን በመረዳት መስራት ነው ። ሌሎች ምርቶች ላይ ለምሳሌ አብዛኛው የወተት ምርት ስናይ በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን የቀንድ ከብት እንደያዘ አይነት አይደለንም ። ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ደግሞ ሰባት ስምንት ላይ ያመጣንን የከብት ብዛት ይዘን በቀን በአንዲት ላም 1 ነጥብ 5 ሊትር ወተት እያመረትን ከብት አለን እያልን እያወራን መኖር አንችልም ። ይህን ዝርያውን በማሻሻል ሌሎቹ እንዳደረጉት ከ15 እስከ ሃያ ሊትር ወተት በቀን ወደማግኘት መምጣት መቻል አለብን ። ይህ ካልሆነ ከውጭ የሚመጣውን የወተት ዱቄት ዶላር እያወጣንበት ልንኖር ነው ማለት ነው፡

ዋናው ነገር ትችት የሚታይበት አንግል ነው እንጂ መተቸት ሁልጊዜ ብቁ ለመሆን ያስችላል ። በእውቀት የተሞላ ትችት ከምሁሩም ሆነ ከሕዝቡ ከመጣ የተዘነጋ ነገር ካለ ለማየት የሚያስችል ነው ። ስለሆነም ትችቱ ያስፈልጋል ። ዋናው ግን መሆን ያለበት የሚያንጽና በባለሙያ የተነገረ ትችት ነው ። ምሁራኑ፣ ለሚደረገው ነገር አቃቂር ማውጣት ብቻ ከሆነ በቂ ነው ብዬ አልገምትም ። በጉዳዩ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግም ተገቢ ነው ። ልክ እንደ ምሁር በሚጎድለው ነገር ላይ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ መሄድ ያስፈልጋል ። ይህ ከሆነ አገሪቱን አንድ ርምጃ ወደፊት ለመውሰድ እድሉ አለ ።

በነገራችን ላይ ማየት ያለብን ነገር ብዙ ችግር ልናወራ እንችላለን፤ ዋናው ነገር ግን ይህ አገር ያለው አቅም ደግሞ በወጉ ለይተን አቅሙን የሚያወጣ አቅም መፍጠር ነው ። ለምሳሌ የሰው ኃይል፣ የአመራር፣ የፋይናንስ እንዲሁም የኤክስፐርቶች ማለት ነው ። እነዚህ ነገሮች አንድ ላይ መፈጠር መቻል አለባቸው ። መንግስት እንደሆነ በዚህ ጉዳይ ፈቃደኝነቱን አሳይቷል ። ሙያዊ ድጋፉን መጨመር ይፈልጋል ። የፋይናንስ ድጋፉንም መጨመር ይፈልጋል ። ይህ ውህድ አንድ ላይ መጥቶ ነው እነዚህ የምንላቸው ነገሮች ወደፊት ሊሄዱ የሚችሉት እንጂ አንዲት ምርት መዝዞ እሱ ላይ ዜና መስራት የኢትዮጵያን ሁኔታ ይቀይራል ብዬ አልገምትም ። ኢትዮጵያ ብዙ ነገር ያላት አገር ናት ። ከዛ አንጻር ቢታይ መልካም ነው ።

አዲስ ዘመን፡- በስንዴ ምርት ላይ በበጋ መስኖ የተያዘ እቅድ አለ? ይህን ለማሳካት በስጋት የተነሱ ጉዳዮች አሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ በቂ የሆነ የፓምፕ አቅርቦት የለም የሚል ነው ። ይህን ችግር ለመፍታት ምን እየተሰራ ነው?

አቶ ዑመር፡- መጀመሪያ ያሰብነው አምና የነበርንበት 680 ሺ. ሔክታር መሬት አካባቢ ነው ። ከዚህ ውስጥ የተመረተው ወደ 25 ሚሊዮን ኩንታል አካባቢ ነው ። ይህንን ከአንድ ሚሊዮን የተሻገረ ብናደርግ በሚል ከክልሎች ጋር ከተወያየን በኋላ የሰራነው እያንዳንዱን ውሳኔ የሚፈልገውን ነገር ለይተን አውጥተን ነው ። ውሃ ያላቸው ቦታዎች ምን ያህል ናቸው? ተጨማሪ ለሚኖረን መሬት ውሃ ከሌለን ምን አማራጭ እንጠቀም? የሚል የፓምፕ አቅርቦቱን ከዛ ጋር አያይዘን ዝርዝር ሰራን ። በዚህም ከ50 ሺ. በላይ ፓምፕ ለየን ። በአጠቃላይ የሚያስፈልገን ወደ 75 ሺ. ፓምፖች ነበር ። አንድ ፓምፕ አስርና አስራ አምስት ሔክታር መሬት የሚያለማ እንዳለ ሁሉ አንድ ፓምፕ ሶስትና አራት ሔክታር መሬት የሚያለማ አለ ። ስለዚህ ቀሪውን 25 ሺ. የተወሰነውን ከእኛ ተገዝቶ እንዲቀርብላቸው የተደረገ ሲሆን፣ ሌላውን ደግሞ ክልሎቹ እንዲገዙላቸው ያደረግን በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ይህ አቅርቦት ከ62 ሺ. ፓምፕ አልፏል ። በዚህ ሒደት ስራው ቀጥሏል ።

በአሁኑ ወቅት የተዘጋጀው መሬት ወደ 680 ሺ. ሔክታር ደርሷል። ይህ ማለት ከአንድ ሚሊዮኑ ውስጥ ማለት ነው ። ጠቅላላ እቅዳችን አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ነው ። ለአንድ ሚሊዮን የሚሆን በፊቱንም ቢሆን መሰረተ ልማት አለ ። አሁን ግን በተለይ በአጫጭር ጉድጓዶች ፓምፕ ተጠቅመን የምናለማው ወደ 300 ሺ. ሔክታር ይሆናል ። ይህ ሲደመርበት ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሔክታር ይሆናል፤ ይህ በሁለት ዙር የታቀደውን ስራ ብናሳካ አሁን ባለው ምርት በመስኖ በሔክታር ከ38 እስከ 40 ኩንታል በአማካይ ቢሆን ከ50 ሚሊዮን በላይ ነው የምንወስደው ። ስለዚህ ከዛ ውስጥ 25 በመቶውን እንኳ ወደኤክስፖርቱ ብናስብ 50 በመቶውን መኸሩ ላይ ባመረትነው ላይ ይጨመራል ። ዝግጅቶቹ ይህን ይመስላሉ ።

ትልቁ ፈተና ማዳበሪያ ላይ ያለው ነው ። እሱ እየፈተነንም ቢሆን በእጃችን የሌለ ነገር ነው፤ በተለይ ዩሪያ ፤ እሱ ላይ ርብርብ እያደረግንና እያስገባን ነው፤ እሱ ከተሳካ የታቀደውን ነገር ወደፊት መውሰድ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ ።

አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር የሚነሳብን ትልቁ ክፍተት ያለንን ንቅናቄ ተጠቅሞ ወደምንፈልገው የብልጽግና ጉዞ አለመሻገር ነው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይህ አገራዊ አቅም የመጠቀም ጥረቶች ተጀምረዋል ። የአገርን አቅም ተጠቅሞ ወደብልጽግና ለመሻገር የተጀማመሩ ስራዎች ምን ያህል ስኬት እየታየባቸው ናቸው? ቀጣይ አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው? ዘላቂ መዳረሻውስ ምንድን ነው?

አቶ ዑመር፡- ሁለት ነገርን አመዛዝኖ ማየት ተገቢ ነው፤ አንደኛ ከአገር አቅም አንጻር ሁሉን ነገር አንዴ መግፋት፤ ፋይናንሱ አስቀድሜ እንዳልኩት አመራሩ በእነዚህ ያልበቃን በመሆናችን ገና በእድገት ላይ ያለን አገር ስለሆንን አንዳንዴ አቅማችንን መጥነን ነገሮችን ከአገራዊ ጥቅም አንጻር ስንይዛቸው ውጤትም እየመጣበት ነው ። ለምሳሌ ለሌማት ትሩፋት አስተዋጽኦ አድርጓል ብዬ የምለው በስንዴ የሰራነውና የተገኘ ድል፣ በአረንጓዴ አሻራ የተሰራና እና የተገኘ ድል፣ ቡና ላይ ትኩረት አድርገን ስርዓቱን አስተካከለን ኤክስፖርት ላይ ያገኘነው ነገር ሊጠቀሱ የሚችሉና ልምድ ልናገኝባቸው የሚችሉ ናቸው ። ከዚህኛው አንጻር ሁለት ነገር በተለይ ከምግብና ስርዓተ ምግብ ደህንነት አንጻር መታየት አለበት ። ብዙ ጊዜ የምግብ ደህንነት ይነሳል፤ የስርዓተ ምግቡ ብዙ አይነሳም ።

አሁን የያዝናቸው በተለይ በወተት ልማት እንዲሁም በዶሮ ልማትና ሌሎች የእንስሳትና አሳ ተዋጽኦ የሆኑት ፕሮጀክቶች ከሌላው ከሰብሉ የተሻለ ኒውትሬሽን (አልሚነት ያለው ምግብ) ያላቸው ናቸው፤ እነዚህን ዝም ብለን የዋለሉ በማድረግ ሰብሉ ላይ ብቻ ለረጅም ዓመት ትኩረት አድርገናል ። ያ ደግሞ ያመጣው የእንስሰት ሀብቱ አለን ከማለት ያለፈ በእውነታ ደረጃ ከኤክስፖርት መተካት አንጻር እንዲሁም ለምግብና ስርዓተ ምግብ ደህንነት በቂ ነገር አለማግኘትን ነው ። የሚጠበቀውን ያህል አላመጣም ። ስለዚህ ግልጽ የሆነ፣ የሴክተሩን ባለሙያ ያሳተፈ አይነት ስራ እንስራ ብለን የተነሳን ሲሆን ይህ ስራም የተጀመረው ከዓመት በፊት ነው ።

ያደረግነው ነገር ለምርታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርገው በተለይ በእንስሳት ሀብቱ ካየን የዝርያ መሻሻል ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት 68 ዓመት እና ከዚያ በላይ ውስጥ ዝርያ መሻሻል ላይ ተሰርቶ እስካሁን ያለንበት አምስት በመቶ አልሞላም ። ይህ የሚታየው ካለን የእንስሳት ሀብት ቁጥር አንጻር ነው ። ስለዚህ ዝሪያውን ያላሻሻለውና ምርታማነትን ያላሻሻልነው የእንስሳ ቁጥር መያዝ ራሱ መጥፎ ባይሆንም ነገር ግን በቂ አይደለም ። ይህንን ስራ የሚለውጥ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት አለብን የሚለውን ጉዳይ አንዱ ነው ።

ያንን ማድረጋችን ወተት ልማት ላይ ዓለም ያስቀመጠውን ስታንዳርድ ለምሳሌ አንድ ሰው በዓመት በነፍስ ወከፍ ሊያገኝ የሚገባው 200 ሊትር የሚል አለ ። በዓመት ሲታይ ኢትዮጵያውያን ያለንበት ገና 60 እና 70 ሊትር አካባቢ ላይ ነው ።

ሁለተኛው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ከዶሮ ጋር ያለው ቅርርብ በዓላት ሲኖሩ ነው፤ በአልሚ ምግብነቱ ካለው አንጻር በስጋም ሆነ በእንቁላል ያለንበት ሁኔታ ቁጥሮች የሚያሳዩት ከአፍሪካ በአማካይ በብዙ ነገር የምናንስበት ሁኔታ መኖሩን ነው ። ለምን ቢባል የእኛ የሕዝብ ቁጥር ትልቅ ስለሆነም ጭምር ነው ። ያለው ምርት እንኳ ትልቅ ቢሆንም በነፍስወከፍ አንሶ ነው የሚገኘው ። ስለዚህ ይህንን ልንቀይር ይገባል ።

በማር ልማት ያለን አቅም፤ እንዲሁም የዓሳ ልማትና ሌሎችንም በአንድ ፓኬጅ ይዘን ባለፈው አገራዊ ፕሮግራም እንደተካሄደው የሌማት ትሩፋት ብለን እንደያዝነው አይነት ነው ። እኔ እንደሚገባኝ አጀንዳዎች የሚቀረጹት የሕብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና ለመጨመር፣ ኤክስፐርቱን ለማንቀሳቀስ እንደሆነ ነው ። ምክንያቱም በስራዎቻችን ዙሪያ ያለን መረዳት የተመጣጠነ አይደለምና ነው ። አሁን ያለበት ሞዴል የሆኑ ፋርሞች በሶስት ክልሎች ሰርተናል ። እሱን ወደሁሉም ክልሎች የማዳረስ ስራ እየሰራን ነው ያለነው ። ክልሎች አገራዊ ፕሮግራሙን ወደታች አውርደውታል ። በመጨረሻ ላይ የሚከፍለው ግን ቁጥር ነው ።

የወተት ልማት ለማምጣት እኛ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት አሁን ካለንበት ዓመታዊ ምርት 6 ነጥብ 9 ቢሊዮን አካባቢ ወደ 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ማምጣት ነው ። ይህ ማለት ዝርያ ላይ ፣ መኖ ላይ ፣ የእንስሳት ጤና ላይ ሰርተን እንጂ ዝም ብሎ የአንድን ላም ምርታማነት በአማካይ ከምትሰጥ ከ1 ነጥብ 5 ሊትር በአንዴ ወደ አምስትና ስድስት ማምጣት አይቻልም ። ይህን በአግባቡ እየሰራን ሲሆን፣ ከኋላ ያለውን ስራ ጨርሶ የሚመጣ ስራ እየሰራን ነው ። በአሁኑ ሰዓት ወደ ሕዝብ ወርደናል ። እርግጥ አሁን ላይ ብዙ ፈተና አለው ። ለምሳሌ አንዱ የግብዓት ፈተና ነው ። ዝርያ ለማሻሻል ሲታሰብ ልክ እንደ ማዳበሪያ የሚፈትነን ነገር አለ፤ ዝርያ ለማሻሻል ሲፈለግ ለምሳሌ በአገር ቤት የቦረና ዝሪያ አለ ። ነገር ግን የራሳችንን ላም ምርታማነቷን ለመጨመር የሚያስችል ግብዓት ከወጪ በዶላር የሚመጣ ነው ። እንደዚህ የተሳሰረ ነገር አለ ። ያንን ግን መንግስት ተረድቶ በጀት በመመደብም እየፈታው ከሄደ ተስፋ አደርጋለሁ የስራ እድል ፈጠራውም የገቢ ምርት መተካቱ ላይም እየተሻሻለ የሚሄድበት ነገር ይፈጠራል ። በአሁኑ ሰዓትም እየሰራን ያለነው ይህንን ቢሆንም ገና በጅምር ያለና ያልከፈለን ስራ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል ። ይሁንና የዛሬ ሶስትና አራት ዓመት ገደማ ምንም እንኳ ድካም የሚጠይቅ ቢሆንም ስለስኬታቸው እናወራለን ። የማቀርበው ጥሪ ቢኖር ሁሉም ግን የየበኩሉን ቁርጠኝነት ማሳየት እንዳለበት ነው ። ያዝ ለቀቅ ማድረግ ሳይሆን እስከ መጨረሻው ውጤት እስኪመጣ በመታገል መስራት ነው ።

አዲስ ዘመን፡- ኢንዱስትሪው ከግብርናው ጋር ቁርኝት አለው፤ የምርት ግብዓት ይፈልጋል፤ የጥሬ እቃ አቅርቦት ይፈልጋል ። ነገር ግን በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ለኢንዱስትሪዎች እየቀረበ ያለው የግብዓት አቅርቦት እንዴት ነው የሚገለጸው? ከዚህ አኳያ ኢንዱስትሪዎች የምርት እጥረት እንዳይገጥማቸው በግብርና ዘርፉ እየተከናወነ ያለው ተግባር ምንድን ነው? ለምሳሌ የዘይት ፋብሪካዎች የምርት እጥረት

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ



**እቅድ ለምን አይያያዝም የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፤ ኤክስፖርት ለማድረግ የተያዘው እቅድ እንዴት ውጤታማ መሆን ይችላል?**

**አቶ ዑመር፡-** በሁሉም ላይ የምናደርገው ርብርብ አራት ዓላማዎችን ማዕከል አድርገን ነው። የመጀመሪያው ከውጭ የሚገባውን የመተካት ስራ ነው፤ ምክንያቱም እኛ እንደ አገር የምናመነጨው ዶላር ካለን አጠቃላይ የአገራዊ ምርት ምጥጥን አንጻር ሲታይ በጣም አናሳ ነው። ይህ ሁሌ የሚነሳ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የዶላር እጥረት ያለበት አገር እንደገና ከውጭ በዶላር እቃ አስገብተን የተጣራ ከፍተኛ የንግድ ሚዛኑን ጠብቆ ሊሄድ የሚችልበት ነገር ሊያመጣ አይችልም።

ስለዚህ በንጽጽር አቅም ያለውን ነገር ማምረት መቻል፤ ሲመረት ደግሞ ምርታማነትን በማሳደግና በዘመነ መንገድ ማድረግ መቻል ትልቅ ድርሻ አለው። ስለዚህ የመጀመሪያው በሁሉም የምናየው መለኪያውም ሲመረጥ አንዱ አሁን የምንመርጠው አገራዊ ፕሮግራም አድርገን የምንይዛቸው ምርቶች ሌሎቹም ቢሆኑ በእቅዳቸው መሰረት ይሰራሉ፤ እውነት ከውጭ እየገባ ያለው ምርት የመተካት ድርሻቸው ከፍተኛ ነው ወይስ አይደለም? ስንዴንም ስናይ በመጀመሪያ ተነሳሽነቱ የመጣው ከሶስት ዓመት በፊት ነው። አሁን የደረስንበት ቦታ የመኸሩንና የበጋውን መስኖ የምናለማውን አንድ ላይ ስናመጣ በአማካይ ከ25 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ወይም 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን በላይ ትርፍ ይኖረናል። በጣም ወግ አጥባቂ ሆነን ብንይዝ ትርፍ የሆነው ምርት አገር ውስጥም ሊሸጥ ይችላል። የአገርን ፍጆታ መጀመሪያ ሲወጣ የሚሸጠውንም የሚበላውን በማውጣት ነው። አሁን ያለንበት ሁኔታ ያንን ይደርሳል። ያ ከደረሰ በኋላ ደግሞ እጥረት ያለብንን ነገር ኤክስፖርት አድርገን ዶላር ማመንጨት፤ ከዚያ በላይ ደግሞ የኢትዮጵያን ገጽታ መቀየር፤ ይህ አገር ለ50 እና 60 ዓመት ስንዴ ከውጭ ሲያስገባ ያልተናገረ ሰው ዛሬ ኢትዮጵያ አስር ሚሊዮን፣ ሃያ ሚሊዮን ኩንታል ኤክስፖርት ስታደርግ ትችቱ መቅደም የለበትም። በሌሎች ምርቶች ላይም ቢሆን ማበረታታ በእጥረት ውስጥም ሆኖ የሚደረግ ነው። ያ ማለት ግን ኢትዮጵያውያን እየተራቡ ሊቀርብላቸው የሚገባ ነገር ሳይቀርብላቸው መሆን የለበትም። የኢትዮጵያ ኤክስፖርት በአብዛኛው አሁን ማኑፋክቸሪንግ ያለው በተወሰነ ደረጃ ሆኖ ለዓመታት የተቀመጠው ከግብርና የተወሰኑ የገቢ ምንጭ ላይ ብቻ ነው። ይህን ካላባዛን በስተቀር የኤክስፖርት አጠቃላይ አገራዊ ምርት (ጂዲፒ) ምጥጥን መጠበቅ አንችልም። ስለዚህ ይህን ስናይ በአቮካዶ ማየት አለብን፤ ወደግሪን ሌጋሲው ስንገባ አቮካዶ ጥሩ ሆኖ እየመጣ ነው። የሚቀረን የመሰረተ ልማት ስራው ነውና እሱን ማጠናከር አለብን።

ስንዴ ላይ ተነሳሽነቱን ወስደን አቅማችንን መፈተሽ አለብን። ትንሽ ዋጋ የሚያስከፍልም ቢሆን እሱ ያለ ነገር መሆኑን በመረዳት መስራት ነው። ሌሎች ምርቶች ላይ ለምሳሌ አብዛኛው የወተት ምርት ስናይ በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን የቀንድ ከብት እንደያዘ አይነት አይደለንም። ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ደግሞ ሰባት ስምንት ላይ ያመጣንን የከብት ብዛት ይዘን በቀን በአንዲት ላም 1 ነጥብ 5 ሊትር ወተት እያመረትን ከብት አለን እያልን እያወራን መኖር አንችልም። ይህን ዝርያውን በማሻሻል ሌሎቹ እንዳደረጉት ከ15 እስከ ሃያ ሊትር ወተት በቀን ወደማግኘት መምጣት መቻል አለብን። ይህ ካልሆነ ከውጭ የሚመጣውን የወተት ዱቄት ዶላር እያወጣንበት ልንኖር ነው ማለት ነው፡

ዋናው ነገር ትችት የሚታይበት አንግል ነው እንጂ መተቸት ሁልጊዜ ብቁ ለመሆን ያስችላል። በእውቀት የተሞላ ትችት ከምሁሩም ሆነ ከሕዝቡ ከመጣ የተዘነጋ ነገር ካለ ለማየት የሚያስችል ነው። ስለሆነም ትችቱ ያስፈልጋል። ዋናው ግን መሆን ያለበት የሚያንጽና በባለሙያ የተነገረ ትችት ነው። ምሁራኑ፣ ለሚደረገው ነገር አቃቂር ማውጣት ብቻ ከሆነ በቂ ነው ብዬ አልገምትም። በጉዳዩ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግም ተገቢ ነው። ልክ እንደ ምሁር በሚጎድለው ነገር ላይ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ መሄድ ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ አገሪቱን አንድ ርምጃ ወደፊት ለመውሰድ እድሉ አለ።

በነገራችን ላይ ማየት ያለብን ነገር ብዙ ችግር ልናወራ እንችላለን፤ ዋናው ነገር ግን ይህ አገር ያለው አቅም ደግሞ በወጉ ለይተን አቅሙን የሚያወጣ አቅም መፍጠር ነው። ለምሳሌ የሰው ኃይል፣ የአመራር፣ የፋይናንስ እንዲሁም የኤክስፐርቶች ማለት ነው። እነዚህ ነገሮች አንድ ላይ መፈጠር መቻል አለባቸው። መንግስት እንደሆነ በዚህ ጉዳይ ፈቃደኝነቱን አሳይቷል። ሙያዊ ድጋፉን መጨመር ይፈልጋል። የፋይናንስ ድጋፉንም መጨመር ይፈልጋል። ይህ ውህድ አንድ ላይ መጥቶ ነው እነዚህ የምንላቸው ነገሮች ወደፊት ሊሄዱ የሚችሉት እንጂ አንዲት ምርት መዝዞ እሱ ላይ ዜና መስራት የኢትዮጵያን ሁኔታ ይቀይራል ብዬ አልገምትም። ኢትዮጵያ ብዙ ነገር ያላት አገር ናት። ከዛ አንጻር ቢታይ መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በስንዴ ምርት ላይ በበጋ መስኖ የተያዘ እቅድ አለ? ይህን ለማሳካት በስጋት የተነሱ ጉዳዮች አሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ በቂ የሆነ የፓምፕ አቅርቦት የለም የሚል ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ዑመር፡-** መጀመሪያ ያሰብነው አምና የነበርንበት 680 ሺ ሔክታር መሬት አካባቢ ነው። ከዚህ ውስጥ የተመረተው ወደ 25 ሚሊዮን ኩንታል አካባቢ ነው። ይህንን ከአንድ ሚሊዮን የተሻገረ ብናደርግ በሚል ከክልሎች ጋር ከተወያየን በኋላ የሰራነው እያንዳንዱን ውሳኔ የሚፈልገውን ነገር ለይተን አውጥተን ነው። ውሃ ያላቸው ቦታዎች ምን ያህል ናቸው? ተጨማሪ ለሚኖረን መሬት ውሃ ከሌለን ምን አማራጭ እንጠቀም? የሚል የፓምፕ አቅርቦቱን ከዛ ጋር አያይዘን ዝርዝር ሰራን። በዚህም ከ50 ሺ በላይ ፓምፕ ለየን። በአጠቃላይ የሚያስፈልገን ወደ 75 ሺ ፓምፖች ነበር። አንድ ፓምፕ አስርና አስራ አምስት ሔክታር መሬት የሚያለማ እንዳለ ሁሉ አንድ ፓምፕ ሶስትና አራት ሔክታር መሬት የሚያለማ አለ። ስለዚህ ቀሪውን 25 ሺ የተወሰነውን ከእኛ ተገዝቶ እንዲቀርብላቸው የተደረገ ሲሆን፣ ሌላውን ደግሞ ክልሎቹ እንዲገዙላቸው ያደረግን በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ይህ አቅርቦት ከ62 ሺ ፓምፕ አልፏል። በዚህ ሒደት ስራው ቀጥሏል።

በአሁኑ ወቅት የተዘጋጀው መሬት ወደ 680 ሺ ሔክታር ደርሷል። ይህ ማለት ከአንድ ሚሊዮኑ ውስጥ ማለት ነው። ጠቅላላ እቅዳችን አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ነው። ለአንድ ሚሊዮን የሚሆን በፊቱንም ቢሆን መሰረተ ልማት አለ። አሁን ግን በተለይ በአጫጭር ጉድጓዶች ፓምፕ ተጠቅመን የምናለማው ወደ 300 ሺ ሔክታር ይሆናል። ይህ ሲደመርበት ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሔክታር ይሆናል፤ ይህ በሁለት ዙር የታቀደውን ስራ ብናሳካ አሁን ባለው ምርት በመስኖ በሔክታር ከ38 እስከ 40 ኩንታል በአማካይ ቢሆን ከ50 ሚሊዮን በላይ ነው የምንወስደው። ስለዚህ ከዛ ውስጥ 25 በመቶውን እንኳ ወደኤክስፖርቱ ብናስብ 50 በመቶውን መኸሩ ላይ ባመረትነው ላይ ይጨመራል። ዝግጅቶቹ ይህን ይመስላሉ።

ትልቁ ፈተና ማዳበሪያ ላይ ያለው ነው። እሱ እየፈተነንም ቢሆን በእጃችን የሌለ ነገር ነው፤ በተለይ ዩሪያ ፤ እሱ ላይ ርብርብ እያደረግንና እያስገባን ነው፤ እሱ ከተሳካ የታቀደውን ነገር ወደፊት መውሰድ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር የሚነሳብን ትልቁ ክፍተት ያለንን ንቅናቄ ተጠቅሞ ወደምንፈልገው የብልጽግና ጉዞ አለመሻገር ነው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይህ አገራዊ አቅም የመጠቀም ጥረቶች ተጀምረዋል። የአገርን አቅም ተጠቅሞ ወደብልጽግና ለመሻገር የተጀማመሩ ስራዎች ምን ያህል ስኬት እየታየባቸው ናቸው? ቀጣይ አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው? ዘላቂ መዳረሻውስ ምንድን ነው?**

**አቶ ዑመር፡-** ሁለት ነገርን አመዛዝኖ ማየት ተገቢ ነው፤ አንደኛ ከአገር አቅም አንጻር ሁሉን ነገር አንዴ መግፋት፤ ፋይናንሱ አስቀድሜ እንዳልኩት አመራሩ በእነዚህ ያልበቃን በመሆናችን ገና በእድገት ላይ ያለን አገር ስለሆንን አንዳንዴ አቅማችንን መጥነን ነገሮችን ከአገራዊ ጥቅም አንጻር ስንይዛቸው ውጤትም እየመጣበት ነው። ለምሳሌ ለሌማት ትሩፋት አስተዋጽኦ አድርጓል ብዬ የምለው በስንዴ የሰራነውና የተገኘ ድል፣ በአረንጓዴ አሻራ የተሰራና እና የተገኘ ድል፣ ቡና ላይ ትኩረት አድርገን ስርዓቱን አስተካከለን ኤክስፖርት ላይ ያገኘነው ነገር ሊጠቀሱ የሚችሉና ልምድ ልናገኝባቸው የሚችሉ ናቸው። ከዚህኛው አንጻር ሁለት ነገር በተለይ ከምግብና ስርዓተ ምግብ ደህንነት አንጻር መታየት አለበት። ብዙ ጊዜ የምግብ ደህንነት ይነሳል፤ የስርዓተ ምግቡ ብዙ አይነሳም።

አሁን የያዝናቸው በተለይ በወተት ልማት እንዲሁም በዶሮ ልማትና ሌሎች የእንስሳትና አሳ ተዋጽኦ የሆኑት ፕሮጀክቶች ከሌላው ከሰብሉ የተሻለ ኒውትሬሽን (አልሚነት ያለው ምግብ) ያላቸው ናቸው፤ እነዚህን ዝም ብለን የዋለሉ በማድረግ ሰብሉ ላይ ብቻ ለረጅም ዓመት ትኩረት አድርገናል። ያ ደግሞ ያመጣው የእንስሰት ሀብቱ አለን ከማለት ያለፈ በእውነታ ደረጃ ከኤክስፖርት መተካት አንጻር እንዲሁም ለምግብና ስርዓተ ምግብ ደህንነት በቂ ነገር አለማግኘትን ነው። የሚጠበቀውን ያህል አላመጣም። ስለዚህ ግልጽ የሆነ፣ የሴክተሩን ባለሙያ ያሳተፈ አይነት ስራ እንስራ ብለን የተነሳን ሲሆን ይህ ስራም የተጀመረው ከዓመት በፊት ነው።

ያደረግነው ነገር ለምርታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርገው በተለይ በእንስሳት ሀብቱ ካየን የዝርያ መሻሻል ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት 68 ዓመት እና ከዚያ በላይ ውስጥ ዝርያ መሻሻል ላይ ተሰርቶ እስካሁን ያለንበት አምስት በመቶ አልሞላም። ይህ የሚታየው ካለን የእንስሳት ሀብት ቁጥር አንጻር ነው። ስለዚህ ዝሪያውን ያላሻሻለውና ምርታማነትን ያላሻሻልነው የእንስሳ ቁጥር መያዝ ራሱ መጥፎ ባይሆንም ነገር ግን በቂ አይደለም። ይህንን ስራ የሚለውጥ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት አለብን የሚለውን ጉዳይ አንዱ ነው።

ያንን ማድረጋችን ወተት ልማት ላይ ዓለም ያስቀመጠውን ስታንዳርድ ለምሳሌ አንድ ሰው በዓመት በነፍስ ወከፍ ሊያገኝ የሚገባው 200 ሊትር የሚል አለ። በዓመት ሲታይ ኢትዮጵያውያን ያለንበት ገና 60 እና 70 ሊትር አካባቢ ላይ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ከዶሮ ጋር ያለው ቅርርብ በዓላት ሲኖሩ ነው፤ በአልሚ ምግብነቱ ካለው አንጻር በስጋም ሆነ በእንቁላል ያለንበት ሁኔታ ቁጥሮች የሚያሳዩት ከአፍሪካ በአማካይ በብዙ ነገር የምናንስበት ሁኔታ መኖሩን ነው። ለምን ቢባል የእኛ የሕዝብ ቁጥር ትልቅ ስለሆነም ጭምር ነው። ያለው ምርት እንኳ ትልቅ ቢሆንም በነፍስወከፍ አንሶ ነው የሚገኘው። ስለዚህ ይህንን ልንቀይር ይገባል።

በማር ልማት ያለን አቅም፤ እንዲሁም የዓሳ ልማትና ሌሎችንም በአንድ ፓኬጅ ይዘን ባለፈው አገራዊ ፕሮግራም እንደተካሄደው የሌማት ትሩፋት ብለን እንደያዝነው አይነት ነው። እኔ እንደሚገባኝ አጀንዳዎች የሚቀረጹት የሕብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና ለመጨመር፣ ኤክስፐርቱን ለማንቀሳቀስ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በስራዎቻችን ዙሪያ ያለን መረዳት የተመጣጠነ አይደለምና ነው። አሁን ያለበት ሞዴል የሆኑ ፋርሞች በሶስት ክልሎች ሰርተናል። እሱን ወደሁሉም ክልሎች የማዳረስ ስራ እየሰራን ነው ያለነው። ክልሎች አገራዊ ፕሮግራሙን ወደታች አውርደውታል። በመጨረሻ ላይ የሚከፍለው ግን ቁጥር ነው።

የወተት ልማት ለማምጣት እኛ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት አሁን ካለንበት ዓመታዊ ምርት 6 ነጥብ 9 ቢሊዮን አካባቢ ወደ 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ማምጣት ነው። ይህ ማለት ዝርያ ላይ ፣ መኖ ላይ ፣ የእንስሳት ጤና ላይ ሰርተን እንጂ ዝም ብሎ የአንድን ላም ምርታማነት በአማካይ ከምትሰጥ ከ1 ነጥብ 5 ሊትር በአንዴ ወደ አምስትና ስድስት ማምጣት አይቻልም። ይህን በአግባቡ እየሰራን ሲሆን፣ ከኋላ ያለውን ስራ ጨርሶ የሚመጣ ስራ እየሰራን ነው። በአሁኑ ሰዓት ወደ ሕዝብ ወርደናል። እርግጥ አሁን ላይ ብዙ ፈተና አለው። ለምሳሌ አንዱ የግብዓት ፈተና ነው። ዝርያ ለማሻሻል ሲታሰብ ልክ እንደ ማዳበሪያ የሚፈትነን ነገር አለ፤ ዝርያ ለማሻሻል ሲፈለግ ለምሳሌ በአገር ቤት የቦረና ዝሪያ አለ። ነገር ግን የራሳችንን ላም ምርታማነቷን ለመጨመር የሚያስችል ግብዓት ከወጪ በዶላር የሚመጣ ነው። እንደዚህ የተሳሰረ ነገር አለ። ያንን ግን መንግስት ተረድቶ በጀት በመመደብም እየፈታው ከሄደ ተስፋ አደርጋለሁ የስራ እድል ፈጠራውም የገቢ ምርት መተካቱ ላይም እየተሻሻለ የሚሄድበት ነገር ይፈጠራል። በአሁኑ ሰዓትም እየሰራን ያለነው ይህንን ቢሆንም ገና በጅምር ያለና ያልከፈለን ስራ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። ይሁንና የዛሬ ሶስትና አራት ዓመት ገደማ ምንም እንኳ ድካም የሚጠይቅ ቢሆንም ስለስኬታቸው እናወራለን። የማቀርበው ጥሪ ቢኖር ሁሉም ግን የየበኩሉን ቁርጠኝነት ማሳየት እንዳለበት ነው። ያዝ ለቀቅ ማድረግ ሳይሆን እስከ መጨረሻው ውጤት እስኪመጣ በመታገል መስራት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢንዱስትሪው ከግብርናው ጋር ቁርኝት አለው፤ የምርት ግብዓት ይፈልጋል፤ የጥሬ እቃ አቅርቦት ይፈልጋል። ነገር ግን በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ለኢንዱስትሪዎች እየቀረበ ያለው የግብዓት አቅርቦት እንዴት ነው የሚገለጸው? ከዚህ አኳያ ኢንዱስትሪዎች የምርት እጥረት እንዳይገጥማቸው በግብርና ዘርፉ እየተከናወነ ያለው ተግባር ምንድን ነው? ለምሳሌ የዘይት ፋብሪካዎች የምርት እጥረት እንደሚያጋጥማቸው ስለሚነገርም ከዚህ አንጻር ግብርናው ምን ያህል ኢንዱስትሪውን እየደገፈው ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ዑመር፡-** አስቀድመን ያነሳነው የኤክስፖርት ጉዳይ እና ሌሎች ነገሮችም ሊመጡ የሚችሉት በመጀመሪያ በአገር ውስጥ ጉዳይ ያለውን ፍላጎት ማሟላት ሲቻል ነው። የአገር ውስጥ ፍላጎት አንዱ አካል የሆነው ደግሞ የኢንዱስትሪው የግብዓት ፍላጎት ነው። የኢንዱስትሪው የግብዓት ፍላጎቱ ከግብርና ምርቶች ላይ ብቻ አይመስለኝም። ሌሎች ግብዓቶችንም ይፈልጋል። ነገር ግን ከግብርና አንጻር እያደረግን ያለነው ሁለት ነገር ነው። አንዱ በጋራ የማቀድ ጉዳይ ነው። ኢንዱስትሪው የሚፈልገው ምንድን ነው? የአስር ዓመቱ እቅድ ላይም ተመላክቷል፡፤ ከዚያ ላይ የዓመትም ስናቅድ በጋራ ማቀድ ነው። እናም ኢንዱስትሪው ከግብርናው በዓመት የሚፈልገውን ነገር የማወቅ ስራ ነው የምንሰራው። ይህ ማለት ከቦታ ቦታና ከምርት ምርት ይለያያል እንጂ ሁሉም ምርቶች ላይ አይደለም። ለምሳሌ ስንዴ ላይ የነበረው

«ደሃ ሆኖ በሰቆቃ ለመቀጠል ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ዓለም አቀፍ



## ለ43 ዓመታት ኢኳቶሪያል ጊኒን የመሩት ፕሬዚዳንት ለስድስተኛ ጊዜ አሸነፉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በዓለም ላይ በመሪነት ለረዥም ዓመታት በስልጣን ላይ በመቆየት የቁንጮነቱን ስፍራ የተቆናጠጡት የኢኳቶሪያል ጊኒው ፕሬዚዳንት አምባገነናዊ አገዛዛቸውን ማስቀጠል የሚያስችላቸውን ምርጫ አሸንፉ።

የ80 ዓመቱ ፕሬዚዳንት ቴዎዶሮ ኦቢያንግ ንጌማ ምባሶጎ 95 በመቶ የሚጠጋ ድምጽ ማግኘታቸውን ባለስልጣናቱ ከምርጫው ከስድስት ቀናት በኋላ አስታውቀዋል።

የፕሬዚዳንቱ ልጅ እና ምክትል ፕሬዚዳንቱ ቴዎዶሮ ንጉዌማ ኦቢያንግ ማንጉ «ውጤቱ ትክክል መሆናችንን ያረጋግጣል። ትልቅ ፓርቲ ሆነን እንቀጥላለን» ብለዋል።

አንዳንድ የተቃዋሚ ዕጩዎች በምርጫው ቢሳተፉም አንዳቸውም ያሸንፋሉ ተብሎ አልተጠበቀም።

ፕሬዚዳንት ኦቢያንግ በነዳጅ በበለጸገችው የመካከለኛው አፍሪካዊት አገር ላይ ጠንካራ ቁጥጥር አላቸው። የቤተሰባቸው አባላትም ቁልፍ የመንግሥት ኃላፊነቶችን ይዘዋል።

በአውሮፓውያኑ 1979 ወታደሩ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ ወደ መሪነት የመጡ ሲሆን፣ ከበርካታ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች አምልጠዋል።

ከአጎታቸው ፍራንሲስኮ ማኪያስ ንጉሜ ቢሮውን ሲረከቡ አንዳንድ ማሻሻያዎችን ቢያደርጉም የንጉዌማን ፍጹማዊ የበላይነት በአገሪቱ ላይ አስቀጥለዋል።

ተቃዋሚዎችን የማይታገሱ ሲሆን ሁሉም መገናኛ ብዙኃን በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ ወይም በአጋሮቻቸው ቁጥጥር ስር ያሉ በመሆናቸው የነፃ ፕሬስ እጦት ከፉኛ በአገሪቱ ተስፋፍቷል።

ከዚህ ቀደም በሰብዓዊ መብት ረገጣ እና በምርጫ መጭበርበር የቀረቡባቸውን ውንጀላዎች ውድቅ ያደረጉት ፕሬዚዳንት ኦቢያንግ ስድስተኛ የስልጣን ዘመናቸውን በዓለም አቀፍ ደረጃ የጠለሸ ስማቸውን ለማጥራት እንደሚጠቀሙበት ተገምቷል። መስከረም ወር ላይ መንግሥት የሞት ቅጣት መሰረዙ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ድጋፍ ተችሯታል።

## አሜሪካ ሁዋዌ እና ዜድቲኢን ጨምሮ በአምስት የቻይና ኩባንያዎች ላይ እገዳ ጣለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ በብሔራዊ ደኅንነቷ ላይ አለ ካለችው ስጋት ጋር በተያያዘ ከአምስት ታላላቅ የቻይና ታዋቂ ኩባንያዎች ጋር ምንም ዓይነት ሽያጭ እና ግዢ እንዳይካሄድ እገዳ ጣለች።

ይህ እገዳ ግዙፎቹን የኮሚዩኒኬሽን ኩባንያ የሆኑትን ሁዋዌ እና ዜድቲኢን ጨምሮ በአምስት የቻይና ተቋማት ላይ ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን፣ በደኅንነት ስጋት ምክንያት አዳዲስ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ቁሳቁሶች ወደ አገሯ እንዳይገቡ እና እንዳይሸጡ ታዟል።

ሌሎቹ ስማቸው የተጠቀሰው እገዳው የተጣለባቸው የቻይና ኩባንያዎች ሂክቪዥን፣ ዳሁዋ እና ሃይቴራ የተባሉ ሲሆኑ፣ የቪዲዮ የደኅንነት መቆጣጠሪያዎች እና ባለሁለት ሞገድ የሬዲዮ ግንኙነት መሣሪያዎች አምራች ተቋማት ናቸው።

እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ በደኅንነት ስጋት ምክንያት በአሜሪካ ተቆጣጣሪ ተቋማት አማካይነት ሲወሰድ የመጀመሪያው ነው።

ውሳኔውን ተከትሎ ሂክቪዥን በሰጠው ምላሽ ምርቶቹ በአሜሪካ ደኅንነት ላይ ምንም ዓይነት ስጋትን አይደቅኑም ብሏል።

ጨምሮም የእገዳ ውሳኔው «የአሜሪካንን ብሔራዊ ደኅንነት በመጠበቅ በኩል የሚያበረክተው ነገር የለም። ይልቁንም የአሜሪካ ትናንሽ የንግድ ተቋማት፣ የአካባቢ ባለሥልጣናት፣ ትምህርት ቤቶችን እና ግለሰብ ተጠቃሚዎች እራሳቸውን፣ ቤታቸውን፣ የሥራ ቦታቸውን እና ንብረታቸውን ለመጠበቅ የሚያወጡትን ወጪ ከፍ በማድረግ ይጎዳቸዋል» ብሏል።

ሁዋዌ እና ሌሎች ኩባንያዎች ለቻይና መንግሥት መረጃ ያቀብላሉ በሚል የቀረበባቸውን ክስ አስተባብለዋል።

የአሜሪካ ፌዴራል መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ኮሚሽን እንዳለው፣ ይህ በቻይና ኩባንያዎች ላይ የተጣለው እገዳ በአባላቱ በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት አግኝቷል።

«ኮሚሽኑ አስተማማኝ ያልሆኑ የኮሚዩኒኬሽን መሣሪያዎች ፈቃድ አግኝተው ወደ አሜሪካ ገብተው ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በማድረግ ብሔራዊ ደኅንነትን ለማስጠበቅ ቁርጠኛ ነው» ሲሉ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ጄሲካ ሮሰንዊረቼል ባወጡት መግለጫ ጠቅሰዋል።

ጨምረውም «አዲሱ ትዕዛዝ በቴሌኮሚዩኒኬሽን አማካይነት ሊያጋጥሙ ከሚችሉ የብሔራዊ ደኅንነት ስጋቶች የአሜሪካንን ሕዝብ ለመጠበቅ እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች ዋነኛው አካል ነው» ብለዋል።

አሁን በቻይና ኩባንያዎች ላይ የተጣለው ዕገዳ ወደ ኋላ ሄዶ ተግባራዊ ስለማይደረግ፣ የተጠቀሱት ተቋማት ቀደም ሲል ወደ አሜሪካ እንዲገቡ ፈቃድ ያገኙ ዕቃዎች እንዲሸጡ ተፈቅዶላቸዋል።

ነገር ግን ቀደም ሲል ወደ አገሪቱ እንዲገቡ እና እንዲሸጡ የተፈቀዱትን መሣሪያዎች በተመለከተ ያለውን ውሳኔ መልሶ ለማየት ኮሚሽኑ አስተያየት እየጠየቀ ሲሆን፣ በዚህም የተሰጠው ፈቃድ ሊሰረዝ የሚችልበት ዕድል አለ ማለት ነው።

በቻይና የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ላይ የተጣለው ይህ እገዳ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያሳሰባቸው ካለው የስለላ ስጋት ጋር የተያያዘ ነው።

በቻይና ቴሌኮም ኩባንያዎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ እና በአሜሪካ ገበያ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴ የመገደብ እርምጃ የተጀመረው በባራክ ኦባማ የሥልጣን ዘመን ነበር።

በፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ አመራር ጊዜ ደግሞ ቁጥጥሩ የበለጠ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ እርምጃው በወቅቱ ፕሬዚዳንት ባይደንም ተግባራዊ እየሆነ ነው ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**


# የንድፈ ሃሳብ እውቀትን ወደ ችግር ፈቺ ፈጠራ ስመቀየር

እዮሩስ ተስፋዬ

የፈጠራ ሥራ ባለሙያ ነው፡፡ የሚኖረው ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዶዶላ ወረዳ - ተማሪ አብዱልቃድር ሁሴን፡፡ ወደ 25 የሚሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ያሉት ሲሆን፤ በ2014 ዓ.ም በተካሄደው የፈጠራ ሥራ ውድድር ላይ ‹‹ፉራ›› የሚባል የመኖ ማቀነባበሪያ ሠርቶ ለሽልማት ከመብቃት ባሻገር ፈጠራው አሁን ላይ ገበያውን ተቀላቅሏል፡፡ በዘንድሮው ዓመት ደግሞ በተመሳሳይ ስያሜ ‹ፉራ›› የምትባል በሞባይል ስልክ የሚቆጣጠሯት እና ሦስት ሰዎችን መያዝ የምትችል መኪና በመሥራት ለውድድር አቅርቧል፡፡

መኪናው ብትጠፋ እንኳን ደውሎ ለማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ እንደሠራ የሚገልጸው የፈጠራ ባለሙያው አብዱልቃድር፤ይህንን የፈጠራ ሥራ ከልጅነቱ ጀምሮ እየሠራበት እንደሆነም ያስረዳል፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው አብዱልቃድር ትምህርቱን አምስት ጊዜ ያቋረጠ ሲሆን፤ ይህም የሆነበት ምክንያት የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት የገንዘብ እጥረት የሚያጋጥመው በመሆኑ የቀን ሥራ በመሥራት የፈጠራ ሥራውን ለመደገፍ ሲል ትምህርቱን በተደጋጋሚ እንዲያቋርጥ ምክንያት ሆኗል፡፡ ‹ፉራ›› ከኦሮምኛ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ‹‹ችግር ፈቺ ማለት ነው›› ያለው ባለሙያው ይህንን የንግድ ስያሜ በመጠቀም ብዙ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት እቅድ እንዳለውም ይገልጻል፡፡

ሌላኛዋ የፈጠራ ሥራ ተወዳዳሪ ነቢሃት ነስሩ ስትሆን የ12ተኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ከወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ስቴም ማዕከል የመጣችው ተማሪዋ፤ የፈጠራ ውጤቷ ደግሞ በየቀኑ የብዙዎችን ሕይወት እየቀጠፈ እና ብዙዎችን ለአካል ጉዳተኝነት እየዳረገ ያለውን የመኪና አደጋ መከላከል የሚችል የሚገጠም ማሽን ነው፡፡ ለአብነትም መኪናው ከአሽከርካሪው ቁጥጥር ውጭ በሚሆንበት ወቅት ይህን




ሊቆጣጠር የሚችል የሚገጠም ማሽን፣ቁልቁለት ላይ አደጋ ከመፈጠሩ በፊት በሴንሰር አማካኝነት ራሱ ታኮ በማበጀት ከአደጋ ሊከላከል የሚችል ሲሆን ሌላው ደግሞ ጠጥተው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችን የአልኮል ሽታ የሚለይ ሴንሰር የመሪው ሲስተም ላይ በመግጠም ከመጠን ሲያልፍ የመኪናውን ሞተር በመቆለፍ ለትራፊክ ፖሊሶች በጂፒኤስ መልዕክት እንዲደርሳቸው የሚያደርግ የፈጠራ ሥራ መሆኑንም ታብራራለች፡፡


ይህንንም ለመሥራትም በመኪና አደጋ ምክንያት በየቀኑ ብዘዎች እየሞቱ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የሀገሯን ችግር ለመፍታት የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት እንደገፋፋት የምትገልጸው ነቢሃት ፤ይሁን እንጂ የፈጠራ ሥራዎችን ወደ ምርትነት ወይም ወደ ችግር ፈቺነት አለመቀየር ትልቁ ፈተና መሆኑን ታነሳለች፡፡ በቀጣይም ይህንን የፈጠራ ሥራዋን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እቅድ እንዳላትም ታስረዳለች፡፡አያይዛም የሴት የሥራ ፈጣሪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑን ከዚ አንጻር ብዙ መሠራት እንዳለበት ትጠቅሳለች፡፡

ከዚህ አኳያም የፈጠራ ሥራ ውድድር የንድፈ ሃሳብ ዕውቀትን ወደ ችግር ፈቺና ፈጠራ ሥራ ለመቀየር መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ትምህርት ሚኒስቴርና አጋር ድርጅቶች በመተባበር ለሰባተኛ ጊዜ ባዘጋጁት ዓለም አቀፍ የሳይንስ ቀን በተማሪዎችና መምህራን የፈጠራ ሥራ በተካሄደበት ወቅት መገለጹ ይታወሳል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ በወቅቱ እንዳሉት፤ የፈጠራ ሥራ ውድድር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቀሰሙትን የንድፈ ሃሳብ ዕውቀት ወደ ችግር ፈቺና ጠቃሚ የፈጠራ ሥራ ለመቀየር መልጋም አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡

ሚኒስቴሩ የተማሪዎች እና መምህራን የፈጠራ ሥራ ውድድር ላይ ለፈጠራ ባለሙያዎች ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ "ሳይንስ አውቀነው የምንቀመጥ ሳይሆን ወደ ተግባር በመቀየር የእለት ተእለት ኑሮአችንን የምናቀልበት ነው" ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤የሀገር እና የማሕበረሰብ ችግሮችን ለመቅረፍ በፈጠራ ሥራዎቻቸው ላይ ጠንክረው መሥራት እንዳለባቸው ለተወዳዳሪ ተማሪዎች እና መምህራን መልዕክታቸውንም አስተላልፈዋል።

ዶክተር ሰለሞን ቢኖር በትምህርት ሚኒስቴር የምርምር እና የማሕበረሰብ ጉድኝት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። እርሳቸው እንደሚያስረዱት ተማሪዎች በአጠቃላይም ይሁን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ክፍል ውስጥ ከሚማሩት ከንድፈ ሃሳብ ትምህርት ባለፈ የሚሠጡ ትምህርቶች ተጨባጭ እና ተግባር ተኮር እንዲሆኑ የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ተደርጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪም በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ጥሩ ተሰጥኦ እንዲኖራቸው እና የፈጠራ ውጤታቸውንም እንዲያጎለብቱ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ ( Science,Technology, Engineering And Maths (STEM) ማዕከላት እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ አሁን ላይ 38 የስቴም ማዕከላት ያሉ ሲሆን ፤በቀጣይም በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች እንዲስፋፉ እና አገልግሎታቸውም በአካባቢያቸው ለሚገኙ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ታስቧል፡፡ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር በሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ብቻ ሳይገደብ ማዕከላቱን በማቋቋም የፈጠራ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች አቅማቸውን እንዲያወጡ እና እንዲያጎለብቱ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነና በቀጣይም ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ዶክተር ሰለሞን ይጠቅሳሉ፡፡

# ስፖርት




# በአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ላይ ለውጥ ለማምጣት ይሠራል

**ብርሃን ፈይሳ**



የአትሌቲክስ ስፖርት ሩጫን፣ ዝላይና ውርወራን የሚያጠቃልል ስፖርት መሆኑ ይታወቃል:: ይሁንና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ትኩረቱን ያደረገው በሩጫ ላይ ያውም በረጅምና መካከለኛ ርቀቶች ላይ ብቻ ነው:: አገሪቷ ለስፖርት አስፈላጊ የሆኑ ጸጋዎች ቢኖሯትም በአግባቡ እየተጠቀመችበት ግን አይደለም::

አስቀድሞ የምትታወቅበት የረጅም ርቀት ውድድርም ቢሆን በተቆራረጠና ተተኪዎች እንደየወቅቱ በማይገኙበት ሁኔታ ቀጥሏል:: በቅርቡ ኦሊምፒክ እና የዓለም ቻምፒዮና ውድድሮች ላይ የአገራቸውን ስም በድል ሲያስነሱ የቆዩ አትሌቶች ፊታቸውን ወደ ጎዳና ላይ ሩጫዎች እየመለሱ መሆኑ ግልጽ ነው:: ለማሳያ ያህልም አልማዝ አያና፣ ገንዘቤ ዲባባ እና ለተሰንበት ግደይ ማንሳት ይቻላል:: በእርግጥ እነዚህ አትሌቶች አገሪቷ በምትታወቅበት ማራቶን ውጤታማ ሊያደርጓት ይችላሉ:: ይሁንና አሁን ላይ በእነሱ እግር የሚተኩ አትሌቶች መኖራቸው አጠራጣሪ ነው::

በመላው አገሪቷ በርካታ ፕሮጀክቶች፣ የማሰልጠኛ ማዕከላትና አካዳሚዎች እንዲሁም በግላቸው የሚንቀሳቀሱ ታዳጊና ወጣቶች ቢኖሩም የመተካካቱ ነገር ግን በሚፈለገው ልክ አይደለም:: ይህ ሁኔታ ታዲያ የስፖርት ቤተሰቡን ስጋት ላይ የሚጥል ጉዳይ ነው:: በሌላ በኩል ዓለም ትኩረቱን በአጭር ርቀቶች እና የሜዳ ተግባራት ላይ አድርጓል:: ኢትዮጵያ በተለይ የምትታወቅባቸው የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶችም ከበርካታ ውድድሮች ላይ መሰረዛቸው ለዚህ አንድ ማሳያ ነው:: በመሆኑም ከጊዜው ጋር ለመራመድ እንዲሁም ከስፖርቱ ከሚገኘው ጥቅም ተቋዳሽ ለመሆን በእነዚህ ስፖርቶች ላይ አተኩሮ መሥራት አስፈላጊ ስለመሆኑ አያጠያይቅም::

በዚህ ላይ ከትምህርት ቤት እና ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ላይ ካሉ አሰልጣኞች አንስቶ እስከ ታላላቅ የስፖርት ሳይንስ ምሁራን ድረስ ድርሻ አላቸው:: በአትሌቶች ምልመላ፣ የስልጠና ሂደት፣ አመጋገብ፣ በውድድሮች ላይ ስለሚከተሏቸው ቴክኒኮች እና ሌሎች ጉዳዮች ላይም በበቂ እውቀትና ሳይንሳዊ ዘዴ ካልተመራ ውጤታማ ሊያደርግ አይችልም:: በዚህ ረገድ ስፖርቱን የሚመራው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን መቆየቱን ፕሬዚዳንቷ ረዳት ኮሚሽነር ጀኔራል ደራርቱ ቱሉ ትጠቁማለች::

አገሪቷ ከምትታወቅባቸው ርቀቶች ባለፈ ውጤታማ ተሳታፊነትን ለማጠናከር ሲባል ፌዴሬሽኑ የአጭር ርቀት፣ ዝላይ እና ውርወራ ቻምፒዮናን ለብቻው በየዓመቱ በመደበኛነት ያዘጋጃል:: ከዚህ ውድድርም በምሥራቅ አፍሪካ እና በአፍሪካ ደረጃ በሚካሄዱ ውድድሮች ላይ የማሳተፍ ፍላጎት ቢኖርም ለተሳታፊነት የሚያበቃ ሚኒማ ማሟላት ግን አዳጋች ሆኖ መቆየቱንም አንጋፋዋ አትሌት ታስታውሳለች:: በመሆኑም የውድድር ዕድሎችን በማስፋት፣ የሚኒማ ማሟያ በማዘጋጀት እንዲሁም በክለቦች ውስጥ ካሉ አትሌቶች ሻል ያሉትን በእነዚህ ውድድሮች ለማሳተፍ ይሞከር ነበር:: ነገር ግን ከዚህ ቀደም ይደረግ እንደነበረው የተሻሉ አትሌቶችን በቀጣና ውድድሮች ላይ ማሳተፍ አልተቻለም:: ምክንያቱ ደግሞ ፌዴሬሽኑ የኤሌክትሮኒክስ ሰዓት መቁጠሪያ መሣሪያ ጥቅም ላይ በማዋሉ አጠጋግቶ በውድድር ማሳተፍ አስቸጋሪ ሆኗል::

ይህንን ችግር ለመቅረፍም ፌዴሬሽኑ የተለያዩ መንገዶችን ሲጠቀም ቆይቷል፤ አሁን ግን እንደመፍትሄ ያስቀመጠው በዘርፉ የተሻሉ አሰልጣኞችን ከውጭ አገራት ጭምር ማስመጣትን ነው:: ከአውሮፓ እና አሜሪካ ባይሆንም በአፍሪካ ልምድ ያላቸውን ከናይጀሪያ፣ ግብጽ፣ ደቡብ አፍሪካ እንዲሁም ሌሎች አገራት በማስመጣት ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ይሞከራል:: አቅም ከፈቀደ ደግሞ በአሰልጣኝነት ለማምጣት ማቀዱንም ፕሬዚዳንቷ ጠቁማለች::


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
### ጨረታ ቁጥር:- ሶ/ክ/ፕ/ሎ/ዌ/ፋ/009/2015

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሶማሌ ክልል ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል የICT እና የኤሌክትሮኒክስ የስቴሽነሪ ዕቃዎች ግዥ በሎት ለያይቶ በተጫራቾች መመሪያ ላይ በዝርዝር በቀረበው መልኩ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል::

| No | የሎት መደብ | የጨረታ ማስከበሪያ መጠን | የግዢው ዓይነት | የጨረታ መዝጊያ ቀንና ሰዓት | የጨረታ መክፈቻ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሎት 01 | 94,304.50 | የአይሲቲና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች | ለሎት 01 ታኅሣሥ 07/2015 8:30፤ | ለሎት 01 ታኅሣሥ 07/2015 8:45 |
| 2 | ሎት 02 | 29,710.50 | የስቴሽነሪ ዕቃዎች | ለሎት 02 ታኅሣሥ 07/2015 8:30፤ | ለሎት 02 ታኅሣሥ 07/2015 10:00፤ |

1. የጨረታው መስፈርቱን የሚያሟሉ በዘርፉ የተሰማሩ ብቃት ያላቸው የንግድ ድርጅቶች መሳተፍ ይችላሉ::
2. ተጫራቾች ዝርዝር መግለጫ የያዘውን የጨረታ ሰነድ መመሪያ የጨረታው ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15/አሥራ አምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ሎት በር 300.00/በመክፈል ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ በመምጣት መግዛት ይችላሉ::
3. ተጫራቾች የዘመኑን ግብር የከፈሉበት ማሳያ የታደሰ ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ ሠርተፍኬት ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሠርተፍኬት ኮፒ አድርገው ማቅረብ አለባቸው::
4. ተጫራቾች የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ ለሎት 01 ብር 94,304.50 ለሎት 02 ብር 29,710.50 በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል::
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን ለ ሎት 01 የICT እና ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ግልጽ ጨረታ ለሎት 02 የስቴሽነሪ ግልጽ ጨረታ ቁጥር ሶ/ክ/ፕ/ሎ/ዌ/ፋ009/2015 የሚል ምልክት በማድረግ ከላይ በተገለጸው ቀንና ሰዓት በተጠቀሰው አድራሻ ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በተጠየቀው መሠረት በግልጽ ማስገባት አለባቸው::
6. ጨረታው ከላይ በሳጥኑ በተገለጸው ቀንና ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይንም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት/ ባይገኙም በኢ/ኤ/አ/ሶማሌ ክልል ፕሮክሪዩመንት ሎጀስቲክ ፕሮፐርቲና ፋሲሊቲ ቢሮ ይከፈታል::
7. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሶማሌ ክልል ጽ/ቤት የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊልም የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::
8. ክፍያ ለመፈጸም በድርጅቱ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000068735487 መሆኑን እናሳውቃለን::
9. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 0252789353/0252782550 እና በኢሜይል plwsr2011@gmail.com በመደወል /በመጻፍ መረጃውን ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን::

ስልክ ቁጥር 0252789353/0252782550
ጅግጅጋ ከተማ ቀበሌ 05 ከሚገኘው የሚካኤል ህንፃ
በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሶማሌ ክልል ጽ/ቤት
ጅግጅጋ



## INVITATION FOR BID
### IFB Reference No. ECWCT/NCB/PG/63/2015

The Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC) hereby invites registered eligible bidders for SUPPLY & FIX MECHANICAL INSTALLATION WORKS. for (Ministry of justice head quarter renovation & compound work ) under National Competitive Bidding -NCB).

1. Interested Potential Bidders are required to present renewed relevant Trade License for the fiscal year, VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate, Online Supplier list Registration Certificate.
2. Bidding document should be prepared in English language.
3. Interested Potential Bidders obtain a complete set of bidding document from the office of Procurement department against payment of none refundable fee of Birr 300.00 upon presentation of Trade License renewed for the fiscal year; VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate and Online Supplier list Registration Certificate.
4. This invitation of bid is open to all interested potential bidders regardless of their nationality and the bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provision indicated in bidding document.
5. The deadline for bid Submission shall be on December 13,2022 at 03:00 PM
6. Bid must be accompanied with a Bid Security of an amount of Birr 400,000.00 (Four hundred thousand) in the form of certified cheque (CPO) or Bank guarantee.
7. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box situated at the office of the Procurement Department, before the closing date and time.
8. Bids will be opened on December 13,2022 at 03:30 PM. In Ethiopian Construction Works Co rporation Procurement Department office, in the presence of bidders and/or their representatives who choose to attend.
9. The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.
10. Bidders may get further information at the following address:

**Building Material Procurement Team. Gurd Sholla, In front of Andinet International School**
**P. O. Box 21952/1000, Addis Ababa, Ethiopia**
**Ethiopian Construction Works Corporation**